# መጽሐፈ ምሥጢር

## ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እንደደረሱት

(1357 ዓ/ም - 1417 ዓ/ም)

## ግእዝና አማርኛ

ትርጉም

በመምህር ሕሩይ ኤርምያስ

© 2001 ዓ/ም ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና ቅዱስ አባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም

**ይኸን መጽሐፈ ምሥጢር በመባል የሚታወቀው መጽሐፍ በታላቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ከዛሬ ስድስት መቶ ዓመት በፊት ተደርሶ ወደ አማርኛ በመተርጉም ለንባብ ያበቃው ጻድቁ የመሠረቱትና መጽሐፉን የጻፉበት የደብረ ባሕርይ ጋሥጫ ገዳም ነው::**

**መጽሐፉን በድጋሚ የማሳተም፣ የማስራጨትና፣ የመሸጥ መብት የቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና የአባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም ነው::**

የገዳሙ ምስጋና

ይኸንን መጽሐፈ መሥጢርን እና ሊሎቹንም በየገዳማቱና አድባራቱ የሚገኙ የቀደምት አበው ሊቃውንት መጻሕፍት እንዳይጠፉ በመጠበቅ እጅግ ብዙ መከራዎችን አሳልፈው ለኛ ያደረሱ ሊቃውንት፣ መምህራን፣ ገዳማውያን፣ ማኅበረ መነከኩሳት በሙሉ ታሪክን በመጠበቅ ላበረከቱት አስተዋጾኦ የአምላክ ቸርነት አይለያቸው እያልን አሁንም የቀደሙት አባቶች በክብር ያቆዩትን ታሪክ በአግባቡ ለትውልድ እንዲተላለፍ ለሚደክሙ ሁሉ ብርታቱን ይስጥልን እንላለን:: ይኸንን መጽሐፍ በተመለከተ በትርጉም የረዱን የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ምሩቅና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድኅረ ምረቃ ክፍል የሥነ ልሳን ማስተርስ ተማሪ የሆኑት መምህር ሕሩይ ኤርምያስን ትርጉሙን በድጋሜ በማንበብና መቅዱሙን በማዘጋጀት የተሳተፉትን መምህር ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መምህርን በመጨረሻም ለሕትመት እንዲበቃ በገንዘብና በሐሳብ ረዱንን ሁሉ የጻድቁ በረከት አይለያችሁ::

ማኅበረ መነኮሳቱ

መጋቢት ፳፻ወ፩ ዓ/ም



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጬጌ
ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት
የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም ምክር ቤት የክብር ፕሬዚዳንት

አዲስ አበባ



ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል
ደቡብ ወሎ፡ ደሴ

ይኽ መጽሐፈ ምሥጢር የተባለ የቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ መጽሐፍ

መምህር አባ ክፍለማርያም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት የቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና የቅዱስ አባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት
ገዳም አበ ምኔት በነበሩበት ጊዜ በገዳሙ ባሉ ማኅበረ መነኰሳት ኅብረት ታተመ።

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፡ ፩ዱ አምላክ፡፡ አሜን፡፡

*‘ፍቅር ያጌብረኒ ነጊረ ዜናሆሙ ለቅዱሳን፡፡ወቅንዐት ያጌብረኒ ከመ እሰብሖ ለክርስቶስ፡፡ወቅንዐት ያጌብረኒ ከመ እውግዞ ለሰይጣን፡፡ፍቅር ያጌብረኒ ከመ እትአምሙ ለሐዋርያተ ክርስቶስ፡ወቅንዐት ያጌብረኒ ከመ እኰይሮሙ ለረሲዓን፡፡ፍቅር ያጌብረኒ ከመ እጽአሎሙ ለግርያን፡፡*

*የቅዱሳንን ዜናቸውን ለመናገር ፍቅር ግድ ይለኛል፡ ቅንዐትም ከሃዲዎችን እንቅፋቸው ዘንድ ያስገድደኛል፡፡ ፍቅር ክርስቶስን እንዳመሰግነው ግድ ይለኛል፡ ቅናትም ሰይጣንን እወግዘው ዘንድ ያስገድደኛል፡፡ፍቅር የክርስቶስን ሐዋርያት እንደ ከተላቸው ያስገድደኛል ቅናትም ዝንጉዎችን እንድ ሸሻቸው ግድ ይለኛል፡፡ ፍቅር ሰማዕታትን አወድሳቸው ዘንድ ግድ ይለኛል ቅናትም ጠንቋዮችን እንድ ዘልፋቸው ያስገድደኛል፡፡ ’ (አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ መጽሐፈ ምሥጢር ገጽ ፺)*

ኢትዮጵያዊው ሊቅና ጻድቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተወለዱት በ፲፫፻፶፯ዓ/ም በወሎ ክፍለ ሀገር በቦረና ወረዳ ሸግላ/ሰግላ በተሰኘች ቦታ ነው፡፡ አባታቸው ሕዝበ ጽዮን ከተከበሩ መምህራን ወገን የሆኑ የቤተ መንግሥት ባለሟል፣ መጻሕፍትን የሚያውቁ ጥበብ የተመሉ ሲሆን የሰግላ ሀገረ ገዥም ነበሩ፡፡ እናታቸው እምነ ጽዮንም ከወለቃ ሹምምንት ወገን የሆኑ ደግ ሰው ነበሩ፡፡ በመጀመሪያ እናታቸው ፈሪሃ እግዚአብሔርን እያስተማሩ በጥበብና በዕውቀት አሳደጓቸው፡፡ አባ ጊዮርጊስ የተመረጠ የሆነ ሰማዕቱን ቅዱስ ጊዮርጊስን በመማፀን የተወለዱ ልጃቸው ስለሆኑ እንደሰማዕቱ የእውነት ምስክር እንዲሆኑላቸው በመመኘት ስማቸውን ጊዮርጊስ ብለው ጠርተዋቸዋል፡፡ ከተወለዱበት ሀገር በመነሳት ጊዮርጊስ ሰግላዊ ተብለው ሲጠሩ በጊዮርጊስ ዘጋሥጫና በጊዮርጊስ ሰግላዊ ለካከል ምንም ልዩነት የለም፡፡




የአባ ጊዮርጊስ አባት ሕዝበ ጽዮን በቤተ መንግሥት በንጉሡ ሥዕል ቤት ከሚያገለግሉ ካህናት ጋር ስለነበሩ ልጃቸውን በመልካም አስተዳደግና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በማስተማር በዕውቀት አሳድገዋል፡፡ ወደ ጳጳሱ ወስደው በዲቁና ማዕረግ አሾመዋል፡፡ ከዚህም በኋላ በንጉሥ ዳዊት ዘመን (፲፫፻፸፮- ፲፬፻፲) በደብረ ሐይቅ ባሕር ወደምትገኝ የቅዱስ እስጢፋኖስ አባ ኢየሱስ ሞዐ ገዳምና ታዋቂዋ ትምህርት ቤት ወስደው ከታላቁ ሊቅ ዓቃቤ ሰዓት አባ ሠረቀ ብርሃን ጉባዔም ተቀላቅለው እንዲማሩ አድርገዋል፡፡ ይሁን እንጅ አባ ጊዮርጊስ በትምህርት ቤቱ የሚሰጡትን የቀለም ትምህርቶች ቶሎ ለማጥናት አልቻሉም፡፡ ወደ ኋላ የመቅረታቸው ዋናው ምክንያትም አባ ጊዮርጊስ ከመማሩ ይልቅ የማረካቸው በሥራ እየደከሙ የገዳሙን አባቶች መርዳትና የብሕትውን ሕይወት መሆኑ ነው፡፡ ጓደኞቻቸው በትምህርት ሲቀድሙአቸው ባዩ ጊዜ እጅግ አዘኑ፡፡ በጾምና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ጮኹ በፍጹም ልባቸው አምነው ብርቱ ልመናን ከእመቤታችን ሥዕል ፊት ቆሞ በጠለቀ ተመስጦልብና እንባን በማፍሰስ ወደ እግዚአብሔር “የአባቶቻችን አምላክ የምህረት ጌታ ሁሉን በቃልህ የፈጠርክ ሰውንም በረቂቅ ጥበብ የፈጠርክ አቤቱ አንተ ከልዑል ጌትነትህ ጥበብን ስጠኝ በእውነትም አትናቀኝ እኔ ባሪያህ ነኝና የባሪያህም ልጅ ነኝና” በማለት ለመኑ፡፡ ከዚህ በኋላ የዓለም ንግሥት የአምላክ እናት ተገለጸችላቸው፡፡ በነሐሴ በሃያ አንደኛው ቀን ወደርሳቸው መጣች፣ በዕውቀትና በትምህርት የሚተጉበትንም ኃይል ሰጠቻቸው፡፡ ከዚያም የዜማ የቅኔና የመጻሕፍትን ትርጓሜ ትምሕርታቸውን በሚገባ አጠናቀቁ ብዙ መጻሕፍትንም ደረሱ፡፡

በዜማ በኩል ከቅዱስ ያሬድ ቀጥሎ የሚጠሩት አባ ጊዮርጊስ ናቸው፡፡ ራሳቸውን በልዩ ልዩ ድረሰቶቻቸው የቤተ መቅደሱ ዘማሪ፣ ማኅሌታይ እያሉ ይጠራሉ፡፡ በአፄ ዳዊት ዘመን የድጓ ምስክር ትምህርት ቤት የነበረው የደብረ ነጎድጓድ መሪ ነበር፡፡ ከገድሉ መረዳት እንደሚቻለው «ከዚህ በኋላ ጊዮርጊስ ለነገሥት፣ ለካህናት፣ ለመኳንንት ለንቡራነ እድ፣ ለመሳፍንት፣ ለሁሉም የቤተ መንግሥት ሠራተኞች አስተማሪ ሆነ፡፡ ለማስተማር እየተጋ፣ እየደከመ፣ የአራቱን ሕግ እያስጠበቀ፣ ከበሮውን በማስመታት፣ በማስማት መሰከቱን በማስነፋት የመንግሥተ ሰማያት ወንጌል በማብሰር በሐዋርያት ቀኖና መሠረት በመጋደል በዳዊት መዝሙር በገና በመምታት በልጁ በሰሎሞን ምስጋና በማመስገን በያሬድ ማኅሌት በማመስገንና ይኸውም የኢትዮጵያ ብርሃን የሆናት ቅዱስ ያሬድ በደረሰው የማኅሌት ዜማ በማመስገን ሲደክም ኖረ፡፡ እርሱ የጋርማ ሰው ከሆነ ከአቡነ ሳሙኤል ዜማን ተምረዋል፡፡ እርሱም ራሱ ብፁዕ ጊዮርጊስ ከብሉይና ከሐዲስ ፍሬ ያጠራቅማል ይሰበስባል በድርሰት ቀንድም ያመሰግናል፡፡ ለቅዱስ ጴጥሮስና ለቅዱስ ጳውሎስም በሰማዕትነት ከረፉባት ከሐምሌ ፭ ቀን ጀምሮ በ፲፪ቱም ወራት የሚመሰገኑበት ማኅሌት ደረሰላቸው፡፡ ለሐዋርያት ሁሉ በየስማቸው በአባቶች ዘንድ የታወቀ ማኅሌት አዘጋጀላቸው፡፡ ብፁዕ ጊዮርጊስም በሚዘምርበት ጊዜ ሕዝቡ አሕዛቡ በቤተ ክርስቲያን ይሰበስቡ ነበር፡፡ በመስማትም ይመሰጡ ነበር፡፡» ይላል፡፡

ሊቅነታቸውን የተረዱት አጼ ዳዊት አባ ጊዮርጊስን ወደ ቤተ መንግሥታቸው በማስገባት የስምንቱም ልጆቻቸው መምህር አድርገዋቸው ነበር፡፡ ከእነርሱ ውስጥ ቅዱስ የተባለው ንጉሥ ቴዎድሮስ እንዲሁም በተለያየ ጊዜ የነገሡት ንጉሥ እንድርያስ ንጉሥ ይስሐቅ ንግሥት እሌኒ እና ንጉሥ ዘርዓያዕቆብ ይገኙበታል፡፡ በአፄ ዳዊት ቤተ መንግሥት እያሉ ንጉሡ አባ ጊዮርጊስን በጋብቻ ተዛምደው ለመሾም በፈልጉም ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ራሳቸውን የመንግሥተ ሰማያት ጃንደረባ ማድረግን ስለመረጡ ሹመቱንም ማግባቱን ትተው በማተማሩና በብሕትውና ጸንተው የአምክሮ ጊዜያቸውን ሲጨርሱ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ገብተው መንኩሰዋል፡፡

በዘመኑ ሰተነሱ ለሁሉም የሃይማኖት ችግሮች አጥጋቢ መልስ በመስጠት የተዋህዶ ጠበቃ አይሁድን እና ሌሎች መናፍቃንን በጉባዔ ያሳፈሩት ሊቅ ከቶዎች እና ምቀኞች በየጊዜው እየተነሱ መከራን ያደርሱባቸውና ይከሱአቸው ነበር፡፡ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ እንደ ሰማዕታት ግርፋትንና እሥራትን፣ እንደ ሊቃውንት የመናፍቃንና የከሀድያን ክርክር፣ እንደ መሐንዲስ ሐናጺ፣ የሕግና የሥርዓት የምሥጢራትና የትርጓሜያት መምህር፣ የጸሎትና የትምህርት መጻሕፍት ደራሲ፣ የሥርዓተ ገዳምና ማኅበረ መነኮሳት አባት እንዲሁም ቢያንስ የአንድ ትምህርት መሥራች ሲሆኑ በግዞት በሄደባቸውና በታሰሩባቸው ቦታዎችም ሆነ በተሾሙባቸው እንደ ደብረዳሞ ገዳም በመሰሉ ቦታዎች ሁሉ ሲያስተምሩና ሲገስጹ ኖረዋል፡፡ በድርሰቱ እስከአሁን በሀገራችን ተወዳዳሪ የላቸውም፡፡ እጆቻቸው ከብዕር በተጨማሪ ከጠንካራ ሥራ ሳይቦዝኑ ዋሻ ሲፈለፍሉ የውሃ ጉድጓድ ሲቆፍሩ ድልድይ ሲሠሩ ኖረዋል፡፡ አንደበታቸውና እና ህሊናቸው ከምስጋና ሳያቋርጡ ለቤተክርስቲያን የጸሎት እና የምስጋና ሥርዓት ሲተጉ ኖረው በጽድቅና በቅድስና ህይወት እንዳጌጡ ተዋህዶ ከካብ ሆኖ በተወለዱ በ60 ዓመቱ 1417 ዓ/ም ሐምሌ 7 ቀን አርፈዋል፡፡ ተማሪዎቹም በመሪረ ሐዘን ሆነው አጽማቸውን በጋሥጫ ራሳቸው ፈልፍለው በእመቤታችን ስም በሠሩት ገዳሙ ውስጥ አስቀምጠውታል፡፡

በትምህርቱ የተመሠጡት ምዕመናን እና የቤተክርስቲያን ሊቃውንት በ፲ኛ ዘመን የተነሱት አዲሱ ዮሐንስ አፈወርቅ ሲሏቸው አፄ ይስሐቅ ደግሞ መናፍቃንን ሁሉ በማሳፈሩና በረቂቅ ድርሰቶቻቸው ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ ብለውታል፡፡

ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ በደብረ ሐይቅ    እመቤታችን የብርሃን ጽዋን እንደሰጠቻቸው    እመቤታችን አርጋኖንን እንደሰጠቻቸው

## ደብረ ባህርይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳም

ደብረ ባህርይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳም የተመሠረተው በታላቁ ሊቅ በአባ ጊዮርጊስ ሲሆን በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት በከላላ ወረዳ ይገኛል። ተፈጥሮአዊ ውበቱ እጅግ የሚማርክ አስገራሚ የሆነ አቀማመጥ እና ግርማ ያለው ይህ ገዳም የተመሠረተበት ዘመንም አባ ጊዮርጊስ ካስተማሯቸው ነገሥታት በአጼ ይስሐቅ ዘመን ነው። የበርካታ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ቅርሶች ባለቤት የሆነው ይህ ገዳም ከ፮፻ ዓመት የሆነው ሲሆን በዚሁ ቦታ አባ ጊዮርጊስ በርካታ ድርሰቶችን ደርሷል። በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ አህመድ ጥፋት ከአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ጋር ከፍተኛ ጉዳት ቢደረሰበትም ብዙም ሳይቆይ እንደገና ተመሥርቷል። የመሠረቷት ጋሥጫ ገዳምም ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ለመባል ምክንያት ስተሆን በተወለዱበት በሰግላም አባታቸው ሕዝበ ጽዮን ያገለግሉበት የነበረው ቤተ ክርስቲያን አሁንም ፍራሹ ይገኛል። ከዚህ ቦታ ጋር በማያያዝ አንዳንድ ጊዜ ጊዮርጊስ ሰግላዊ ይባላሉ።

ወደ አምባው ለመውጣት አንድ በር ብቻ ሲኖረው እርሱም የሚወጣው እንደ ደብረ ዳሞ በገመድ ወይም እንደ ጣና ገዳማት በጀልባ ሳይሆን በሁለት እርከን ተካፍሎ 46 ሜትር ከፍታ ያለውን መሠላል በመጠቀም ነው።አባ ጊዮርጊስም መሠላሉን የሠሩት በቋጥኞች መካከል እንጨቶችን በመረብረብ ነው። ይኸውም ታሪካዊና አስገራሚ ነው። ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ራሳቸው ፈልፍለው የሠሩት ዋሻ ቤተክርስቲያን ቅኔ ማኅሌት ቅድስት እና መቅደስ አለው። ወደ ውስጥ መግቢያ ሦስት በሮች ሲኖሩት ውስጣዊ ክፍሎች በምሰሶዎች እና በተፈጥሮ አለቶች የተከፈሉ ናቸው።አስገራሚ የሆኑ የብርሃን ማስገቢያ መስኮቶችም አሉት። በዚህም አባ ጊዮርጊስ ድርሰት የደረሱበት ዋሻ የክርስትና ቤት እና የቅዱሳን መካነ አጽም ከአለቱ ተፈልፍለው ተሰርተዋል። ከቤተክርስቲያኑ በተጨማሪ በውጭ በስተምስራቅ ከእዚያው ወጥ አለት የተፈለፈሉ የቤተልሔም እና ሌሎች ጸሎት ማድረጊያ ዋሻዎች ይገኛሉ። ሌላው እጅግ በጣም አስገራሚው ነገር በዚያው አምባ ላይ ያለውን የውሃ ችግር ለመቋቋም አባ ጊዮርጊስ የቆፈሯቸው ውሃ ከማያሰርግ አለት የተሠሩ የውሃ ማቆሪያዎች ናቸው። እነዚህም እያንዳንዳቸው ከ2000 ሊትር በላይ የመያዝ አቅም አላቸው። በጋስጫ እና አባ ጽጌ ድንግል ገዳም መካከል የነበረው የወለቃ ወንዝ ለመሻገር እንዲያመች  የሠሩትን የአለት ድልድይ ጨምሮ ሌሎቹን አስገራሚ ሥራዎቹን ስናስተውላቸው አባ ጊዮርጊስ ቀዳሽ መነኩሴ ብቻ ሳይሆኑ /ደራሲ/ ጸሐፊ እና አስተማሪ ከዚያም አልፎ የስነ ጥበብ ሊቅ የህንፃ እና የድልድይ ሐናፂ እንደነበሩም የሚመሰክር ነው። ትምህርት ቤትና ማኅበረ መነኮሳትንም በማደራጀት ዛሬ ፰ የሚሆኑ መናንያን ቅርስ እየተጠበቁና መንፈሳዊ አገልግሎት እየተሰጠበት ይገኛል።





ደብረ ባህርይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ገዳም   / ወደ አምባው የሚያወጣው መሰላል/   በአባ ጊዮርጊስ የተቆፈረው የውሃ ማቆሪያ

## የቅዱስ አባ ጊዮርጊስን ሥራዎች በተመለከተ ገድሉ በሚከተለው ቅደም ተከተል አስቀምጧል

### ኆኅተ ብርሃን

«ከዕለታት በአንዳቸውም እንዳስለመደው ከመቤታችን ሥዕል ፊት ቁሞ ሲጸልዩ ክብር ስግደት ይግባትና በፍቅር ተመስጦ ልቡና ሕሊናውን ወደሷ አበረረ ሮጦ ሄደም ሥዕሏን አቀፎ የሥዕሊቱን ጡት በጸጋ ጠባ። ያን ጊዜ ኆኅተ ብርሃን የተባለችውን መጽሐፍ ለምስጋናዋ ክብር በበዓለቷ ሁሉ እንድትነበብ ደረሰለት። ከዚህም በኋላ በሐይቅ ደሴት የተሠራችውን ቤተ ክርስቲያን በማኅሌት ቃል አስደሰታት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሀገር ሰዎች ሁሉ መጻሕፍቱንና ትርጓሜአቸውን እንዲሁም ለማኅሌት የሚሆኑ ድርሰቶችን ሁሉ ይለምኑ ጀመሩ። ሥዕሏ አሁንም በደብረ ሐይቅ የምትገኝ ሲሆን «አጥባተ ድንግል» ትባላለች። ኆኅተ ብርሃንም የመጀመሪያ ድርሰታቸው ናት።

### መጽሐፈ አርጋኖን

«አርጋኖን» የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ «ምስጋና[ዎች]» ማለት ነው። በመዘሙረ ዳዊት በገና ከሚባለው ዐሥር አውታር ካለው የዳዊት የዜማ ዕቃ ጋር አብሮ ተተርጉሟል። ለምሳሌ «በመዝሙር ዘበዐሥርቱ አውታሪሁ...» ሲል

የግሪኩ መዝሙር በሚለው እርጋኖን ይላል። ጽንሰ ሐሳባዊ ትርጉሙ ግን በገና ለማለት ነው። አባታችን ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍቶችም የተሠወረው ምሥጢር ተገልጾለት። የእግዚአብሔር ወዳጅ በሆነ በንጉሥ ዳዊትም ዘመን እርጋኖን የተባለውን የምስጋና መጽሐፍ ደርሶ ጸፈው። ይህንም መጽሐፍ እርጋኖን ውዳሴ መሰንቆ መዝሙር፣ ዕንዚራ ስብሐት በማለት ሰየመው። ከመጽሐፉ ቃል መጣፈጥ የተነሳም ንጉሡ አጼ ዳዊት በወርቅ ቀለም አጻፈው።

## ውዳሴ መስቀል

ከዕለታትም በአንድ ቀን ጴጥሮስና ጳውሎስ መስቀል አምጥተው ከፊቱ ቢያስተምጡት የመስቀሉ ቁመት በሰውነቱ ልክ ሆነ የመስቀሉም ግራና ቀኙ ክንፉ በጊዮርጊስ በክንዱ ልክ ሆነ። ... ያንጊዜም የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን በልቡና አበራለትና ውዳሴ መስቀል የተባለውን ድርሰት ደረሰ። በመስቀሉ ክብርና ትርጉም ዙሪያ የሚያስረዳ ረቂቅ ጽሑፍም ነው።

## መጽሐፈ ብርሃን

ሁለተኛም በመዓልትም በሌሊትም በየሰአቱ የሚጸለይ የምስጋና መጽሐፍን ደረሰ። ስሙን መጽሐፈ ብርሃን ብሎ ጠራው። የጌታችን የእግዚአብሔርን የጌትነቱን መንገድ የሚያሳይ ድርሰት ነውና። ብርሃንን የተጐናጸፉ የቅዱሳንን መንገድና የትጉሃን መላእክትን መንገድ ያሳያልና። ዳግመኛም የድንግል ንጽሕት ማርያምን ምስጋና በማጣጣም ይናገራል የአብ ሙሽራ፣ የበጉ እናት (ሕመ በግዑ)፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አክሊል በማለት ያመሰግናታል። በዚህ መጽሐፍ ስያሜም በኋላ ዘመን ሌሎች ድርሰቶች ተደርሰዋል።

## መጽሐፈ ሰዓታት ዘመዓልት ወዘሌሊት

ይኽ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰፊው የሚታወቅና በየእለቱ አግልግሎት ላይ የሚውል የዜማው ሥርዓት ከቅዱስ ያሬድ ምሥጢሩ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ የሆነ ድርሰት ነው። በቀንና በሌሊት በተከፈሉ የሥርዓቱ አደራረሶቹ ውስጥ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባባት፣ የጥንት ድርሰቶች የሆኑ መስተብቍዓትና ሊጦናት አሉበት። የሥርዓቱ አጠቃላይ መዋቅር የተደረሰው በአባ ጊዮርጊስ ነው። ከዚሁ ጋር የበኋ ሊቃውንት «እንደ ሰላምታ» «ሰቤሐተ ፍቁር» በመሰሉ ክፍሎቹ ውስጥ ከሊቁ በኋላ ተነሱ ቅዱሳንን ስም በማመሳሰል አካተዋል። የዚህን መጽሀፍ ድርሰት እየቆራረጡ እንኳን በድርሰት በበጎ ምግባራቸው የማይታወቁ ነገሥታት ጸፉት ማለት መሠረት ወይም ምስክር ያለው አይመስልም። በሰዓታት ውስጥ ሊቁ እንደ መጽሐፈ ምስጢር ሁሉ ምሥጢረ መለኮትን፣ ነገረ ማርያምን፣ ነገረ ቅዱሳንንና መላእክትን አስፍተውና አምልተው በረቂቅ የዜማ ሥርዓት ደርሰዋል። ወደ ሥነ ፍጥረትም በመሄድ ድንቅ የሆኑ የተፈጥሮ ክስተቶችን በምርምር ጽፈዋል። ለምሳሌ ረቂቅ ደመና ከውሃማ/ርጥብ አካላት በተን ተነስቶ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ቀዝቅዞ ዝናም እንዴት እንደሚሆን ይገልጻሉ። እነዚህም ሊቁን የረቀቀ ሥነ ተፈጥሮአዊ ምርምር ለማወቅ ይረዳል። ከዚሁ ጋር ተደምረው የሚደረሱ ነገር ግን ለየራሳቸው የሆኑ እንደ መልክዐ ውዳሴ፣ መልክዐ ሥዕል፣ ያሉትም ተጨማሪ ሥራዎች ሲሆኑ ከሰዓታት እየወጡ የሚጸለዩት እንደ «ይዌድስዋ መላእክት» እና «ነአኵተከ» ያሉት ሊቁ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው የደረሷቸው ናቸው።

## የቅዳሴ መጻሕፍት (መዓዛ ቅዳሴ)

ከዕለታት አንድ ቀንም አንድ አይሁዳዊ የእግዚአብሔር ፊቱ ወዴት ነው ብሎ ክርስቲያኖችን ጠየቃቸው። የሚመልስለትም ሰው አልተገኘም። አባ ጊዮርጊስ ግን ለመለኮት ሳይና ታች፣ ወርድና ቁመት፣ ቀኝ ግራ ያለው ፊትና ጀርባ ያለው አይደለም በሁሉ የመላ ነው እንጂ ብሎ መለሰለት። በወቅቱ የነበረው ጳጳስም ይህን ሲመልስለት ሰምቶ በጣም ተደሰተ ከደስታውም ብዛት የተነሳ ሳመው ባረከው ቅዳሴ እንዲያርስም ፈቀደለት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በወንድሞች ዘንድ የታወቀች የቅዳሴ ጸሎትን ደረሰ ይቺውም «መዓዛ ቅዳሴ ናት» ከዚሁም ጋር በተያያዘ ብዙ የታሪክ ሊቃውንት በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚታወቁ ከዐሥራ ዐራት እስከ ዐሥራ ስምንት የሚደርሱ ቅዳሴያት የአብዛኛዎቹ ደራሲ አባ ጊዮርጊስ ናቸው ብለው ያምናሉ።

## ጸሎት ፈትቶ

ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ የደረሱትን ጸሎተ ፈትቶ በቤተ ክርስቲያን ካህናት ሲቀድሱበት ሰምቶ አንድ ሰው ምንድር ነው ይህ ቅዳሴ ከሐዋርያት ያልመጣ ከሊቃነ ጳጳሳት ያልተገኘ አሁን ይህ ሥጋ ወደሙ ይለውጣል? በማለት በነሲናው ተጠራጠረ። ያም ሰው አባ ጊዮርጊስን ይጠላው ነበር ይንቅፈው ነበረ፣ አያከብረውም ነበር በዚያም ሰው እግዚአብሔር ተቆጣበትና የእርዮስ አንጀት ተዘርግፎ እንደወጣ ከውሀ ቤት ተቀምጦ ሳለ አንጀቱ ተዘርግፎ ወጣ። በዚህም የድርሰቱ ቅንነት ተረድተው በየቅዳሴው የሚጸለይ ሆኗል።

## ውዳሴ ሐዋርያትና የሐዋርያት ማኀሌት

ከዚህ በኋላ ንዑድ ክቡር ጊዮርጊስ ሐዋርያትን በማኀሌት ያመሰግናቸው ጀመረ። ለቅዱስ ጴጥሮስና ለቅዱስ ጳውሎስም በለማዕትነት ከረፋበት ከሐምሌ ፭ ቀን ጀምሮ በ፲፪ቱም ወራት የሚመሰገኑበት ምስጋና ደረሰላቸው። ለሐዋርያት ሁሉ በየስማቸው በአባቶች ዘንድ የታወቀ ምስጋናን አዘጋጀላቸው። ዳግመኛም ውዳሴ ሐዋርያት የተባለ መጽሐፍን ጽፏል።

## መልክዐ ቍርባንና የቍርባን ሥርዓት

ከዕለታት በአንድ ቀን አባ ጊዮርጊስ ቀድሶ በሚያቆርብበት ጊዜ ተራዳኢው ካህን ጋር ሕዝቡን ሲያቆርቡ ከመቅደስ በወጡ ጊዜ አባ ጊዮርጊስን ንጉሥቲቱን ካለችበት ሂደን እናቁርባት አለው። አባ ጊዮርጊስ ግን አይሆንም እርሷ ካለችበት ተነስታ ትምጣና ትቁረብ አለው። ከዚያ በፊት ካህናቱ ነገሥታቱ ከቆሙበት ድረስ ወስደው የማቁረብ ልማድ ነበረና። ይህን ሲነገረው አይሆንም ቁርባኑ ንጉሡ ነገሥት ነውና መሄድ የለበትም በማለት መጥታ እንድትቆርብ አደረገ። በዚያውም መልክዐ ቍርባንን ደርሷል። በዚህም ሊቁ ምን ያህል ለሕግና ለሥርዓት የቆሙ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል።

## ፍካሬ ሃይማኖት

ከዕለታትም አንድ ቀን አንድ ስሙ ቴዎድሮስ የተባለ መስፍን /ገዥ/ ስለቀናች ሃይማኖት ጠየቀው:: ስለዚህ ፍካሬ ሃይማኖት የተባለች ድርሰች ደርሶ ጽፎ ሰጠው:: ይህን መጽሐፍም ንጉሡና ምሥጢር የሚያውቁ ካህናት በአነበቡት ጊዜ በእውነት ይህ ሰው እንደዮሐንስ አፈወርቅና እንደ አፈ በረከት ቄርሎስ ነው:: በዘመናችን እንደነሱ ሆኖ ተነሳ ኢትዮጵያ ቁስጥንጥንያን መሰለች እስክንድርያንም ተስተካከለቻት አሉ:: ፍካሬ ሃይማኖት በመጠኑ እንደ ጸሎተ ሃያማኖት ያነሰ ሆኖ ከመጽሐፈ ምሥጢር ጋር የሚያመሳስለው ጉዳይ አለ:: በፍካሬ ሃይማኖት መጽሐፍ የተጠቀሱት መናፍቃን በመጽሐፈ ምሥጢር ተጠቅሰዋል::

በገድሉ ውስጥ በቀጥታ ያልተገለጹ በታሪክ የሚታወቁ ሌሎች ድርሰቶቻቸውም በመጠኑ ለመጥቀስ ያህል አንዚራ ስብሐት፣ መሰንቆ መዝሙር፣ ሕይወታ ለማርያም፣ ተአምኖ ቅዱሳን፣ ጸሎት ዘቤት ውስተ ቤት፣ ውዳሴ ስብሐት ወሰላምታ፣ ጸሎተ ማዕድ፣ ቅዳሴ እግዚእ ዘአባ ጊዮርጊስ፣ ውዳሴ ማርያም ዘአባ ጊዮርጊስ፣ መዝሙረ ድንግል፣ መልክዐ ውዳሴ ፣ ይዌድስዋ መላእክት (የሰዓታት ክፍል)፣ መልክዐ ሥዕል ይገኙበታል::

## መጽሐፈ ምሥጢር

በገድሉ እንደተገለጸው ከዕለታትም በአንዳቸው ገና የሌሊት እኩሌታ ሳይሆን አባ ጊዮርጊስ ተማሪዎቹን ሁሉ ከተኙበት ቀስቅሶ ተነሱ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ አላቸው:: ልጆቹም አባታችን ጊዜው ገና ነው አሉት:: እርሱም አይሆንም አትስነፉ ይልቁንም ፈጥናችሁ ተነሡ አላቸውና እሺ በማለት ተከትለው እየሄዱ በመንገድ ላይ ሳሉ መንፈስ ቅዱስ ከመንገድ መካከል አቆመው:: ኅሊናውን በተመሰጠ ወደ ሰማይ ወሰደው:: እጁንም ዘርግቶ ወደ ላይ አንጋጠጠ ብዙ ጊዜ ቆየ:: ያን ጊዜ ልጆቹ አባታችን ሆይ ወደ ቤተክርስቲያን እንሂድ ያለዚያም ወደ ቤታችን እንመለስ አሉት:: ኅሊናው ወደ ሰማይ በተመስጦ ሄዶ ስለነበረ የሚናገሩትን አይሰማቸውም ነበር:: ... መጽሐፈ አሪትን ሊያጽፍባቸው ወዶ አዘጋጅቶ ያስቀመጣቸው የተዘጋጁ የተጠረዙ ብራናዎች ነበሩትና እነርሱን አቀረበ:: እነዚህን ጥራዛትና ፭ ጸሐፊዎችን አስመጥቶ ቤቱ ፀሐይ እስከሚመስል ድረስ መብራት አበርቶ እኒያን ጸሐፊዎች የምነግራችሁን ለመጻፍ ፍጠኑ አላቸው:: በየክፍሉ እየነገራቸው እስከሚነጋ ድረስ ጻፉ ያንንም መጽሐፍ በሁለት ቀን ጽፈው ፈጸሙት:: ይህንም መጽሐፍ ጸሐፊዎች በሚጽፉ ጊዜ እጅግ ይደንቁ ነበር ብፁዕ አባ ጊዮርጊስም አይቶ እጅግ ያደንቅ ነበር ልቡም እጅግ ደስ ተሰኘ:: ይህን መጽሐፍ መንፈስ ቅዱስ በኔ አንደበት ተናገረው እንጂ እኔ አልተናገርኩትም አለ:: ይህን መልካም ነገር ሁሉ የገለጽክልኝ እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ አመሰግንሃለሁ አለ:: ይህንም መጽሐፍ መጽሐፈ መሥጢር በማለት ጠራው መጽሐፉ የመለኮትን መሥጢር ይናገራልና::

መጽሐፉ በይዘቱ በአጠቃላይ ከቀድሞ ጀምሮ በእውነተኛዋ የሐዋርያት እምነት ላይ ለተነሱ መናፍቃን ለትምህርታቸው መልስ ለመስጠትና ምእመናንን በሃይማኖትና በምግባር ለማጽናት የተጻፈ ነው:: በመጀመሪያ መግቢያው ላይ እንደተጻፈ መጽሐፉ ለሚያምኑ (ለምእመናን) እንጅ ለማያምኑት አልተጻፈም ይላል:: በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን እንደ ተዋሕዶ ሃይማኖት ምስክር አድርገን የምንጠቀምበት «ሃይማኖተ አበው» ከዓረብኛ የተተረጐመበት ጊዜ በመቅድሙ ላይ እንደተገለጸው በዓፄ እስክንድር ዘመነ መንግሥት (፲፬፻፸፰-፲፬፻፺፬/ም) ነው::አንዳንድ ሊቃውንት በበኩላቸው በዓፄ ገላውዴዎስ ዘመን (፲፭፻፴፩-፲፭፻፶፩ ዓ/ም) ነው ይላሉ:: ተርጓሚው የራስ ዓምዱ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ስሙ መብዓ ጽዮን ወይም ዓሥራተ ጽዮን ነው ተብሎ ይገመታል:: ይኸ ከመጽሐፈ ምስጢር ከተጻፈበት ከ፲፱፻፺፬/ም ጋር ሲነጻጸር ከግማሽ ምእት ዓመት በላይ ልዩነት መኖሩን ያሳያል:: በመሆኑም መጽሐፉ በተጻፈበት ጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ ከፍተኛ የሃይማኖት ምስክር ተደርጎ መወሰዱን ምሁራን ይናገራሉ:: በውስጡም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክንም ያካትታል፣ እጅግ ጥልቅ የሆነ ምሥጢረ ሃይማኖት፣ ስፊ የሥነ ምግባር ትምህርት «የመብራት ፈትል ያለ ዘይት በጾምና በጸሎት መትጋትስ ያለ የዋህነት ቤተክርስቲያንንም መከተል ለድሆች ያለመራራት ድንግልናም ያለ ትሕትና ምን ይጠቅማል:: ገጽ/፻፺፩» በማለት ያስተምራል:: ክርስቲያን የመሆን ምስጢር ገጽ/፺፣ የመናፍቃንኑ ትምህትና መልስ ከታሪካዊ መነሻቸው ጋር አብራርቶ ይተርካል ረቂቅና እጅግ ከፍተኛ አመክናታዊ (logic) ሥርዓት ባለው ወጥ በሆነ የመልስ አቀራረብ መልስ ይሰጣል:: ሲጨርስ መናፍቃኑን ከትምህርታቸው ክፋት አንጻር በልዩ ልዩ መንገድ መስሎ ያቀርባል:: ዮሐንስ መጥምቅ ክፉዎችን «የእፉኝት ልጆች» (ማቴ፫፥፯) እንዳለ:: ጌታም «የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ»(ማቴ ፯፥፮) እንዳለ መጽሐፈ ምስጢርም «የዝንጉዎች የሃይማኖታቸው መታሰቢያ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው:»(ገጽ/፹) «አርዮስ የሰይጣን ሠረገላው የአጋንንትም ማኅበረተኛቸው ነው:: በሽንጋይ ልቡ የሚሸነግል የሰይጣንን አሠር የሚከተል የውሾችን መንጋ ጠባቂ በገሊላዊ ኢየሱስ አምላክነት ላይ ስድብን የተናገረ የከሀዲው የአርዮስ ተግሣጽ ተፈጸመ::» በማለት ያትታል:: እንዚህ ዘለፋዎች መናፍቃኑ ወይም ክፉዎች መምህራን በክርስቲያኖች አንድነት ላይ፣ በእውነተኛው የአምልኮት ትምህርት ውስጥ መከፋፈልንና ረብሻን ለመፍጠራቸው፣ ምእመናንን ለማወካቸው፣ በአንዲቱ ቅድስት ማኅበር ውስጥ የራሳቸው ቡድንና የቡድን መሪያ በማውጣት ለሚሠሩት ተንኮል ምሳሌ ለመስጠት የሥራቸውን ክፉ መዓዛ ለማጋለጥ ነው:: ከዚሁም በማያያዝ ለወደፊቱ የእነርሱን አሠር በመከተል በቅድስት እናት ቤተ ክርስቲያን ላይ የቡድንና የሥጋ ዝሀ (ንግድ) ለሚፈጽሙ፣ በኑፋቄ መርዝ ለሚበርዙ፣ የክርስቶስን በጎች ለሚያደናብሩ ርጉማንም፣ ግዘቱም፣ ዘለፋውም እንደሚተላለፍ ያስረዳል::

በመጽሐፈ ምሥጢር መልስ የተሰጣቸው መናፍቃን በጥንት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚታወቁ፣ ከዘመነ ሊቃውንት በኋላ የተነሱ እስላሞች (መሐመዳውያን) እና በሀገራችን የተነሱ እንደ ቢቱ ላሉ መናፍቃን ነው:: የዘመነ ሊቃውንት መናፍቃንን ትምህርት ከግሪክ መጻም ከዐረብኛ ከተተረጎሙ ወይም በራሳቸው ቋንቋ ከተጻፉ መረጃዎች በመነሳት መልስ የሰጡ ሲሆን፤ የእስላሞችን ትምህርት በሚገባ የተረዱት ይመስላል፤«እስላሞችም እግዚአብሔር አልወለደም አልተወለደምም ይላሉ፡ የእግዚአብሔርንም ልጅ በገብርኤል ቃል ከማርያም ተፀነሰ ይሉታል የእግዚአብሔር ንግግር ይሉታል የእግዚአብሔር ልጅ ግን አይሉትም የእግዚአብሔርን መምጣት ግን አይክዱም የአይሁድና የእስላሞች ክህደት ስለኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም በማለት ነው፡ እኛ ግን ክርስቲያን ነን እግዚአብሔር ከልጁና ከቅዱስ መንፈሱ ጋር እንደሚመጣ እናምናለን::» እንደ ቢቱ ያሉት የሀገር ውስጥ መናፍቃን ግን ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ራሳቸው በዘመን ደርሰው የተከራከሯቸው ናቸው::

በ· መሠ እሱጣፕ ሐደት ዋና ምስክር የሚያደርጉት ቅዱሳት መጻሕፍትን (ብሉይና ሐዲስ ኪዳንን) ነው:: በዚህም ሊቁ ለባታችን ጊዮርገስ ጥልቅ የሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት እንደነበራቸው መረዳት ይቻላል:: ከሁሉ በበለጠ

እነዚህን ሁለት ኪዳናት የቤተ ክርስቲያን እናታችን ሁለት ጡቶች ብለው ይጠሯቸዋል:: «ቤተክርስቲያን ከአራትና ከወንጌላት ሌላ ጡቶች ከነቢያትና ከሐዋርያትም በቀር መምህራን የሉአ ትምና::»ገጽ/፪፻፫፮ ከዚህ በተጨማሪ በጣም አልፎ አልፎ ከሲኖዶስ ገጽ/፪፻ ከዲድስቅልያና ትምህርተ ሐዋርያት (ገጽ/፪፻፶) እንደ አስፈላጊነቱ ተጠቅሷል:: አንድ ቦታ ላይ ብቻ ደግሞ የአባ ሰትዱንን ገድል (ገጽ/፪፻፲፩) እና ከጎርጎርዮስ ራእይ (ገጽ/፪፻፲) ለምክርነት ሳይሆን ለምሳሌ ጠቅሷል:: በአጠቃላይ በሁሉም ትምህቶቹ ቅዱሱ ሊቅ የምስራቅ (ኦሬንታል) ኦርቶዶክስ ትምህትና ውሳኔን በሚገባ ያስተሳሰቀ ራሳቸውንም «የምሥራቃውያን ከዋክብት የትምህርታቸው ልጅ የሆንሁ:: የሚሉ (ገጽ/፪፻፶፱)» የኢትዮጵያን ሊቃውንት ትምህርት የሚወክሉ ናቸው::

በመጽሐፈ ምሥጢር በእያንዳንዱ ክፍል ጸሐፊው ራሳቸው እንደሆኑ ስማቸውን ሲገልጹ በሁለት ቦታዎች ብቻ «ርቱዐ ሃይማኖት» የሚለውን ስያሜ ተጠቅመዋል:: ይኸውም ሌላ ሰው ጸፈው ሳይሆን ስትህትና ነው:: የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከቀድሞ ጀምር በተለይ የምግባርን ነገር ሲጽፉ ስማቸውን ሳይጽፉ «ርቱዐ ሃይማት» በሚለው ስም የመጻፍ ልምድ አላቸው:: ሊቁም በእነዚህ ክፍሎች ስምእመናንና ስካህናት የምግባር ምክር ያስተላለፉበት ስለሆነ ውዳሴ ከንቱ እንዳይሆንባቸው ስማቸውን አልጻፉም:: ክርስቲያን በሃይማኖቱ ፋጹም ነኝ ይላል እንጅ ምግባሬ ፍጹም ነው ብሉ ራሱን ከፍ አድርጎ ምስክር አድርጎ አይጽፍምና::

እኛም በአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ገዳም የምንገኝ ማኅበረ መነኮሳት ቀደምት አባቶቻችን በብዙ ተጋድሉ ጠብቀው ያቆዩትን መጻሕፍት በሃያኛው ክፍለ ዘመን በመጣው ሥልጣኔ ሰዎች የሀገራችንን ዕውቀትና የአባቶቻችንን ቅርስ በካሜራ ቀርጸው ወደ ተለያዩ ቦታዎች በመውሰድና በማስራጨት ሥርዓትና ትውፊቱን ባልጠበቀ መልኩ ስግላቸው እንዳይጠቀሙበት በማሰብ ሊቃውንትና ምእምናን ግእዙን ከአማርኛው እያገናዘቡ እንዲጠቀሙበት የዓመቱን ምንባብ ሳንቆራርጥና ሳንጨምር ታሪኩንና ይዘቱን እንደጠበቀ በጥንቃቄ አቅርበናል::

### በመጽሐፈ ምስጢር መልስ የተሰጣቸው መናፍቃን

መጽሐፈ ምሥጢር በመጀመሪያ ክፍሉ መልስ ስለ ተሰጣቸው መናፍቃን አጭር መግቢያ ይጽፋል:: መናፍቃኑ በተነሱበት የዘመን ሒደትም ተራቸውን ጠብቀው አስፈላጊውን መልስ ሰጥተዋቸዋል:: ይኸውም በተለይ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደቀ መዛሙርት አስፈላጊ ስለሆነ በውጭ ከሚታወቁበት ስያሜአቸው ጋር አቅርበነዋል::

ትምህርት ተቋማት ደቀ መዛሙርት አስፈላጊ ስለሆነ በውጭ ከሚታወቁበት ስያሜአቸው ጋር አቅርበነዋል::
ሰባልዮስ (Saballius) አብና ወልድ መንፈስቅዱስም አንድ ገጽ ናቸው ያለ መናፍቅ ነው በዘመናዊው የነገረ መለኮት
ጥናት (Trinitarian heresy) ሲባል ትምህርቱ (Monricianism/Modalism) ይባላል:: የኖረው (በ220 ዓ/ም) አካባቢ ነው::
አቡናርዮስ (Apollinarius) (310-390 ዓ/ም) አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስም ለየራሳቸው ናቸው ያለ መናፍቅ፤ መጀመሪያ
ጸረ አርዮሳዊ ነበር ከዚያም የሎዶቅያ ጳጳስ ተደረገ:: በኋላ በኑፋቄው በጉባኤ ተወግዞአል::
አርዮስ(Arius) ክርስቶስ ፍጡር ነው አለ:: እርሱም በ325 ዓ/ም በኒቅያ በ318 ሊቃውት ተወገዘ::
ንስጥሮስ (Nestorius) (351-451ዓ/ም) ወልድ ከነቢያት እንደ አንዱ ነው የእግዚአብሔር ልጅ በዮርዳኖስ ባደረበት ጊዜ
በጸጋ አምላክ ሆነ ያለ መናፍቅ ነው:: እርሱም የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሆኖ የሁለት ባህርይ ትምህርት አስፋፋ
በመጨረሻ በሰኔ 22 ቀን 431 ዓ/ም በተደረገው የኤፌሶን ጉባኤ ተወገዘ::
ፎጢኖስ (Photinus) የወልድ ህልውና ከማርያም ከተወለደ ወዲህ ነው፤ ከጥንት አይደለም አለ:: የስሚርና ጳጳስ ነበር
ከተረፈ ሰባልዮስ አንዱ ነው:: በዐራተኛው ክፍለ ዘመን የተነሳ ሲሆን በ344 ዓ/ም አካባቢ ተወግዞ ተለየ::
አርጌንስ (Origen) 185-254ዓ/ም የኖረ የግብጽ ተወላጅ ነው:: እርሱም ወልድ ከአብ ያንሣል አይተካከለውም
መንፈስቅዱስም ከወልድ ያንሳል እርሱንም ማየት አይቻለውም... አለ:: አብ ፍጹም አምላክ(θέος) ወልድ ንዑስ አምላክ
(όυτο θέος) ነው በማለት:: ጸሎት ሁሉ ለአብ ይደርሳል የሚል ትምህርት አስተማረ:: እርሱም በኋላ ተወገዘ::
ፈሪሳውያን ጌታችንንም ባለመድኃኒት ሆይ ራስህን አድን አሉት::ሁለተኛም በአጋንንት አለቃ አጋን ንትን ያወጣቸዋል
አሉት:: ትንሣኤ ሙታን የለም የጻድቃን ደስታ የኃጥአንም መከራ የለም ያሉ ሰዱቃውያንንም መልስ ይሰጣል::
በወንጌል መምጣት አሪት እንደ ቀረች በሐዋርያትም ስብከት የነቢያት ትንቢት እንደ ጠፋ ሰንበትም ትንሣኤ በሆነባት
በእሑድ እንደተሻረች ብለው ለሚናገሩም መልስ ይሠጣል::
ቤቱ ኢትዮጵያዊ እና በቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘመን የነበረ መናፍቅ ነው::(Eschatological Heresy) ለኃጥአን ፍዳን
ለመክፈል ለጻድቃንም በጎ ዋጋ ለመስጠት ወልድ ከአባቱ ተለይቶ ብቻውን ይመጣል ስላለ ለርሱም መልስ ይሰጣል::
ፀረ ማርያም የሆኑ አንጢዲቆማርያሞስም (Antidicomarianites) የኖሩት በ428ዓ/ም አካባቢ ነው:: ድንግል ማርያም
መድኃኒታችንን ከወለደችው በኋላ ከዮሴፍ ጋር ተገናኝታለች ይላሉ:: በአንድ ወቅት የተነሱ ሳይሆኑ ክርስቶስን የዮሴፍ
ልጅ ካሉ ከፈሪሳውያን ጀምሮ ያስተማሩ መናፍቃንን ነው:: ቅዱስ ቄርሎስ ከምስራቅ ሊቃውንት አውግስታይን የሚባል
የምዕራቦች አስተማሪም ከተቃወሟቸው በኋላ ጠፍተው ነበር:: ትምህቱን በ16ኛው ክፍለ ዘመን ሉተር ተጠቅሞታል::
የእግዚአብሔር ልጅ ያለ ፈቃዱ በግድ ሞተ የሚሉ የሕንድ ጳጳስ ሳዊሮስ የእለእስክንድርያውም ቴዎዶስዮስ ናቸው::
አቡርዮስ (Apollinarius) በድጋሚ መልስ ይሰጠዋል ሁለተኛው የሚመለከተው የክርስቶስ ሰውነት ልብና ነፍስ
የለውም መለኮቱም ስለልብና ነፍስ ፋንታ ሆነው ብሉ ላስተማረው (Adoptionist) ትምህርት ነው::
አፍትኪስ (Eutychius) የክርስቶስ ሥጋ ከሰማይ ወረደ አለ:: ተዋሕዶን ለማስተማር የተሳሳተ መንገድ የተከተለ ነው::
መንክዮስ (Manichaeus) ወይም (Mani/Manes) (216-270 )የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ነው የሰው ልጅም ሥጋ አይደለም
አለ:: እነዚህ ከጥንት የዕውቀት አምላኪዎች ግኖስቲክስ (Gnostics) ውስጥ ሲሆን ትምህርቱ በኋ ዘመን ጠፍቷል::
አርሲስ የሚለው ስያሜ በላቲን (Heresy) ሑረሲ ሲሆን መናፍቅ ማለት ነው::በነፍስና በሥጋ ወደ ሲኦል ወረደ
ይላሉ::
የሮሜ ሊቀጳጳሳት ልዮን (Le'o) ሥጋ ከመለኮት ያንሣል አለ:: ይህ ሰው ለቤተ ክርስቲያን መከፈል ምክንያት ነው::
የሮም ካቶሊክም በኋላ ጊዜ ለካቶሊካውያን አመለካከት መሥራች አድርገውታል::
የኬልቄዶን ማኅበርተኞች (Chalcedonian) ይኸ ስያሜ የሚያመለከተው በጥቅምት 8 ቀን 451 ዓ/ም በኬልቄዶን
የተሰበሰቡ መለኮትና ሥጋ በሁለት መንገድ በሁለት ሥርዓት ናቸው ብለው በአንድ ሰው ደብዳቤ የሃይማኖትን
ምስጢር የለወጡ ከ500-600 የሚደርሱ ጳጳሳት ናቸው እነርሱም ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ተከፈሉ::
ፍልብያኖስ (Flabianos) (በ 449 ዓ/ም አርፏል) የመድኃኒታችን የክርስቶስ መለኮቱና ትስብእቱ ሁለት ገጽ ያለ ነው::
መቅዶንዮስ(Macedonius) (በ362 ዓ/ምአርፏል)መንፈስቅዱስ ፍጡር ነው ያለ ሲሆን ትምህርቱ በ381ዓ/ም በቁስጥንጥንያ
ተወግዟል::

# የአርዕስት ማውጫ


ምዕራፍ አንድ የጌና ስብከት ምንባብ
ስለ መጽሐፉ መግቢያና የስባልዮስ ተግሣጽ ---------- ፩
ምዕራፍ ሁለት የብርሃናት ምንባብ
የአቡርዮስ ተግሣጽ ---------- ፲፮
ምዕራፍ ሦስት የኖላዊ ምንባብ
የአርዮስን ተግሣጽ ---------- ፳፱
ምዕራፍ አራት የጌና ምንባብ
የንስጥሮስ ተግሣጽ ---------- ፴፯
ምዕራፍ አምስት የልደት ምንባብ
የፎጢኖስ ተግሣጽ ---------- ፶፩
ምዕራፍ ስድስት የጥምቀት ምንባብ
የአርጌንስ ተግሣጽ ---------- ፷፩
ምዕራፍ ሰባት በቃና ዘገሊላ ምንባብ
የመለኮት ቃል ሰው ወደ መሆን ተለወጠ ለሚሉ ተግሣጽ። ---------- ፷፯
ምዕራፍ ስምንት የጥምቀት ሦስተኛ ቀን ምንባብ
የመንፈስቅዱስ መገለጥ ከክርስቶስ ጥምቀት ወዲህ ነው ለሚሉ ተግሣጽ ---------- ፸፩
ምዕራፍ ዘጠኝ የስምዖን ምንባብ
ስለ እመቤታችን ስለ ስምዖን ነቢይ ---------- ፸፮
ምዕራፍ ዐሥር/ የደብረ ዘይት ምንባብ
ወልድ ያለ አብ ይመጣል ያለ የቢቱ ዘለፋ ---------- ፺
ምዕራፍ ዐሥራ አንድ የትስብእት ምንባብ
የአንጢዲቆማርያጦስ (ጸረ ማርያም) ተግሣጽ ---------- ፻፭
ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት የሆሣዕና ምንባብ
ድርሳን ዘርቱዐ ሃይማኖት ---------- ፻፱
ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት የጸሎተ ሐሙስ ምንባብ/ በጸሎተ ኀሙስ ምንባብ
ድርሳን ዘርቱዐ ሃይማኖት ---------- ፻፳
ምዕራፍ ዐሥራ አራት በዓርብ ስቅለት የነግህ ምንባብ
የአውጣኪ ተግሣጽ ---------- ፻፳፯
ምዕራፍ ዐሥራ አምስት የዓርብ ስቀለት የሦስት ሰዓት ምንባብ
የሀንዱን ጳጳስ የሳዊሮስንና የእለ እስክንድርያውን የታውዶስዮስ ተግሣጽ ---------- ፻፴፱
ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት የዓርብ ስቅለት የስድስት ሰዓት ምንባብ
የአቡርዮስ ተግሣጽ ---------- ፻፶፩
ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት የዓርብ ስቅለት የዘጠኝ ሰዓት ምንባብ
የአፍቲኪስ ተግሣጽ ---------- ፻፷
ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት የዓርብ ስቅለት የሰርክ ምንባብ
የመንክዮስ ተግሣጽ ---------- ፻፷፱
ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ የዓርብ ስቅለት የመኝታ ጊዜ ምንባብ
አርሲስ የተባሉ የመናፍቃን ዘለፋ ---------- ፻፸፩
ምዕራፈ ሃያ የፋሲካ ምንባብ
የቁስጥንጥንያ ሊቀጳጳሳት የልዮን ተግሣጽ ---------- ፻፹፩
ምዕራፍ ሃያ አንድ የፋሲካ ሰኞ ምንባብ
የኪልቄዶንን ማኅበረተኞች ተግሣጽ ---------- ፪፻፳፪
ምዕራፍ ሃያ ሁለት የፋሲካ ማክሰኞ ምንባብ
አርእያውን ወደ መስቀል ግንድ አወጣ የተቸነከረው እርሱ አይደለም የሚሉ ሰዎች ተግሣጽ ---------- ፪፻፳፭
ምዕራፍ ሃያ ሦስት የፋሲካ ረቡዕ ምንባብ
ሲሕፃን ከአባቱና ከእናቱ የሚሰጠውን የሕይወት እስትንፋስ መቀበልን የካዱ ሰዎች ተግሣጽ ---------- ፪፻፴፯
ምዕራፍ ሃያ ዐራት የፋሲካ ኀሙስ ምንባብ
ለአርጌንስ ---------- ፪፻፶፩
ምዕራፍ ሃያ አምስት የፋሲካ ዓርብ ምንባብ
ኀበስቱም ወደ ክርስቶስ ሥጋነት፤ የወይኑ ጽዋም ደሙን ወደ መሆን አይለወጥም የሚሉ ሰዎች ተግሣጽ ---------- ፪፻፷፯
ምዕራፍ ሃያ ስድስት የቀዳሚት ሰንበት ምንባብ ---------- ፪፻፸፩
ከመጽሐፈ ኩፋሌ ---------- ፪፻፸፱
የጴጥሮስና የጳውሎስ ትእዛዝ ---------- ፪፻፹፩
ትእዛዝ ---------- ፪፻፺፫
ምዕራፍ ሃያሰባት በአግብኦተ ግብር የሚነበብ ---------- ፫፻፱
ምዕራፍ ሃያ ስምንት የዕርገት ምንባብ ---------- ፫፻፳፯
ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ የበዓለ ኀምሳ ምንባብ ---------- ፫፻፴፬
ምዕራፍ ሠላሳ የደብረታቦር ምንባብ ---------- ፫፻፵፰

# ምዕራፍ ፩

## በስብከተ ጌና ምንባብ

፩ በስመ እግዚአብሔር ሥሉስ ዘኢይትሌለይ፡ ኅቡዕ ዘኢይትረአይ ፡ ምሉዕ ዘኢይትነከይ፡ ጕንደ ሃይማኖት ዘኢይትወቀይ። መዝገበ በረከት ውስተ ልበ መሀይምናን ዘይትወደይ፡ ዘአሐደ ይሰገድ ወአሐደ ይሴባሕ ወአሐደ ይጼለይ፡ ሎቱ ስብሐት በምድር ወበሰማይ በባሕር ወበቀላይ ለዓለመ ዓለም። አሜን። ዮሐ፲፬፥፳፫

፪ መጽሐፈ ምሥጢር ዘይትነገር ለመሀይምናን ወአኮ ለኢመሀይምናን፡ እስመ ኢአደሞሙ ለዳታን ወአቤሮን ምስፍናሁ ለሙሴ እስከ አብቀወት ምድር ወውሕጠቶሙ ወኢኮነ ሠናየ ቅድመ አዕይንቲሆሙ ለደቂቀ ቆሬ እስከ ወጽአት እሳት እማዓጥኒሆሙ ወበልዐቶሙ። ዘኍ፲፮፥፩-፶

፫ ተግሣጸ ኤልያስ ነቢይ ኮኖሙ ሰቆራረ ለአክአብ ወለኤልዛቤል እስከ በልዑ ከለባት አበድንቲሆሙ ወተሐጽባ ዘማት በደሞሙ። ትንቢተ ሚክያስ አሕመመ ልቦ ካዕበ እስመ ተአመነ በትንቢተ ሴዴቅያስ እስከ ቀስለ በሐጸ ሶርያ ወሞተ። ፩ነገ፳፥፲፱፤፳፪፥፴፯ ፪ነገ፱፥፴-፴፯

፬ ወለእግዚእነሂ ይቤልዎ አ ዐቃቤ ሥራይ ፈውስ ርእሰከ። ካዕበ ይቤልዎ በመልአከሙ ለአጋንንት ያወጽኦሙ ለአጋንንት። ወዓዲ ይቤልዎ በመባ ሕተ መኑ ትገብር ዘንተ ከመዝ ወአብጽሕዎ እስከ ለሞት ወመጠውዎ ለቅንዋተ መስቀል። ፩ነገ ፳፪፥፲፫-፴፭ ማቴ፳፯፥፵፪ ፤፲፪፥፳፬፤ ፳፩፥፳፫ ፤፳፯፥፳፯

፭ ወለጴጥሮስኒ ተቃወመ ትምህርቶ ሲሞን መሠርይ ዘሰማርያ ወዐርገ ውስተ አየራት በኃይለ አጋንንት መስሕታን፡ ወወድቀ እም ውስተ ምጽንዓት በኃይለ መንፈስቅዱስ ዘኀዳር ላዕለ ጴጥሮስ። ሐዋ፰፥፲፰-፳፬

፮ ወለጳውሎስኒ ይቤልዎ ምንተ ይብል ዝ ዘራኤ ነቢብ።ለሊሁኒ ይቤ ለአይሁድኒ ይመስሎሙ ዘነአብድ ወለአረሚኒ ዘንጌጊ፡ ወለነሰ ለእለ አመነ ኃይለ እግዚአብሔር ውእቱ። ሐዋ፲፯፥፲፰ ፩ቆሮ፩፥፳፬

፯ እስመ ሰብእሰ ያበድር ጽልመተ እምነ ብርሃን፡ እስመ ይትከሠት ኃጣውኢሆሙ በከመ

# ምዕራፍ አንድ

## የጌና ስብከት ምንባብ

፩ የማይለይ ሦስት የማይታይ የተሠወረ ሙሉ የማይጎድል፣ የማይቆረጥ የሃይማኖት ግንድ፣ በምእመናን ልቡና አድሮ የሚኖር የበረከት መዝገብ፣ በአንድነት የሚሰገድለት በአንድነትም የሚመሰገን በሆነ ወደርሱ የሚጸለየውንም በሚሰማ በእግዚአብሔር ስም፣ በምድርና በሰማይ በባሕርና በቀላይ ለርሱ ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን። ዮሐ፲፬፥፳፫

፪ ለምእመናን የሚነገር የምሥጢር መጽሐፍ፡ ላላመኑትም አይደለም፡ ምድር ተከፍታ እስከትውጣቸው ድረስ የሙሴ መስፍንነቱ ዳታንና አቤሮንን ደስ አላሰኛቸውምና ከማዕጠንቶቻቸውም እሳት ወጥታ እስክትበላቸው ድረስ በቆሬ ልጆች ዓይን ፊት የተወደደ አልሆነም። ዘኍ፲፮፥፩-፶

፫ ውሾች በድኖቻቸውን እስኪበሉ አመንዝሮችም በደማቸው እስኪታጠቡ ድረስ የነቢዩ የኤልያስ ተግሣጽ ለአክዓብና ለኤልዛቤል የሚያስጸይፍ ሆነባቸው፡ የሚክያስም ትንቢት ዳግመኛ ልቡን አሳዘነው በሶርያ ፍላፃ ቆስሉ እስኪሞት ድረስ በሴዴቅያስ ትንቢት ታምኗልና። ፩ነገ፳፥፲፱፤፳፪፥፴፯ ፪ነገ፱፥፴-፴፯

፬ ጌታችንንም ባለመድኃኒት ሆይ ራስህን አድን አሉት።ሁለተኛም በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣቸዋል አሉት።ዳግመኛም ይህንን እንደዚህ በማን ሥልጣን ታደርጋለህ አሉት እስከ ሞትም አደረሱት ለመስቀል ችንካርም አሳልፈው ሰጡት። ፩ነገ፳፪፥፲፫-፴፭ ማቴ፳፯፥፵፪፤ ፲፪፥፳፬ ፤፳፩፥፳፫ ፤፳፯፥፳፯

፭ የጴጥሮስንም ትምህርቱን ተቃውሞ የሰማርያ መድኃኒተኛ በአሳቾች አጋንንት ኃይል ወደ አየር ወጣ በጴጥሮስ ላይ ባደረ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ግን ከጠፈረ ሰማይ ወደቀ። ሐዋ፰፥፲፰-፳፬

፮ ጳውሎስንም ይህ ለፍላፊ ምን ይላል አሉት።እርሱም ራሱ ለአይሁድ የምንስት ለአሕዛብም የምንበድል ይመስላቸዋል፤ ለእኛ ላመንን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው አለ። ሐዋ፲፯፥፲፰ ፩ቆሮ፩፥፳፬

፯ ሰውስ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ይመርጣል ኃጢአታቸው ይገለጣልና ጌታችን

ይቤ እግዚእነ እስመ ኵሉ ዘእኩይ ምግባሩ ይጸልዕ ብርሃነ። ንሕነሰ ንሰብክ ሥሉሰ ዘኢይቶሳሕ ጽሙረ ዘኢይትሌለይ። ዮሐ፫፥፲፱-፳

፰ በከመ አብ ብርሃን ወልድኒ ብርሃን ዘያበርህ ለኵሉ ዓለም።በከመ ወልድ ብርሃን መንፈስ ቅዱስሂ ዘበ፩ ሱራሄ ወጸዳል። ዮሐ፰፥፲፪

፱ በከመ አብ እሳት ዘኢይትገሰስ ወልድኒ እሳት ዘኢይትለከፍ። በከመ ወልድ እሳት ዘኢይትለከፍ መንፈስቅዱስሂ እሳት ዘበላህበ ሃይማኖቱ አርሰና ለቤተክርስቲያን። በከመ አብ ኃይል ዘኢያስተርኢ ወልድኒ ኃይል ዘኢይትከሠት ዘእንበለ ዳዕሙ በሥጋዌሁ።ወበከመ ወልድ ኃይል ዘኢይትከሠት መንፈስቅዱስሂ ኃይል ዘይጸውራ ለቤተ ክርስቲያን ከመ ኢትትገፈታእ እምትንሣኤ ዕልዋን። ዕብ፲፪፥፳፱

፲ በከመ አብ አምላክ ፍጹም ወልድሂ አምላክ ፍጹም።በከመ ወልድ አምላክ ፍጹም መንፈስቅዱስሂ አምላክ ፍጹም ዘበአሐዱ ራእይ።

፲፩ ንንግርኬ ዘለፋሆሙ ለረሲዓን፡ ሰብልያኖስ ይቤ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ፩ ገጽ። ንሕነሰ ንብል ፫ ገጽ ወ፩ ራእይ ፫ አካል ወ፩ አምላክ፣፫ አስማት ወ፩ እግዚአብሔር።

፲፪ አቡርዮስ ይቤ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ዘዘዚአሁ።ንሕነሰ ንብል አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ፩ አምላክ ወ፩ ራእይ ወአሐቲ መንግሥት ወአሐቲ ሥምረት። አርዮስ ይቤ ፍጡር ውእቱ ክርስቶስ። ንሕነሰ ንብል ኢፍጡር ወኢግቡር ኢንቱግ ወኢብዑድ እምሀላዌ አቡሁ።

፲፫ ንስጥሮስ ይቤ ወልድ ከመ ፩ እምነቢያት ወሶበ ተራከበ ወልደ እግዚአብሔር በወስተ ዮርዳኖስ ኮነ አምላክ በጸጋ። ንሕነሰ ንብል አምላክ ውእቱ እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ።

፲፬ ፎጢኖስ ይቤ ለፌ እማርያም ሀላዌሁ ለወልደ እግዚአብሔር ወአኮ እምትካት። ንሕነሰ ንብል ሀላዌሁ ውእቱ እምቅድመ አዝማን ወመዋዕል እምቅድመ ሰዓት ወዕለት፡ወበደኃሪ መዋዕል ተሠገወ እማርያም ቅድስት ድንግል ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ በእንተ መድኃኒትነ። ገላ፬፥፬

፲፭ አርጌንስ ይቤ የሐጽጽ ወልድ እምአብ ወኢይሬእዮ፡ወየሐጽጽ መንፈስቅዱስ እምወልድ ወኢይክል ነጽሮቶ።ንሕነሰ ንብል አልቦ መዓርግ

በወንጌል ሥራው ክፉ የሆነ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል እንዳለ። እኛ ግን የማይጨመርበትና የማይለይ ሥላሴን እንሰብካለን። ዮሐ፫፥፲፱-፳

፰ አብ ብርሃን እንደሆነ ወልድም ለሰው ሁሉ የሚያበራ ብርሃን ነው። ወልድ ብርሃን እንደሆነ መንፈስቅዱስም ፍጹም በሆነ አንድ ጸዳል ያለ ብርሃን ነው። ዮሐ፰፥፲፪

፱ አብ የማይዳሰስ እሳት እንደሆነ ወልድም የማይያዝ እሳት ነው። ወልድ የማይያዝ እሳት እንደሆነ መንፈስቅዱስም በሃይማኖት ሙቀት ቤተ ክርስቲያንን የሚያሞቃት እሳት ነው። አብ የማይታይ ኃይል እንደሆነ ወልድም ሰው በመሆኑ ካልሆነ በቀር የማይገለጥ ኃይል ነው። ወልድ የማይገለጥ ኃይል እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም ከጥፋት ሰዎች መነሣሣት የተነሣ እንዳትገለባበጥ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠብቃት ኃይል ነው። ዕብ፲፪፥፳፱

፲ አብ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ወልድም ፍጹም አምላክ ነው። ወልድ ፍጹም አምላክ እንደሆነ መንፈስቅዱስም በአንድ ኅብረ መልክእ ያለ ፍጹም አምላክ ነው።

፲፩ የዝንጉዎችን ተግሣጽ እንናገር። ሰብልያኖስ አብና ወልድ መንፈስቅዱስም አንድ ገጽ ናቸው አለ። እኛ ግን ሦስት ገጽ አንድ ኅብረ መልክእ ሦስት አካል አንድ አምላክ ሦስት ስሞች አንድ እግዚአብሔር እንላለን።

፲፪ አቡናርዮስ አብና ወልድ መንፈስቅዱስም ለየራሳቸው ናቸው አለ፣ እኛ ግን አብና ወልድ መንፈስቅዱስም አንድ አምላክ አንድ ኅብረ መልክእ አንዲት መንግሥት አንዲት ፈቃድ ናቸው እንላለን።አርዮስ ክርስቶስ ፍጡር ነው አለ እኛ ግን ፈጽሞ ያልተፈጠረ ከአባቱም አኗኗር የጐደለና የተለየ ያይደለ እንደሆነ እንናገራለን።

፲፫ ንስጥሮስ ወልድ ከነቢያት እንደ አንዱ ነው የእግዚአብሔር ልጅ በዮርዳኖስ ባደረበት ጊዜ በጸጋ አምላክ ሆነ አለ። እኛ ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም በመለኮቱ ከአብ ጋር የተካከለ አምላክ ነው እንላለን።

፲፬ ፎጢኖስ የእግዚአብሔር ልጅ ህልውና ከማርያም ከተወለደ ወዲህ ነው፤ ከጥንትም አይደለም አለ።እኛ ግን ከዘመናትና ከጊዜ ከሰዓትና ከዕለት አስቀድሞ ነበረ በኋላኛው ዘመን እኛን ስለማዳን ያለ ወንድ ዘር ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ እንላለን። ገላ፬፥፬

፲፭ አርጌንስ ወልድ ከአብ ያንሣል አይተካከለውም መንፈስቅዱስም ከወልድ ያንሳል እርሱንም ማየት አይቻለውም አለ።

ውስተ ሥላሴ ኢሑጸጼ ወኢፍድፋዴ አላ ዘውግ በመለኮት ወእጉዛን በጽምረት።

፲፮ ወቦ እለ ይቤሉ ተመይጠ ቃለ መለኮት ለከዊነ ሰብእ።ንሕነሰ ንብል ኢተመይጠ ቃለ መለኮት እምህላዌሁ አላ ተዋሐደ ዘእንበለ ቱሳሔ ወኮነ ጽሙረ ዘእንበለ ሙያጤ።ወቦ እለ ይቤሉ ለፌ እምጥምቀተ ክርስቶስ ኮዋኔሁ ለመንፈስ ቅዱስ።ንሕነሰ ንብል እመቅድመ ዓለም ሀሉ ወይሄሉ እስከ ለዓለም።

፲፯ ቢቱ ይቤ ይመጽእ ወልድ ዘእንበለ አቡሁ ለፍዳ ኃጥአን ወለዕሤተ ጻድቃን። ንሕነሰ ንብል ይመጽኡ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ከመ ይኰንኑ ሕያዋነ ወሙታነ በ፩ ዐውድ ወበአሐቲ ሙቃስ።

፲፰ አንጢዲቆማርያጦስ ይቤሉ ዘውእቶሙ ፀረ ማርያም እምድኅረ ወለድቶ ማርያም ለመድኃኒነ ተደመረት ምስለ ዮሴፍ። ንሕነሰ ንብል ወላዲተ እግዚአብሔር ይእቲ ማርያም እምድኅረ ወለደቶ ነበረት በድንግልና እስከ ለዓለም። አውጣኪ ይቤ ሥጋሁ ለክርስቶስ ኢኮነ ድኩመ ከመ ሥጋነ ወኢሐመ። ንሕነሰ ንብል ሥጋሁ ለክርስቶስ ደከመ ወሐፈወ ርኅበ ወጸምአ ሐመ ወሞተ በሥጋዌሁ ወአልቦ ዘተርፈ እምሕገ ሰብእ ዘእንበለ ኃጣውእ ባሕቲቶን።
ሕዝ፵፬+፪ ማቴ፩+፫ ሉቃ፩+፴፪

፲፱ ሳዊሮስ ጳጳስ ዘሕንድከያ ወታኦዶስዮስ ዘእለስክንድርያ ይቤሉ ሐመ ወልደ እግዚአብሔር በኵርሕ ወሞተ ዘእንበለ ፈቃዱ።ንሕነሰ ንብል ሐመ በፈቃዱ ወሞተ በሥምረቱ ወተንሥአ በኃይለ መለኮቱ። ወካዕበ አቡርዮስ ይቤ አልቦቱ ልብ ወነፍስ ለትስብእተ ክርስቶስ ወመለኮቱ ኮና ሆንተ ነፍስ ወልብ። ንሕንሰ ንብል ቦቱ ነፍሰ ሰብአዊ ወቦቱ ልቡና ጠባይዓዊ ወካዕበ ቦቱ ዕበየ መለኮታዊ ወቦቱ ክሂል እግዚአብሔራዊ።

፳ አፍቲክስ ይቤ ሥጋሁ ለክርስቶስ ወረደ እምሰማይ። ንሕነሰ ንብል ሥጋሁ ለክርስቶስ ወነፍሱ እምጠባይዓ ፍጥረቱ ለአዳም ዘነሥአ ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ ዘእምባሕቲታ ንጽሕት ድንግል ገሊላዊት ማርያም። መንክዮስ ይቤ ምትሐተ ሥጋሁ ለክርስቶስ ወአኮ ሥጋ እጓለ እመሕያው። ንሕነሰ ንብል ፍጹም ትስብእቱ ለክርስቶስ ሥጋ እንተ ትትገሰስ ወአጽም ዘይጸንዕ ለማኀፈደ ሥጋ ደም እንተ ትትከዐው አሥራወ ወአምትንተ መዓሥረ ሥጋዊ ጸጉር ሠርፀ ድማኅ ወሐንገዘ ነፍስ እንተ ኢታስተርኢ ወመንፈስ ሕይወት እንተ ትሌቡ ወትትናገር ወአጽፋር ሠርፀ አጻብዕ ዘአእዳው ወእእጋር።

እኛ ግን በሥላሴ ዘንድ በማዕረግ ማነሥና መብለጥ የለም በመለኮት አንድ ወገን ናቸው እንላለን።

፲፮ የመለኮት ቃል ሰው ወደመሆን ተለ ወጠ የሚሉ አሉ እኛ ግን ያለጭማሪ ተዋሐደ እንጂ መለኮታዊ ቃል ከባሕርዩ አልተለወጠም፡ ያለመለወጥ የተዋሐደ ሆነ እንላለን። የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ከክርስቶስ ጥምቀት ወዲህ ነው፡ የሚሉ አሉ። እኛ ግን ከዓለም አስቀድሞ አለ እስከ ዘላለምም ይኖራል እንላለን።

፲፯ ቢቱ ለኃጥአን ፍዳን ለመክፈል ለጻድቃንም በጎ ዋጋ ለመስጠት ወልድ ከአባቱ ተለይቶ ይመጣል አለ። እኛ ግን አብና ወልድ መንፈስቅዱስም በሕያዋንና በሙታን ሲፈርዱ በአንድ አደባባይ በአንዲትም መወቃቀሻ ቦታ ይመጣሉ እንላለን።

፲፰ ፀረ ማርያም የሆኑ አንጢዲቆማርያ ጦስም ማርያም መድኃኒታችንን ከወለደችው በኋላ ከዮሴፍ ጋር ተገናኝታለች ይላሉ። እኛ ግን ማርያም አምላክን የወለደች ናት ከወለደችውም በኋላ ለዘላለም በድንግልና ኖራለች እንላለን። አውጣኪ የክርስቶስ ሥጋ እንደኛ ሥጋ ደካማ አይደለም መከራንም አልተቀበለም አለ።እኛ ግን የክርስቶስ ሥጋ ደከመ ወዛ ተራበ ተጠማ ታመመ ሰው በመሆኑም ሞተ ከብቻቸው ከኃጢአቶችም በቀር ከሰው ሕግ የቀረው የለም እንላለን። ሕዝ፵፬+፪ ማቴ፩+፫ ሉቃ፩+፴፪

፲፱ የሕንድ ጳጳስ ሳዊሮስ የእለእስክንድርያውም ቴዎዶስዮስ የእግዚአብሔር ልጅ ያለ ፈቃዱ በግድ ሞተ ይላሉ።እኛ ግን በፈቃዱ መከራን ተቀበለ በውዱም ሞተ በመለኮቱም ኃይል ተነሣ እንላለን።ዳግመኛም አቡርዮስ የክርስቶስ ሰውነት ልብና ነፍስ የለውም መለኮቱም ስለልብና ነፍስ ፋንታ ሆነው አለ።እኛ ግን ነፍስ ነባቢት ልቡና ጠባይዓዊ አለው እንላለን። ዳግመኛም መለኮታዊ ጌትነት አምላካዊም ሁሉን ቻይነት አለው።

፳ አፍትኪስ የክርስቶስ ሥጋ ከሰማይ ወረደ አለ። እኛ ግን የክርስቶስ ሥጋና ነፍስ ከአዳም ባሕርይ ብቻዋን ንጽሕት ድንግል ከምትሆን የገሊላ ሴት ማርያም ያለ ወንድ ዘር የነሣው ነው እንላለን። መንክዮስ የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ነው የሰው ልጅም ሥጋ አይደ ለም አለ። እኛ ግን የክርስቶስ ሰውነት ፍጹም የሚዳሰስ ሥጋ የሥጋን አዳራሽ የሚያጸና አጥ ንት በደም ሥሮች ውስጥ የምትፈስ ደም ሰውነ ትን የሚያሥሩ ጅማቶች አናትን የሚሸፍን ጠጉርና ቅንድብ የማትታይ ነፍስ የምታስተው ልና የምትናገር የሕይወት እስትንፋስ የእጆችና የእግሮች ቡቃያ ጥፍሮች አሉት እንላለን።

፳፩ አርሲስ መናፍቃን ይቤሉ ወረደ ውስተ ሲኦል በነፍስ ወሥጋ። ንሕነሰ ንብል ወረደ ውስተ ሲኦል ቃለ መለኮት ምስለ ነፍስ ባሕቲታ ወለሥጋሰ አውረድዋ እምዲበ መስቀል ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ ወጠብለልዋ በልብሰ ገርዜን ወወደይዋ ውስተ ከርሠ መቃብር ይእቲኒ ነበረት ባሕቲታ እንበለ ነፍስ እስከ እመ ትንሣ ኤሁ። ወመለኮቱሰ ምስለ ነፍስኒ ሀለወ እም ሥጋሁኒ ኢተፈልጠ ወበየማነ አብኒ ኮነ ግጽወ በከመ ሀላዌሁ ዘእምቅድም እስመ ይመልእ በኵለሄ ወይሄሉ ውስተ ኵሉ። ዮሐ፲፱፥፴፰-፵፪

፳፪ ልዮን ሊቀ ጳጳሳት ዘሮሜ ይቤ የሐጽጽ ትስብእት እመለኮት። ንሕነሰ ንብል ኢየሐጽጽ ትስብእቱ ለክርስቶስ እመለኮቱ እም ድኅረ ፩ ከዊን። ማኅበረ ኬልቄዶን ይቤሉ መለ ኮት ወትስብእት በክልኤ ፍናው ወበክልኤ ሥርዓት። ንሕነሰ ንብል አምላክ ዘተሰብአ እማርያም ድንግል ፩ አምላክ ወ፩ ሥምረት።

፳፫ ወቦ እለ ይቤሉ አርአያሁ አዕረገ ዲበ ዕፀ መስቀል ወአኮ ውእቱ ዘተቀነወ። ንሕነሰ ንብል ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰቤዛ ብዙኃን ተጸፍዐ እምንብረ ሊቀ ካህናት ወበዐውደ ጲላጦስ ተቀሥፈ ወበሐጻውንት ተቀነወ ወበኵናተ ለንጊኖስ ተረግዘ። ማቴ፳፯፥፳፯ ዮሐ፲፱፥፴፬

፳፬ ወካዕበ ዓዲ ቦ እለ ይቤሉ ከመ ይከውን ንሥአተ መንፈስ ሕይወት ውስተ ሥጋሆሙ ለሕፃናት እምንፍሐተ መንፈሱ ለእግዚአብሔር በከመ ኮነ ላዕለ አዳም። ንሕነሰ ንብል እስመ ፀአተ ነፍስ ወሥጋ እምሐቌ ብእሲ በዘርአ መላ ድ ይትዐቀር ውስተ ማኅፀነ ብእሲት ወእም ኔሃኒ ይከውን ቱሳሔ ጠባይዕ ዘሥምረተ ብእሲ ወብእሲት ዘበትእዛዘ እግዚአብሔር ይከውን ተሰእሎ እመሂ ዘርአ ወእመሂ ዘወለት። ዘፍ፪፥፯

፳፭ ወዓዲ ይቤ አርጌንስ አዕዳል ዘአል በሶሙ እግዚአብሔር ለአዳም ወለሔዋን ሥጋ ውእቱ ዘላዕሌነ እንተ ባቲ ናንሶሱ ንሕነ ወአኮ አዕዳለ አንዳ ዘእምዕስት። ንሕነሰ ንብል በሙ ሥጋ እምቅድም እምእመ ተልሕኩ ወዘአል በሶሙሰ እግዚአብሔር ልብሰ አዕዳል ውእቱ ዘእምዕስት ልብሰ ኀሳ በእንተ ዘአስተሐቀሩ ትእዛዞ። ዘፍ ፫፥፳፩

፳፮ ወቦ እለ ይብሉ እፎ የኀድር ኃይለ መለኮት ዘሰማየ ሰማያት ኢያገምሮ ውስተ ቤተ ክርስቲያን እንተ ተገብረት በእደ እጓለ እመሕ ያው ዘንስቲት ትርብዕተ ገበዋቲሃ። ወካዕበሙ ይቤሉ ይክልኑ ኀብስት ከዊነ ሥጋሁ ለክርስቶስ ወወይን ምሥጢርኒ ከዊነ ደሙ።ንሕነሰ ንብል

፳፩ አርሲስ የተሰኙ መናፍቃን በነፍስና በሥጋ ወደ ሲኦል ወረደ ይላሉ። እኛ ግን መለኮታዊ ቃል ከብቻዋ ከነፍስ ጋር ወደ ሲኦል ወረደ፣ ሥጋን ግን ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ከመስቀል አወረዱት በበፍታም ገንዘው በመቃብር ውስጥ አኖሩት እርሷም እስከ ትንሣኤው ድረስ ብቻዋን ያለነፍስ ቆየች፣ መለኮት ግን ከነፍሱ ጋር ነበረ ከሥጋውም አልተለየም በአብም ቀኝ ከዓለም አስቀድሞ እንደነበረ አኗኗሩ በአካል የተለየ ሆነ በሁሉ ሥፍራ በሁሉ ዘንድ መልቶ ይኖራልና። ዮሐ፲፱፥፴፰-፵፪

፳፪ የሮሜ ሊቀጳጳሳት ልዮን ሥጋ ከመለኮት ያንሣል አለ።እኛ ግን ከአንድነት በኋላ የክርስቶስ ሥጋው ከመለኮቱ አያንሥም እንላለን። የኬልቄዶን ማኅበርተኞች መለኮትና ሥጋ በሁለት መንገድ በሁለት ሥርዓት ናቸው አሉ። እኛ ግን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው የሆነው አምላክ አንድ አካል አንድ ፈቃድ ነው እንላለን።

፳፫ አምሳሉን ወደ መስቀል አወጣ የተቸነከረ እርሱ አይደለም የሚሉ አሉ. እኛ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ለብዙዎች መዳን በሊቀ ካህናት አገልጋይ ፊቱን ተጸፋ። በጲላጦስም አደባባይ ተገረፈ በብረቶችም ተቸነከረ በለንጊኖስም ጦር ተወጋ እንላለን።ማቴ፳፯፥፳፯ ዮሐ፲፱፥፴፬

፳፬ ዳግመኛም በአዳም ላይ እንደሆነው በሕፃናት አካል ውስጥ ከእግዚአብሔር እስት ንፋስ እፍታ የሕይወት እስትንፋስን መቀበል እንደሚደረግ የሚናገሩ አሉ። እኛ ግን የነፍስና የሥጋ መውጣት ከወንድ ጭን በመዋለጃ ዘር ወጥቶ በሴቲቱ ማኅፀን ይፀነሳል ከእርሷም በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚሆን የወንድና የሴት ፈቃድ የጠባይ መቀላቀል ይሆናል ወንድም ቢሆን ሴትም ቢሆን ይሣላል እንላለን። ዘፍ፪፥፯

፳፭ ዳግመኛም አርጌንስ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ያለባሳቸው ቁርበት እኛ የምንመላለስበት በላያችን ያለ ሥጋ ነው የቁር በትም ልብስ አይደለም አለ። እኛ ግን ሥጋስ ቀድሞም በተፈጠሩ ጊዜ አላቸው እግዚአብሔር ያለበሳቸው ግን የቁርበት ልብስ ነው ትእዛዙን ስላቃለሉ የነቀፋ ልብስ ነው እንላለን።ዘፍ ፫፥፳፩

፳፮ ሰማየ ሰማያት የማይወስነው እግዚአ ብሔር አራት ጉኖቿ ባነሡ በሰው ልጆች እጅ በተሠራች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ያድ ራል የሚሉ አሉ።ሁለተኛም ኅብስት የክርስቶስን ሥጋ የምሥጢርም ወይን ደሙን መሆን ይችላልን ይላሉ። እኛ ግን በጽርሐ አርያም ያለ

የጎድር ኃይለ መለኮት ውስተ ቤተክርስቲያን ከመ ይቀድሳ በደሙ እንዘ ኢየዐርቅ ህላዌሁ በጽርሐ አርያም። ወኅብስትኒ ይትመየጥ ለከዊነ ሥጋሁ እምከዊነ ኅብስት ዘልማድ ወወይንኒ ይትመየጥ ለከዊነ ደም እምከዊነ ወይን ዘልማድ ሶበ ይትቄደስ በርደተ መንፈስቅዱስ።

፲፮ ወቦ እለ ይቤሉ ከመ ተፀርዓት አሪት በምጽአተ ወንጌል ወበጠለ ትንቢተ ነቢያት በስብከተ ሐዋርያት ወተሥዕረት ሰንበት በእሑድ ትንሣኤ። ንሕነሰ ንብል ከብረት አሪት በስብከተ ወንጌል ተሰዐሉ ነቢያት በትምህርተ ሐዋርያት ተከለለት ሰንበተ አዕርፎ ዘእምፍጥረተ ዓለም በሰንበተ ትንሣኤ ዘመድኅን ዓለም።

፲፯ ወቦ ካዕበ ዘሮፀ ዜና ውስተ እዘኒነ ከመ ይትከሀዱ በእንተ ማርያም ወመስቀል መንፈቆሙ እንዘ ይብሉ ተዐቢ ማርያም እንተ ወለደቶ እም ዕፀ መስቀሉ ወመንፈቆሙኒ ይቤሉ የዐቢ መስቀሉ ዘተጠምቀ በደመ ሕማማቲሁ። ንሕነሰ ንብል ነአምን በማርያም ከመ ወላዲተ እግዚአብሔር ይእቲ፡ ወነአምን በመስቀሉ ከመ ማዕተበ ብርሃን ውእቱ ዘተቀደሰ በደመ ትስብእተ መለኮቱ። ፍልብያኖስ ይቤ ክልዔ ገጸ መለኮቱ ወትስብእቱ ለመድኃኒነ ክርስቶስ። ንሕነሰ ንብል በ፩ ገጽ ወበ፩ ህላዌ ትስብእቱ ወመለኮቱ ለእምላክነ ።

፲፱ መቅዶንዮስ ይቤ መንፈስቅዱስ ፍጡር ውእቱ :አብሰ ወወልድ ዕሩያን ወኀቡራን ። ወንሕነሰ ንብል መንፈስቅዱስ ኢፍጡር ወኢግቡር ወኢነኪር እምነ አብ ወወልድ አላ አሐዱ ራእይ ወአሐዱ ህላዌ ዘአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ። ሰዱቃውያን ወእለ ከማሆሙ ይቤሉ አልቦ ትንሣኤ ምውታን።ንሕነሰ ንብል ቦ ትንሣኤ ሙታን ወቦ ፍዳ ለኃጥአን ወዕሤት ለጻድቃን። ማቴ፳፪+፳፫ ሉቃ፳+፳፯-፴፱ ሐዋ፳፫+፰

፳ ንገብእኬ ኀበ ጥንተ ነገር ከመ ንዘልፎ ለሰባልዮስ ዘይቤ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ፩ ገጽ። እፎኬ ይትበሀል ፩ ገጽ ህላዌሁ ለሥሉስ ዘበእንቲአሁ ይነገራ መጻሕፍት በበጸታሆን። ቀዳሚ ኩሉ ትብል ቅድስት አሪት ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ። ኢይቤ ባሕቲቱ አብ በአርአያየ ወበአምሳልየ ከመ ዘባሕቲቱ አብ ወኢይቤ በአርአያከ ወበአምሳሊከ ከመ ዘባሕቲቱ ወልድ። ወዓዲ ኢይቤ በአርአያሁ ወበአምሳሊሁ ከመ ዘባሕቲቱ መንፈስቅዱስ አላ ይቤ በአርአያነ ወበአም ሳሊነ ።እእምርኬ ከመ በአርአያ እግዚአብሔር ተሥዕለ እጓለ እመሕያው። ዘፍ፩+፳፮

እናኗኗሩ ሳይጉድል ይቀድሳት ዘንድ የመለኮት ኃይል በቤተ ክርስቲያን ያድራል። ኅብስትም በመንፈስቅዱስ መውረድ በተቀደሰ ጊዜ ከልማዳዊ ኅብስትነት ሥጋውን ወደመሆን ይለወጣል ወይንም ከልማዳዊ ወይንነት ደሙን ወደመሆን ይለወጣል እንላለን።

፲፮ በወንጌል መምጣት አሪት እንደ ቀረች በሐዋርያትም ስብከት የነቢያት ትንቢት እንደ ጠፋ ሰንበትም ትንሣኤ በሆነበት በእሑድ እንደተሻረች የሚናገሩ አሉ።እኛ ግን አሪት በወንጌል ስብከት ከበረች ነቢያትም በሐዋርያት ትምህ ርት ከፍ ከፍ አሉ ዓለምን ከመፍጠር የማረፍ ሰንበትም በዓለም አዳኝ ትንሣኤ ዘውድ ተቀዳ ጀች እንላለን።

፲፰ ዳግመኛም ስለማርያምና ስለ መስቀል እንደሚክዱ በጆሮአችን የገባ ወሬ አለ፤ እኩሌ ቶቹ የወለደችው ማርያም ከመስቀሉ ትበል ጣለች ይላሉ እኩሌቶቹም በሕማማቱ ደም የተነከረ መስቀሉ ይበልጣል ይላሉ። እኛ ግን ማርያም አምላክን የወለደች እንደሆነች እናም ናለን። መስቀሉም መለኮት የተዋሐደው ትስብእት ደም የተቀደሰ የብርሃን ማዕተብ መሆ ኑን እናምናለን። ፍልብያኖስ የመድኃኒታችን የክርስቶስ መለኮቱና ትስብእቱ ሁለት ገጽ ነው አለ።እኛ ግን የእምላካችን የመለኮቱና የትስብእቱ ባሕርይ በአንድ ገጽ በአንድ አካል ያለ ነው እንላለን።

፲፱ መቅዶንዮስ መንፈስቅዱስ ፍጡር ነው አብና ወልድ ግን የተካከሉ አንድ ናቸው አለ። እኛ ግን መንፈስቅዱስ ፈጽሞ ያልተፈጠረ ከአብና ከወልድም ያልተለየ ነው አንድ ኀብረ መልክእ ነው እንጂ የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስም ባሕርይ አንድ ነው እንላለን። ሰዱቃውያንና እንደነርሱ ያሉ ትንሣኤ ሙታን የለም ይላሉ።እኛ ግን ትናሣኤ ሙታንስ አለ ለኃጥአን ፍዳ ለጻድቃንም በጎ ዋጋ አለ እንላለን። ማቴ፳፪+፳፫ ሉቃ፳+፳፯-፴፱ ሐዋ፳፫+፰

፳ አብና ወልድ መንፈስቅዱስም አንድ ገጽ ናቸው ያለ ሰባልዮስን እንወቅሰው ዘንድ ወደቀደመ ነገራችን እንመለስ።መጻሕፍት በየወገ ናቸው ስለርሱ የሚናገሩለት የሥላሴ አካል እንደምን አንድ ገጽ ይባላል። ከሁሉ በፊት የከበ ረች አሪት እግዚአብሔርም አለ ሰውን በአርአያ ችንንና በምሳሌያችን እንፍጠር ትላለች።ለወልድ ለብቻው እንደሚገባ በአርአያዬና በምሳሌዬ አላለም፤ ሁለተኛም ለመንፈስቅዱስ ለብቻው እን ደሚገባ በአርአያውና በምሳሌው አላለም፤ በአርአያችንና በምሳሌያችን አለ እንጂ።የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አርአያ እንደተፈጠረ ዕወቅ። ዘፍ፩+፳፮

፴፩ ወካዕበሙ አእምር ግጻዌሁ ለትሥልስተ መለኮት::ዳዊትኒ ይቤ ገጸ ዚአከ እኅሥሥ እግዚኦ:: ያቀድም ኀበ አብ:: ኀሠሥኩ ገጸከ ያተሉ ኀበ ወልድ:: ወኢትሚጥ ገጸከ እምገብርከ፡ ያሜልስ ኀበ መንፈስቅዱስ፣ ናሁኬ ጽሒቀ ነቢይ ለኀሢሠ ገጸ ሥላሴ:: ወዘሰ ይሜህር ፩ ገጸ ኢጥሙቅ ወኢቅቡዕ ወኢክርስቱን ውእቱ:: መዝ፹፰፥፮

፴፪ ወዓዲ ተብህለ በመዝሙር ዘበሃሌ ሉያ የማነ እግዚአብሔር ገብረት ኃይለ:: ዝኒ በእንተ አብ:: የማነ እግዚአብሔር አልዐለተኒ:: ዝኒ በእንተ ወልድ እስመ ዘበትስብእተ መለኮቱ ለክርስቶስ ኮነ ልዕልናሁ ለእጓለ እመሕያው በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል እስመ ወልደ እግዚአብሔር ወልደ እጓለ እመሕያው ውእቱ:: መዝ፻፲፯፥፲፮

፴፫ ወዓዲመ ይሜልስ ወይቤ የማነ እግዚአብሔር ገብረት ኃይለ:: ዝኒ በእንተ መንፈስቅዱስ:: ኃይልሰ ይተረጐም በጽንዓ መለ ኮተ እግዚአብሔር ዘይሬኢ ወዘኢያስተርኢ ዘይገ ስስ ወዘኢይትገሰስ ዘይቀኒ ወዘኢይትቀነይ:: ናሁኬ ነገርነ ጸታሁ ለሥላሴ:: ወለትምህርተ ሰብልያናስ ሲኦል ጕሥዑቶ ወገሃነም ቈአ ዘእም እስትንፋሰ አፉሁ ለሰይጣን::ወጽአ ወተዘርአ ውስተ ልበ ዕቡሳነ ኀሊና በቀለሂ ወልህቀሂ ወፈረየ ሦከ ኃጢአት:: ወበእንተዝ ሐመት ቤተ ክርስቲያን ምስለ ደቂቃ::

፴፬ አ ሰባልዮስ አርዌ ምድርኑ ሦጠ ሕምዞ ውስተ ልብከ ወሚመ አፍያትኑ፡ እስመ ትብል በአፉከ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ካዕበመ ትብል ፩ ገጽ:: ወእመሰ ፩ ገጽ መኑኬ አብ ወመኑ ወልድ ወመኑ መንፈስቅዱስ:: ወእመሂ ትብል አብኒ ውእቱ ወልድኒ ውእቱ መንፈስቅዱስኒ ውእቱ መኑኬ ፈናዊ ወመኑ ተፈናዊ::ናሁኬ በእንተ ርእሱ ወበ እንተ አቡሁ ይነግር ወልደ እግዚአብሔር እንዘ ይብል እስመ አብ ዘፈነወኒ የዐቢ እምኔሁ:: ወበእንተ መንፈስቅዱስ ይብል ወእፌኑ ለክሙ ካልአ ጰራቅሊጦስሃ:: ናሁኬ ይሰምዮ ካልአ ለመንፈስቅዱስ:: ወካዕበመ ይነግር በእንተ አቡሁ እንዘ ይብል ካልዕ ሰማዕትየ ውእቱ አብ ዘፈነወኒ:: ወበእንተ ርእሱኒ ይነግር እንዘ ይብል ወአልቦ ዘይክል መጺአ ኀበ አብ ዘእንበለ እንተ ኀቤየ:: ዮሐ፲፬፥፲፮ ፥፳፰

፴፭ ወካዕበ ይቤ ተኀደጉኒ ባሕቲትየ ወት ዘረዉ ዘዘዚአክሙ ወኢኮንኩ ባሕቲትየ እስመ አብ ምስሌየ:: ወካዕበ ይቤ ወለዘሰ አፍቀረኒ ያፈቅሮ አቡየ ወንመጽእ ወነኀድር ምስሌሁ ወንገብር ምዕራፈ ኀቤሁ::ናሁኬ ይነግር በእንተ

፴፩ ሁለተኛም የሥላሴን መልክ ዕወቅ ዳዊትም አቤቱ ፊትህን እሻለሁ አለ:: የአብን አስ ቀደመ፣ፊትህን ፈለግሁ ብሎ ወልድን አስከተለ:: ፊትህን ከእኔ ላይ አትመልስ ብሎ ሦስተኛ የመንፈስቅዱስን ተናገረ:: እነሆ ነቢይ የሥላሴን መልክ ለመፈለግ ተጋ፣ አንድ ገጽ ብሎ የሚያስተምር ያልተጠመቀ ያልተቀባ ክርስቲያንም ያልሆነ ነው:: መዝ፹፰፥፮

፴፪ ዳግመኛም በሃሌ ሉያ በሚመጀምረው መዝሙር የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች አለ ይህም ስለአብ ነው:: የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ አለ ይህም ስለወልድ ነው፣ መለኮት በተዋሐደው የክርስቶስ ትስብእት የሰው ልጅ ክብሩ ሆኗልና ጌታ በወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ነውና እንዳለ:: መዝ፻፲፯፥፲፮

፴፫ ዳግመኛም ሦስተኛ መልሶ የእግዚ አብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች አለ፣ይህም ስለ መንፈስቅዱስ ነው ኃይልም ሁሉን በሚያይ እር ሱ ግን በማይታይ በሚዳስስ እርሱ ግን በማይ ዳሰስ በሚገዛ እርሱ ግን በማይገዛ በእግዚ አብሔር መለኮት ጽናት ተተርጉሟል:: እነሆ የሥላሴን ማዕረግ ተናገርን የሰባልዮስን ትምህር ት ግን ሲኦል ገሳችው ገሃነምም ከሰይጣን ከአፉ ተፋው ኀሊናቸው ደካማ በሆነ ሰዎች ልብ ውስጥ ተዘራ በቀለ አደገም የኃጢአት እሾህንም አፈራ:: ስለዚህም ነገር ቤተክርስቲያን ከልጆቿ ጋር መከራን ተቀበለች::

፴፬ ሰባልዮስ ሆይ እባብ በልብህ ውስጥ መርዝ ጨመረን ወይስ እፉኝት:: በአንደበትህ አብና ወልድ መንፈስቅዱስም ትላለህ፣ ሁለተኛ አንድ ገጽ ትላለህ::አንድ ገጽስ ከሆነ አብ ማን ነው ልጁስ ማን ነው መንፈስቅዱስስ ማን ነው፣ አብ ነው ወልድም ነው መንፈስቅዱስም ነው ብትል ላኪ ማን ነው ተላኪስ ማን ነው ፣እነሆ የእግዚአብሔር ልጅ ስለአባቱ የላከኝ አብ ከሁሉ ይበልጣል ብሎ ይናገራል ስለ መንፈስ ቅዱስም ሁለተኛ ጰራቅሊጦስን እልክላችኋላሁ አለ፡ እነሆ መንፈስቅዱስን ሌላው ይለዋል:: ሁለተኛም ምስክሬ ሌላ ነው የላከኝ አብ፣ ሁለተኛም የላከኝ አብ ካልሳበው በቀር ወደ እኔ መምጣት የሚችል የለም፣ ስለራሱም በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደአብ መምጣት የሚችል የለም ብሎ ይናገራል:: ዮሐ፲፬፥፲፮ ፥፳፰

፴፭ ዳግመኛም እኔን ብቻዬን ትታችሁኝ ለየራሳችሁ ትበተናላችሁ ብቻዬን ግን አይደ ለሁም አብ ከእኔ ጋር ነውና አለ::ሁለተኛም የሚወደኝን አባቴ ይወደዋል እኛም እንመጣለን በርሱም እናድራለን በርሱም ማረፊያ እናደርጋ ለን:: እነሆ እንመጣለን በእርሱም እናድራለን

ዘለክልዔ ወአኮ ዘለአሐዱ ሰብ ይብል ንመጽእ ወንገድር ምስሌሁ። ዮሐ፲፬+፳፫፣፲፮+፴፪

፹፮ ወካዕበመ ይነግር በእንተ መንፈስ ቅዱስኒ ወይቤ አነ እስእሉ ለአብ ይፈኑ ለክሙ ጰራቅሊጦስሃ መንፈሰ ጽድቅ ዘኢይክል ዓለም ንሢአቶ። ናሁ ያኤምር በዝ ጸታ ሥላሴ።ወልድ ሰአሉ ለአቡሁ ከመ ይፈንዎ ለጰራቅሊጦስ ወጰራቅሊጦስ ተፈነወ ኀበ ሐዋርያት። ወዓዲ ይቤ ኵሉ ዘነገርኩክሙ ኢትክሉ ጸዊሮቶ ይእዜ ወመጺኦ ውእቱ ጰራቅሊጦስ ዘይፈኑ አብ በስምየ ያጤይቀክሙ ኵሎ ወያዜክረክሙ።

፹፯ ወካዕበ ይብል በእንቲአሁ ወበእንተ አቡሁ ውስተ ኦሪትክሙ ጽሑፍ ስምዐ ፪ ሰብእ ወ፫ አሙን ውእቱ፡ ወአነ ሰማዕት ለርእስየ ወሰማዕትየ አብ ዘፈነወኒ። ወካዕበ ይቤ በእንተ ጰራቅሊጦስ ወመጺአ ጰራቅሊጦስ ዘአነ እፌኑ ለክሙ እምኀበ አብ ውእቱ ሰማዕትየ ዘይወጽእ እምኀበ አብ መንፈሰ ጽድቅ ወአንትሙኒ ሰማዕ ትየ ከመ እምትካት ሀሉ ምስሌየ። ዮሐ፲፭+፳፮

፹፰ በእንተ አቡሁ ወበእንተ ርእሱ ይነግር እንዘ ይብል ኵሉ ዘሰማዕኩ በኀበ አቡየ እነግር ወኢይነግር ዘእምኀቤየ ወኢምንተኒ ወቃለ ዘአየ ዘትሰምዑ ኢኮነ ዚአየ ዘእንበለ ቃሉ ውእቱ ለአብ ለዘፈነወኒ ። ወበእንተ ጰራቅሊጦስኒ ይቤ ወመጺኦ ውእቱ መንፈሰ ጽድቅ ይመርሐክሙ በኵሉ ጽድቅ እስመ ኢይነግር ዘእምኀቤሁ ዘሰምዐ ዳእሙ ይነግር ወዘይመጽእ ይነግ ረክሙ። ውእቱ ኪያየ ይሴብሕ እስመ እምዚአየ ይነሥእ ወይነግረክሙ ኵሉ።ኵሉ ዘቦ ለአቡየ ዚአየ ውእቱ ወበእንተ ዝንቱ እብለክሙ እምዚ አየ ይነሥእ ወይነግረክሙ።ዮሐ፲፯+፵፱ ፣፲፮+፲፫

፹፱ ጳውሎስኒ ይቤ አሐዱ እግዚአብሔር ወአሐዱ ኅሩይ ማእከለ እግዚአብሔር ወሰብእ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኮነ ሰብአ ወመጠወ ርእሶ ቤዛ ኵሉ። ወካዕበ ይቤ ኵልክሙ ዘንተ ኀልዩ ዘከመ ገብረ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘውእቱ አርአያ ገጹ ለእግዚአብሔር። ፩ጢሞ፪+፮ ዕብ፩+፫

፺ አእምርኬ ከመ ሰመዮ ጳውሎስ ለወልድ አርአያ ገጹ ለእግዚአብሔር። እመሰኬ ፩ ገጽ እምይቤ ገጹ ለእግዚአብሔር እስመ አርአያ ገጹ ለእግዚአብሔር ብሂል ወልድ ይመስሉ ለአ ቡሁ። ወበእንተዝ ይቤ እግዚእነ በወንጌል ዘርእየ ኪየየ ርእዮ ለአቡየ፡ ዮሐንስኒ ይቤ ደቂቅየ ዘንተ እጽሕፍ ለክሙ ከመ ኢተአብሱ ወእመኒ በ ዘአበሰ ጰራቅሊጦስ ብነ ኀበ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ። ፩ ዮሐ፪+፩

፺፩ ንዑኬ ንጸውያሙ ለነቢያተ እግዚአብሔር

ሲል ለሁለት እንደሚገባ ይናገራል ለአንድ እንደሚገባም አይደለም። ዮሐ፲፬+፳፫፣፲፮+፴፪

፹፮ ዳግመኛም ስለመንፈስቅዱስም ዓለም ሊቀበለው የማይቻለውን የእውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስን ይልክላችሁ ዘንድ አብን እለምና ለሁ ብሎ ተናገረ። እነሆ በዚህም የሥላሴ ትምህ ርት ክፍል ወልድ ጰራቅሊጦስን ይልከው ዘንድ ጠየቀው። ጰራቅሊጦስም ወደ ሐዋርያት ተላከ ሁለተኛም የምነግራችሁን ሁሉ አሁን ልትሸ ከሙት አትችሉም አብ በስሜ የሚልክላችሁ ጰራቅሊጦስ እርሱ መጥቶ ሁሉን ይነግራችኋል ያሳስባችኋል አለ።

፹፯ ዳግመኛም በለሱና ስለ አባቱ በኦሪታ ችሁ የሁለት ወይም የሦስት ሰዎች ምስክርነት የታመነ ነው እኔ ለራሴ ምስክር ነኝ የላከኝም አብ ምስክሬ ነው አለ።ሁለተኛም ስለ ጰራቅ ሊጦስ እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ከአብ የሚ ወጣ የእውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስ እርሱም ምስክሬ ነው ከጥንት ጀምሮ ከእኔ ጋር እንደነበረ ምስክሮቼ ናችሁ አለ። ዮሐ፲፭+፳፮

፹፰ ስለ አባቱና ስለራሱ በአብ ዘንድ የሰማሁትን እናገራለሁ ከራሴም ምንም ምን አልናገርም የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ቃል እንጂ የእኔ አይደለም ብሎ ተናገረ። ስለ ጰራቅ ሊጦስም የእውነት መንፈስ እርሱ መጥቶ ወደጽድቅ ሁሉ ይመራችኋል ከራሱ አንቅቶ አይናገርም የሰማውን ይናገራል እንጂ የሚመ ጣውንም ይነግራችኋል እርሱ እኔን ያከብረኛል ከእኔ ተቀብሎ ይነግራችኋልና።ለአባቴ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ስለዚህም አላችኋለሁ ከእኔ ተቀብሎ ይነግራችኋል። ዮሐ፲፯+፵፱ ፣፲፮+፲፫

፹፱ ጳውሎስም እግዚአብሔር አንድ ነው በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለው ሰው የሆነውና ራሱን ለሁሉ ቤዛ አድርጎ የሰጠ የተመረጠ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ነው ብሎ ተናገረ።ሁለተኛም ሁላችሁ የእግዚአብሔር የፊ ቱ ምሳሌ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገላችሁን ይህን አስቡ አለ። ፩ጢሞ፪+፮ ዕብ፩+፫

፺ ጳውሎስ ወልድን የእግዚአብሔር የፊቱ ምሳሌ(መልክ) እንዳለው ዕወቅ፣አንድ ገጽስ ቢሆ ን የእግዚአብሔር ፊቱ ባለው ነበር። የእግዚ አብሔር የፊቱ ምሳሌ ማለት ወልድ አባቱን ይመስለዋልና ነው። ስለዚህም ጌታችን በወንጌል እኔን ያየ አባቴን አይቶታል አለ። ዮሐንስም ልጆቼ ሆይ እንዳትበድሉ ይህንን እጽፍላችኋለሁ የበደለም ቢኖር በአብ ዘንድ የሚያጸናን ኢየሱስ ክርስቶስ አለን አለ። ፩ ዮሐ፪+፩

፺፩ የሰባልዮስን ትምህርት ለመውቀስ

ከመ ያርድእዎሙ ለሐዋርያተ ኢየሱስ ክርስቶስ በዘሊፈ ትምህርቱ ለሰብአዮስ። ትብል ቅድስት አሪት ይቤ እግዚአብሔር ናሁ ኮነ አዳም ከመ ፩ እምኔነ የአምር ሠናየ ወእኩየ ዮጊ ያሌዕል እዴሁ ወይበልዕ እም ውእቱ ዕፀ ሕይወት ወየሐዩ ለዓለም። ወሶበሰኬ ፩ ገጸ ሥላሴ እምይቤ አዳም ኮነ ከማየ። ወዘይቤሰ አዳም ኮነ ከመ ፩ እምኔነ በእንተ ትስብእቱ ለክርስቶስ ዘውእቱ ሥጋ አዳም ዘነበረ በየማነ እግዚአብሔር። ዘፍ፫+፳፪

፺፪ ወካዕበ ትቤ ቅድስት አሪት ወይቤ እግዚአብሔር ንዑ ንረድ ወንክዐው ነገሮሙ ኢይሰምዑ እስመ አሐዱ ዘመድ እሙንቱ። ወካዕበ ትቤ ወአውረደ እግዚአብሔር ላዕለ ሰዶም ወገሞራ እሳተ ወተየ እምኀበ እግዚአብ ሔር እምሰማይ።ናሁኬ ያጤይቅ ወያሌቡ ከመ አሐዱ እምካልዑ አውረደ እሳተ እምሰማይ ሶበ ይብል ወአውረደ እግዚአብሔር እምኀበ እግዚአብሔር። ዘፍ፲፩+፯ ፣፲፱+፳፬

፺፫ ወካዕበ ትቤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሉ በሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ያንጽሑ ርእሶሙ የም ወጌሰመ ይሕጽቡ አልባሲሆሙ ወይጽንሑ ድልዋኒሆሙ ለአመ ሣልስት ዕለት እስመ በሣልስት ዕለት ይወርድ እግዚአ ብሔር ኀበ ደብረ ሲና። ናሁኬ ዜነወ ወልድ ርደቶ ለአብ ከመ የሀብ ሕገ ለሙሴ። ወካዕበ ትቤ ቅድስት አሪት ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ለአብርሃም በኀበ ዕፀ ምንባር እንዘ ይነብር ኀበ ኖኀተ ሐይመት ቀትረ። ወሶበ አልዐለ አዕይ ንቲሁ ወነጸረ ወናሁ ፫ ዕደው ይቀውሙ መልዕ ልቴሁ ወሰገደ ውስተ ምድር ወይቤሎሙ እጋእ ዝትየ እመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድመ አዕይንቲክ ሙ ናምጽእ ማየ ወንሕፅብ እገሪክሙ ወታጽ ልሉ ታሕተ ዕፅ ወናምጽእ ኅብስተ ወትብልዑ ወእምዝ ተሐውሩ ኀበ ኀለይክሙ እም ከመ ማኀሥክሙ ኀበ ገብርክሙ።ወይቤልዎ ግበር በከመ ትቤ። ዘፍ፲፰+፩-፬ ዘጸ፲፱+፲

፺፬ ዳዊትኒ ይቤ ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ። መኑኬ እግዚኡ ለዳዊት ዘእንበለ ዳእሙ ቅዱስ እስራኤል። ዘንተሰ ይቤ በእንተ ወልድ ዘነበረ በየማነ አቡሁ። ወእምዝ ያተሉ ወይብል እስከ አንብእሙ ለጸላዕትከ ታሕተ መከየደ እገሪከ። ዝኒ በእንተ ሰቃልያን። በትረ ኃይል ይፌኑ ለከ እግዚአብሔር እም ጽዮን። ወዝኒ ኃይለ ሃይማኖት ዘዕፀ መስቀል። ወት ኬንን በማእከለ ጸላእትከ። ዝኒ ዐውደ ምኩናን ዘዕለተ ፍዳ። ምስሌከ ቀዳማዊ በዕለተ ኃይል። ዕለተ ኃይልሰ መንግሥት እንተ ትመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወኃይል እንተ ትገፌትዮሙ ለዕል ዋነ ሃይማኖት። መዝ፻፱+፩-፫

የኢየሱስን ሐዋርያት ይረዱአቸው ዘንድ ኑ የእግዚአብሔርን ክብሯት እንጥራቸው። የከበረች አሪት እግዚአብሔርም አለ እነሆ አዳም በጎውንና ክፉውን ያውቅ ዘንድ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፣ገናም እጁን ያነሣል ከሕይወትም ዛፍ ይበላል ለዘላለምም በሕይወት ይኖራል አለች። የሥላሴ ገጽ አንድ ቢሆንስ ኖሮ አዳም እንደ እኛ ሆነ ባላለ ነበር።አዳም ከእኛ ጋር እንደ አንዱ ሆነ ያለው ግን ስለክርስቶስ ትስብእት (ሰው መሆን) ነው፣ ይኸውም በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው የአዳም ሥጋ ነው። ዘፍ፫+፳፪

፺፪ ዳግመኛም የከበረች አሪት እግዚአብ ሔርም አለ፡ ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማ ቋንቋቸውን እንደባልቀው አንድ ወገን ናቸውና ትላለች።ሁለተኛም እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ እሳትና ዲን አወረደ።እነሆ እግዚአብሔር ከእግዚ አብሔር ዘንድ አወረደ ሲል እሳትን ከሰማይ ማውረድ አንዱ ከሌላው መሆኑን ፈጽሞ ያስረ ዳል። ዘፍ፲፩+፯ ፣፲፱+፳፬

፺፫ ዳግመኛም አለች እግዚአብሔር ሙሴን የእስራኤልን ልጆች ዛሬ ራሳቸውን እንዲያነጹ ነገም ልብሶቻቸውን እንዲያጥቡ በሦስተኛውም ቀን የተዘጋጁ ሆነው እንዲጠብቁ አዘዛቸው በሦ ስተኛው ቀን እግዚአብሔር ወደ ደብረሲና ይወ ርዳልና።እነሆ ወልድ ለሙሴ ሕግን ሊሰጥ አብ መውረዱን ተናገረ። ሁለተኛም የከበረች አሪት አለች እግዚአብሔር በመምሬ ዛፍ ሥር በቀትር በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ለአብርሃም ተገለ ጠለት ዓይኖቹንም አንሥቶ ተመለከተ። እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው ነበር።ወደ ምድርም ሰግዶ ጌቶቼ በፊታችሁ ሞገስን አግኝቼ ከሆነ ውኃ አምጥተን እግራችሁን እንጠብ በዛፍም ሥር እረፉ ወደ አገልጋያችሁም ከመጣችሁ ዘንድ እንጀራ እናምጣና ብሉ ከዚያም ወዳሰባች ሁት ትሄዳላችሁ አለ፡እነርሱም እንዳልኸው አድ ርግ አሉት። ዘፍ፲፰+፩-፬ ዘጸ፲፱+፲

፺፬ ዳዊትም ጌታ ጌታዬን በቀኜ ተቀመጥ አለው አለ። ከእስራኤል ቅዱስ በቀር የዳዊት ጌታ እንግዲህ ማን ነው። ይህንን ግን በአባቱ ቀኝ ስለተቀመጠ ስለ ወልድ ተናገረ።ከዚህም አስከትሎ ጠላቶችህን ከእግርህ መረገጫ በታች እስኪያደርጋቸው ድረስ ይላል።ይህም ስለ ሰቃዮች ነው። የኃይልን በትር እግዚአብሔር ከጽዮን ይልክልሀል አለ፣ይህም የዕፀ መስቀል የሃይማ ኖት ኃይል ነው።በጠላቶችህ መካከል ትፈርዳለህ አለ፣በፍዳ ቀን የሚሆን የፍርድ አደባባይ ነው። ቀዳማዊ እርሱ በኃይል ቀን ከአንተ ጋር ነው አለ፣የኃይል ቀንም በእግዚአብሔር ስም የምት መጣ መንግሥት ናት ኃይልም የሃይማኖት ባለጋራ ዎችን የምትገለባብጣቸው ናት። መዝ፻፱+፩-፫

፶፭ በብርሃናሙ ለቅዱሳን። ዝኒ ስነ ብርሃን ዘዕሤተ ጻድቃን እስመ ምግባሩ ለጻድቅ ያበርህ ሎቱ። ወሰድኩከ እምከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ።ዝኒ ይተረጐም በሥምረተ መለኮት እስመ ከርሥ መዝገበ ኀሊናሁ ለብእሲ። ወወልድኒ ኀሊናሁ ለአብ እስመ አልቦ ኀሊና ባዕለ አብ ዘኢሀሉ ባዕለ ወልድ። ወበእንተዝ ይቤ ወሰድኩከ እምከርሥ፣ ልደት ውሳጤያዊት ወአኮ አፍአዊት። ወእምቅድመ ኮከበ ጽባሕሰ ዘይቤ በእንተ ብርሃን ዘፍጥረተ ዓለም በከመ ጽሑፍ ዘይብል ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ብርሃን ወኮነ ብርሃን። እስመ ጽባሕ ቀደሚት ሰዓት ይእቲ ዘመዐልት ወብርሃንኒ ቀዳሚ ግብሩ ውእቱ ዘፍጥረተ ዓለም። ወካዕበ ይተረጐም ኮከበ ጽባሕ ለሰይጣን በእንተ ቀደመ ተፈጥሮ በዕለተ እሑድ። ወድቀቱሰ ኮነ በዕለተ ረቡዕ። ወበእንቲአሁ ይቤ ኢሳይያስ ነቢይ ለምንትኬ ወድቀ ኮከበ ጽባሕ ዘይሠርቅ ሶበ ይገውሕ፡ እስመ ይቤ እነብር መንበርየ መልዕልተ አርዮብ ወእዐርግ ውስተ ምጽንዓት ወእትሜሰሎ ለልዑል። ዘፍ፩+፫ ኢሳ፲፬+፲፪

፶፮ ወመትልወ ቃለ ዳዊት ይቤ መሐለ እግዚአብሔር ወኢይኔስሕ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከጼዴቅ።ዘንተ ይቤ በእን ተ ቍርባነ ወንጌል ዘበኅብስተ ሥርናይ ወወይን፡ ትብል ቅድስት ኦሪት መልከጼዴቅ አውጽሐ ኅብስተ ወወይነ ወካህኑ ለእግዚአብሔር ውእቱ። መዝ፻፱+፬

፶፯ ወካዕበ ይቤ በወንጌል ነሥአ ኅብስተ አእኰተ ወባረከ ወፈተተ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ ውእቱ ሥጋየ ። ወከማሁ ጽዋዐኒ ባሪኮ ይቤ ሎሙ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ኢይሰቲ እንከ እምዝንቱ እጺረ ፍሬ ወይን እስከ አመ እሰትዮ ሐዲሰ በመንግሥተ አቡየ።ወበእንተዝ ይቤ ጳውሎስ ወሰዘሰ በመሐላ ሤሞ ይቤ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከጼዴቅ፡ ወኢይቤ በከመ ሢመቱ ለአሮን።ማቴ፳፮+፳፮ ዕብ፭+፮

፶፰ ንትመየጥኬ ኀበ ቃለ መዝሙር ዘይቤ እግዚአብሔር በየማንከ። ናሁኬ አጠየቀነ ነቢረ መንፈስቅዱስ በየማነ ወልድ ወበጥንተ መዝ ሙር ይቤ ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ እንዘ ያኤምር ነቢረ ወልድ በየማነ አብ። ወእምድኅሬሁ ይብል በቃለ ዝ መዝሙር እግዚአብሔር በየማንከ። አርአየኬ ህላዌ ሥላሴ በበጾታሁ ወትሥልስተ መለኮት በበንባሬሁ። ዘሰ ኢይሌቡ በዝኒ አይሌቡ ወዘኒ ይትከሀድ በዝኒ ይትከሀድኑ።

፶፱ ኢሳይያስኒ ይቤ ወእምዝ በዓመተ ሞተ ዖዝያን ንጉሥ ርኢክዎ ለእግዚአብሔር ጸባዖት ይነብር ዲበ መንበሩ ነዋኅ ወልዑል ወም

፶፭ በቅዱሳን ብርሃን አለ፣ ይህም የቅዱሳን በጎ ዋጋ የብርሃኑ ክብር(ጸዳል) ነው የጻድቅ ሰው ሥራው ያበራለታልና። ከአጥቢያ ኮከብ አስቀ ድሞ ከሆድ ወለድሁህ አለ፣ይህም በመለኮት ፈቃድ ይተረጐማል።ሆድ የሰው የኅሊናው መዝ ገብ ነውና።ወልድም የአብ ኅሊናው ነው፣ በወል ድ የሌለ ኅሊና በአብ የለምና። ስለዚህም ከሆድ ወለድሁህ አለ፣አፍአዊት ያልሆነች ውሳጣዊት ልደት ናት። ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ያለውም ስለ ዓለም ፍጥረት ብርሃን ነው። እግዚአ ብሔርም አለ ብርሃን ይሁን ብርሃንም ሆነ ተብሎ እንደተጻፈ።ንጋት የቀን የመጀመሪያዋ ሰዓት ናትና። ብርሃንም የዓለም ፍጥረት የመጀመሪያ ግብር ነውና። ዳግመኛም የአጥቢያ ኮከብ በእሑድ ቀን በመፈጠር ስለቀደመ በሰይጣን ይተረጐማል፣ አወዳደቁ ግን በረቡዕ ቀን ሆነ። ስለርሱም ነቢዩ ኢሳይያስ ጐሀ በቀደደ ጊዜ የሚወጣ የአጥቢያ ኮከብ ለምን ወደቀ ብሉ ተናገረ። ዙፋኔን በዐቢይ ኮከብ ላይ አኖራለሁ ወደ ሣልሲት ሰማይም እመጣለሁ ልዑልን እመስለዋለሁ ብሏልና።ዘፍ፩+፫ ኢሳ፲፬+፲፪

፶፮ ቀጥሎም የዳዊት ቃል እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትም አለ። አንተ እንደ መልከጼዴቅ ክህነት ለዘላለም ካህን ነህ ይህንን በስንዴ ኅብስትና በወይን ስለሚሆን የወንጌል ቁርባን ተናገረ። የከበረች ወንጌል መልከጼዴቅ ኅብስትና ወይን አቀረበ አለች የእግዚአብሔርም ካህን ነው። መዝ፻፱+፬

፶፯ ዳግመኛም በወንጌል ኅብስቱን አንሥቶ አመሰገነ አከበረ ቆርሶም ይህ ሥጋዬ ነው እንካ ችሁ ብሉ ብሎ ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው። ጽዋ ውንም እንዲሁ ባርኮ ይህ ጽዋ ደሜ ነው እንካ ችሁ ጠጡ በአባቴ መንግሥት አዲሱን እስክጠ ጣው ድረስ ከእንግዲህ ከዚህ የወይን ጭማቂ አልጠጣም ብሎ ሰጣቸው። ስለዚህም ጳውሎስ በመሐላ የሾመውን እንደ መልከጼዴቅ ሹመት አንተ ለዘላለሙ ካህን ነህ አለ እንደ አሮን ክህነት ግን አላለም። ማቴ፳፮+፳፮ ዕብ፭+፮

፶፰ እግዚአብሐር በቀኝህ ይሁን ወደሚለው የመዝሙር ቃል እንመለስ፡ እነሆ የመንፈስቅዱስን በወልድ ቀኝ መቀመጥ አስረዳን በመዝሙር መጀመሪያ ጌታ ጌታዬን በቀኜ ተቀ መጥ አለው አለ። የወልድን በአብ ቀኝ መቀመጥ ሲያመለክት። ከርሱም በኋላ በመዝሙር ቃል እግዚአብሔር በቀኝህ ይሁን ያለው የሥላሴን አኗኗር በየወገኑ ሦስትነቱንም በየአቀማመጡ አመለከተ።የማያስተውል በዚህም አያስተውልምን? የሚክድም በዚህ ይክዳልን?

፶፱ ኢሳይያስም ከዚህም በኋላ ንጉሥ ዖዝያን ባሞተበት ወራት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋኑ ተቀምጦ አየሁት ቤቱም ከምስጋ

ሉዕ ቤተ ስብሐቲሁ። ወሱራፌል ይቀውሙ ዐውዶ ወለለ፩ ፩ ዘበበ፮ ክንፊሆሙ ወተሰዐሰ መርፈቀ ኖኀት እምቃል ዘይኬልሑ ወይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐ ቲከ።ወብሂለ ቅዱስሰ ለእመ ፩ ገጽ ውእቱ ወ፩ሂ እምበቀ·ዖሙ ወእመ አብዝትሂ እምፈድፈዶሙ አላ ከመ ያጠይቁ ጾታ ሥላሴ ወሀቡ ፫ ቅዳሴያተ። ወብሂለ እግዚአብሔር ጸባዖት ዘ፩ ጊዜ አመሩ ጽምረተ መለኮት። ኢሳ፮+፩-፭

፱ ዳንኤልኒ ይቤ ወእምጽኡ መናብርተ ለብሉየ መዋዕል ወሥዕርተ ርእሱ ጸዓዳ ከመ ፀምር ወአዕይንቲሁ ከመ ነደ እሳት ወፈለገ እሳት ይውኅዝ ቅድሜሁ። ወእምጽኡ መጻሕፍተ ወከሠትዋ በቅድመ እግዚአብሔር ወለመጽሐፈ ሕይወትሰ ከሠትዋ እንተ ባሕቲታ። ወመጽአ ወልደ እጓለ እመሕያው ወነበረ ኀበ ብሉየ መዋዕል። ናሁኬ ነበረ ፩ ኀበ ካልዑ ወፍካሬሁሰ ወልድ ኀበ አቡሁ። ወበዝኒ ኢትሌቡኑ ኦ ዕውረ ልብ። ወካዕበ ይቤ ዳንኤል አመ ፲ወ፰ ዓመት በ፰ ጽባሕ በረቡዐ ሠርቀ ወርኀ ቀደሚ ሀለውኩ እነ ኀበ ፈለግ ዐቢይ ወነጸርኩ ብእሴ ዘይለብስ በድነ ወቅኑት ውስተ ሐቌሁ በወርቀ አፌዝ ወነፍስቱሂ ከመ ተርሴስ። ዘንተ ይቤ በእንተ ወልድ ዘለብሰ ሥጋ መዋቴ። ደገመ ወይቤ ናሁ ከመ አምሳለ ወልደ እጓለ እመሕያው ገሰሰኒ ከናፍርየ ከሠትኩ አፉየ ወነበብኩ። ዘንተ ይቤ በእንተ አብ። ኢይቤ ወልደ እጓለ እምሕያው አላ ይቤ አምሳለ ወልደ እጓለ እመሕያው እስመ በአምሳለ እግዚአብሔር ተፈጥረ እጓለ እመሕ ያው። ወዓዲ ሥልሰ ይቤ ወዳግመ ገሠሠኒ ከመ ራእየ ብእሲ ወአጽንዐኒ። በእንተ ወልድሰ ይብል ዘይለብስ በድነ እንዘ ያኤምር ትስብእቶ። ወበእንተ አብኒ ይብል አምሳለ እጓለ እመሕያ ው። በእንተ መንፈስቅዱስኒ ይብል ከመ ራእየ ብእሲ። ናሁኬ አግኀሦሙ እምተሰብኦ ለአብ ወለመንፈስቅዱስ።ወባሕቱ ነገረ አርአያ ወአም ሳለ በከመ ንቤ ቀዳሚ። ዳን፯+፱-፲፫ ፲+፬-፭

፲፪ ሕዝቅኤልኒ ይቤ ወመጽአ ዝኩ ብእሲ ዘይለብስ ጰደሬ ወቅናት ውስተ ሐቌሁ፡ተሠጥወ ወይቤ ገበርኩ በከመ አዘዝከኒ። ናሁኬ ያወሥእ ወልድ ለአቡሁ በእንተ ዘፈጸመ ትእዛዞ።ወልብሰ ጰደሬሰ ሥጋ ንጽሕት ይእቲ እንተ ኢረስሐት እስመ ጰደሬ ስሙ ለልብሰ ሜላት ንጹሕ። ሕዝ፲+፩-፫

፲፫ ወካዕበ ይቤ ሕዝቅኤል ወይቤሉ ለብእሲ ዘይለብስ ጰደሬ ባእ ማእከለ ሠረገላ ዘታ ሕተ ኪሩብ ወምላዕ እዴከ አፍሐመ እሳት ወዝ ርዎ ውስተ ሀገር። ወበእቱሰ ለወልድ ማዕከለ

ናው የተነሣ የተመላ ነው። ሱራፌልም በዙሪ ያው ቆመው ነበር፡ ለእያንዳንዳቸውም ስድስት ስድስት ክንፎች አሉአቸው። የደጃፉም መድረክ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አቸናፊ ፍጹም የምስጋናህ ክብር በሰማይና በምድር የመ ላ ነው፡ ብለው ከሚጮሁት ቃል የተነሣ ተና ወጸ።አንድ ገጽ ቢሆን ቅዱስ ማለቱ አንዱ በበቃ ቸው ነበር ቢያበዙትም በበዛባቸው ነበር የሥላሴ ን ማዕረግ ያስረዱ ዘንድ ሦስት ምስጋናዎችን አቀረቡ።አንድ ጊዜ አቸናፊ እግዚአብሔር ማለት የመለኮትን አንድነት አመለከቱ። ኢሳ፮+፩-፭

፱ ዳንኤልም በዘመን ለሸመገለው ዙፋኖችን አመጡ የራስ ጠጉሩም እንደግምጃ ነጭ ነው፡ዓይኖቹም እንደ እሳት ናቸው፡የእሳትም ወን ዝ በፊቱይፈሳል፣መጽሐፍም አምጥተው በእግዚ አብሔር ፊት ገለጡአት ብቻዋን ያለች የሕይ ወት መጽሐፍንም ገለጡአት የሰው ልጅ መጣ በዘመን በሸመገለው ዘንድ ተቀመጠ እነሆ አንዱ በሁለተኛው ዘንድ ተቀመጠ።ትርጉሙም ወልድ በአባቱ ዘንድ ነው ማለት ነው። ልብህ የታወረ ሆይ በዚህም አታስተውልምን።ዳግመኛም ዳንኤ ል አለ ከዐሥራስምንት ዓመት በኋላ በሃያ አንደ ኛው ንጋት የፊተኛው ወር በባተ በአራተኛው ቀን በታላቅ ወንዝ አጠገብ ሳለሁ ነጭ ሐር የለ በሰ ሰው አየሁ ወገቡንም በአፌዝ ወርቅ ታጥቆ ነበር ሰውነቱም እንደሚያበራ ዕንቍ ነበር። ይህንን ሟች ሥጋን ስለለበሰ ስለ ወልድ ተናገ ረ።ደግሞም እነሆ የሰው ልጅ የመሰለ ከንፈሮቼ ን ዳሰሰኝ አፌንም ከፍቼ ተናገርሁ አለ፡ይህንን ስለ አብ ተናገረ፣ የሰው ልጅ አላለም የሰው ልጅ የመሰለ አለ እንጂ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ምሳሌ ተፈጥሯልና።ሦስተኛም ዳግመኛም በሰው መልክ ያለ ዳሰሰኝ አጸናኝም አለ፣ ስለ ወልድ ግን ሰው መሆኑን ሲያመለከት ነጭ ሐር የለበሰ አለ። ስለአብም የሰው ልጅ የመሰለ አለ ስለ መንፈስቅዱስም እንደሰው መልክ አለ እነሆ አብና መንፈስቅዱስን ሰው ከመሆን ለያቸው። ነገር ግን የአርአያ የአምሳል ነገር አስቀድመን እንደተናገርነው ነው።ዳን፯+፱-፲፫ ፲+፬-፭

፲፪ ሕዝቅኤልም አለ ግምጃ የለበሰ ይህ ሰው መጣ በወገቡም ዝናር ነበረ እንዳዘዝኸኝ አደረግሁ ብሎ መለሰ፣ እነሆ ትእዛዝ ስለፈጸመ ወልድ ለአባቱ መለሰለት፣ ግምጃ ልብስም ያላደፈች ንጽሕት ሥጋ ናት ግምጃ የንጹሕ ሐር ልብስ ስም ነውና። ሕዝ፲+፩-፫

፲፫ ዳግመኛም ሕዝቅኤል አለ ግምጃ ልብስ የለበሰውን ሰው ከኪሩብ በታች ወዳለው ሠረገላ ግባ በእጅህም የእሳቱን ፍም መልተህ ወደ ከተማ በትነው አለው። የወልድ ወደ ኪሩብ

ኪሩብ ክቡር ኀበ ህላዌ አቡሁ። ወዘረወ እፍሐመ እሳትኒ መንፈስቅዱስ ውእቱ ዘወረደ ሳዕለ ሐዋርያት ከመ ዘእሳት እስመ ሠለስቲሆሙ ዲበ ሠረገላ ኪሩቤል ይነብሩ።ወበሂለ እሳትሰ አብኒ እሳት በከመ ይቤ ሙሴ እስመ እግዚአብሔር አምላክነ እሳት ውእቱ ዘይወጽእ።ወልድኒ እሳት በከመ ይቤ ኢሳይያስ ወተፈነወ ኀቤየ ፩ እምሱራፌል ዘውስተ እዴሁ ፍሕም፡ ነሥአ በጉጠት ፍሕመ እምውስተ ምሥዋዕ ወአልከፈኒ ከናፍርየ። ወዓዲመ መንፈስቅዱስ እሳት እስመ ወረደ በጽርሐ ጽዮን ከመ ዘእሳት በከመ ጽሑፍ በግብረ ሐዋርያት። ኢሳ፮+፮ ሐዋ፪+፫

፶፬ ናሁኬ አብጻሕኩ ለክሙ ስምዐ እምቃለ ኦሪት ወነቢያት ወእምቃለ ወንጌል ወሐዋርያት። ወእመሰ ትትከሀዱኒ ወበእንተ ገጽ ወመልክዕ ያዕቆብኒ ይቤ ርኢክዎ ለእግዚአብሔር ገጸ በገጽ ወድኅነት ነፍስየ። ካዕበ ትቤ ቅድስት ኦሪት እንዘ ትነግር ከመ ተምዐ እግዚአብሔር ዲበ አሮን ወማርያም እኅቱ ወይቤሎሙ እመቦ ዘኮነ ነቢየ እምኔክሙ በራእይ አስተርኢ ሎቱ ወበሕ ልም እትናገሮ፡ አኮ ከመ ቍልዔየ ሙሴ ዘእት ናገሮ ገጸ በገጽ ወአፈ በአፍ።ዳዊትኒ ይቤ ገጸ ዚአከ አኀሥሥ እግዚኦ ወኀሠሥኩ ገጸከ ወኢት ሚጥ ገጸከ እምገብርከ።

፶፭ ወካዕበ ይቤ ሚጥ ገጸከ እምኃጢአትየ። ወዓዲ ይቤ ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ። ወካዐበ ይቤ ገጹ ለእግዚአብሔር ኀበ እለ ይገብሩ እኩየ፡ ወዓዲ ይቤ ኢትግድፈኒ እምቅድመ ገጽከ፡ወዓዲ ይቤ አይቴኑ አሐውር እመንፈስከ ወአይቴኑ እጐይይ እምቅድመ ገጽከ። መዝ፲+፬፣ ፹፫+፲፭

፶፮ እግዚእነሂ ይቤ በወንጌል ዘሰ ክህደኒ በገጸ ሰብእ እክህዶ አነኒ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት። ዘሰ አምነኒ በገጸ ሰብእ አነኒ አአምኖ በገጸ አቡየ ዘበሰማያት። ወካዕበ ይቤ ኀድግዎሙ ለእሉ ሕፃናት ወኢትክልእዎሙ መጺአ ኀቤየ እስመ መላእክቲሆሙ ዘልፈ ይሬእዩ ገጾ ለአቡየ ዘበሰማያት።

፶፯ ጳውሎስኒ ይቤ ዝ ውእቱ አርአያ ገጹ ለእግዚአብሔር።

፶፰ ወበእንተ ርእሱኒ ይቤ ዳንኤል ወሥዕርተ ርእሱ ጸዓዳ ከመ ፀምር። ሰሎሞንኒ ይቤ ርእሱ ወርቀ ቴፋዝ ወድላሴሁ ጸሊም ከመ ቋዕ።በእንተ ዓይንኒ ንነግር ይቤ ዳዊት እስመ አዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር ኀበ ጻድቃን ወእዝኑሂ ኀበ ስእለቶሙ። ወካዕበ ይቤ አዕይንቲሁኒ ኀበ ነዳይ ይኔጽራ ወቀራንብቲሁኒ የሐትቶ ለእጓለ እመሕያው። ወዓዲ ይቤ አዕይንቲሁኒ ኀበ ነዳይ ያስተኀይዓ። ዳን፲+፱ መዝ፲+፱

፶፱ ኢሳይያስኒ ይቤ ቦኑ ኢይሬኢ በአዕይንትየ ወቦኑ ኢይሰምዕ በእዝንየ። ወባሕቱ

መግባቱ በአባቱ ዕሪና መኖር ነው። የእሳት ፍም መብተንም በእሳት አምሳል በሐዋርያት ላይ የወረደ መንፈስቅዱስ ነው። ሦስቱም በኪሩቤል ሠረገላ ይቀመጣሉና እሳት ማለትም አብ እሳት ነው ሙሴ አምላካችን እግዚአብሔር የሚነድ እሳት ነው እንዳለ፣ ወልድም እሳት ነው። ኢሳይያስ በእጁ ፍም ያለ ከሱራፌል አንዱ ተላከ ከመሠዊያውም በጉጠት ፍም አንሥቶ ከንፈ ሮቼን አስነካኝ አለ። ሁለተኛም መንፈስቅዱስም እሳት ነው በጽርሐ ጽዮን በእሳት ላንቃ አምሳል ወርዷልና በየሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደ ተጻፈ። ኢሳ፮+፮ ሐዋ፪+፫

፶፬ እነሆ ከኦሪትና ከነቢያት ቃል ከወን ጌልና ከሐዋርያትም ቃል አስረጅ ምስክር አመጣሁላችሁ ስለ ገጽና ስለ መልክ የምትከራከሩኝ ከሆናችሁስ ያዕቆብም እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁት ሰውነቴም ድና ቀረች አለ። የከበረች ኦሪትም ሁለተኛ እግዚአብሔር በአሮንና በእኅቱ በማርያም ላይ ተቆጥቶ በመካከላችሁ ከእናንተ ነቢይ ቢኖር በራእይ እገለጥለታለሁ በሕልምም አነጋግረዋለሁ ፊት ለፊት አፍም ለአፍ እንደማ ነጋግረው እንደወዳጄ እንደ ሙሴ ግን አይደለም እንዳላቸው ትናገራለች።ዳዊትም አቤቱ ፊትህን አሻለሁ ፊትህን ፈለግሁ ፊትህን ከባሪያህ አት መልስ አለ።

፶፭ ሁለተኛም ፊትህን ከኃጢአቴ መልስ አለ፣ ዳግመኛም ፊትህን ከእኔ አትመልስ አለ ከእንደገና የእግዚአበሐር ፊቱ ክፉ ወደሚያ ደርጉት ነው አለ።ዳግመኛም ከፊትህ አትጣለኝ አለ።ዳግመኛም ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ ከፊ ትህስ ወዴት እሸሻለሁ አለ። መዝ፲+፬፣ ፹፫+፲፭

፶፮ ጌታችንም በወንጌል በሰው ፊት የካደኝን እኔም በሰማያት ባለ አባቴ ፊት እክደ ዋለሁ በሰው ፊት ያመነብኝንም በሰማያት ባለ በአባቴ ፊት አምነዋለሁ አለ። ዳግመኛም ወደኔ ይመጡ ዘንድ እነዚህን ሕፃናት ተውአቸው ጠባቂዎቻቸው ዘወትር በሰማያት ያለ የአባቴን ፊት ያያሉና አለ።

፶፯ ጳውሎስም የእግዚአብሔር የፊቱ ምሳሌ የሆነ ይህ ነው አለ።

፶፰ ስለ ራስም ዳንኤል የራስ ጠጉሩ እንደ ግምጃ ነጭ ነው አለ። ሰሎሞንም ራሱ ዝምዝም ወርቅ ጠጉሩም እንደ ቁራ ጥቁር ነው አለ።ስለ ዓይንም እንናገር፣ዳዊት የእግዚአብሔር ዓይኖቹ ወደ ጻድቃን ናቸው ጆሮዎቹም ወደ ልመናቸው አለ።ዳግመኛም ዓይኖቹም ወደ ድሀው ይመለከ ታሉ ቅንድቦቹም የሰውን ልጅ ይመረምሩታል አለ።ሁለተኛም ዓይኖቹ ወደ አሕዛብ ይመለከታ ሉ አለ። መዝ፲+፱ ዳን፲+፱

፶፱ ኢሳይያስም አለ በውኑ በዓይኖቼ አላይምን በጆሮዎቼስ አልሰማምን ነገር ግን

ኃጢአትክሙ ይቀውም ማእከሌየ ወማእከሌክሙ ይቤ እግዚአብሔር:: ወካዕበ ይቤ አሌ ሎሙ ለእለ ያስተእኅዙ ቤተ ምስለ ቤት ወለእለ ያስ ተቃርቡ ገራህተ ምስለ ገራህት ከመ ይቅስጡ ዘኮነ እምገራህተ ቢጾሙ ከመ ተሰምዐ ዝንቱ ነገር ውስተ እዝነ እግዚአብሔር ፀባዖት:: ኢሳ፭፥፰

ኃጢአታችሁ በእኔና በእናንተ መካከል ቆሟል ይላል እግዚአብሔር:: ዳግመኛም አለ ቤትን ከቤት ጋር ለሚያያዙ በባልንጀራቸው እርሻ የሆነውን ይሰርቁ ዘንድ እርሻን ከእርሻ ጋር ለሚያቀራርቡ ወዮላቸው ይህ ነገር በአሸናፊ እግዚአ ብሔር ጆሮ ተሰምቷልና:: ኢ፡፭፥፰

፰ ካዕበ ይቤ ዳዊት አጽምዕ እግዚኦ እዝነከ ወስምዐኒ ኀቤየ:: ወካዕበ ይቤ ወይኩን እዝንከ ዘያጸምእ ቃለ ስእለትየ:: ናሁኬ ተዐውቀ ከመ ቦቱ ለእግዚአብሔር ዐይን ወቀራንብት ወአእዛን:: ወዓዲ ይነግራ መጻሕፍት ከመ ቦቱ አእዳው: ትብል ቅድስት ኦሪት ሰበ ፈጸመ እግዚአብሔር ተናግሮቶ ለሙሴ ወሀቦ ጽላተ ዘኪዳን ወጽላተ ዘትእዛዝ እለ ጽሑፋት በአጸ ብዒሁ ለእግዚአብሔር:: ወካዕበ ይቤሎ እግዚ አብሔር ለሙሴ እነ እሠይም ገጽየ ውስተ ስቍረተ ኰኵሕ ወእሜወር በእዴየ::ወካዕበ ይቤ በነቢይ ሰማይኒ መንበርየ ወምድርኒ መከየደ እገርየ አየኑ ቤተ ተሐንጹ ሊተ ለምዕራፍየ ይቤ እግዚአብሔር:: እኮኑ እደውየ ገብራ ዘኵሎ:: ዘጸ፴፩፥፲፰ ኢሳ፷፮፥፩

፰ ዳግመኛም ዳዊት አቤቱ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል ስማኝም አለ: ሁለተኛም ጆሮህ የልመናዬን ድምጽ የሚሰማ ይሁን አለ፣ እነሆ እግዚአብሔር ዓይንና ሽፋሽፍት ጆሮዎችም እን ዳሉት ታወቀ::ዳግመኛም እጆች እንዳሉት መጻ ሕፍት ይናገራሉ:: የከበረች ኦሪት አለች እግዚ አብሔርም ለሙሴ መናገሩን በፈጸመ ጊዜ የትእ ዛዙን ጽላት በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፈባቸ ውን የኪዳን ጽላት ሰጠው::ሁለተኛም እግዚ አብሔር ሙሴን ፊቴን በተሰነጠቀ አለት አደር ጋለሁ በእጄም እሠውራለሁ አለው::በነቢይም ዳግመኛ ሰማይ ዙፋኔ ምድርም የእግሬ መረገጫ ነው እነሆ ለማረፊያዬ ምን ዓይነት ቤት ትሠሩ ልኛላችሁ ይላል እግዚአብሔር ይህን ሁሉ እጆቼ የሠሩት አይደለምን:: ዘጸ፴፩፥፲፰ ኢሳ፷፮፥፩

፰፩ ዳዊትኒ ይቤ ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር ወግብረ እደዊሁ ያየድዓ ምጽና ዓት:: ወዓዲ ተብህለ በመዝሙር የድ እደዊከ ገብራኒ ወለሐኳኒ:: ወዓዲ ተብህለ ፈኑ እዴከ እምአርያም:: ወዓዲ ተብህለ መዝራዕትከ ምስለ ኃይል: ጽንዐት እዴከ ወተለዐለት የማንከ:: ወካዕበ ዓዲ ተብህለ ትርከቦሙ እዴከ ለኵሎሙ ፀርከ::ወትትረከቦሙ እዴከ ለኵሎሙ ጸላዕ ትከ:: ወዓዲ ተብህለ ህየኒ እዴከ ትመርሐኒ ወታነብረኒ የማንከ:: ወዓዲ ተብህለ እስመ አንተ ረዳእየ እግዚኦ ውስተ እዴከ አማሕፀን ነፍስየ:: ወዓዲ ተብህለ እዴከ ሠረወቶሙ ለፀር ወተከልከ ኪያሆሙ: ሣቀይኮሙ ለአሕዛብ ወሰደድኮሙ: ዘኢኮ በኲናቶሙ ወረስዋ ለምድር ወመዝራዕቶ ሙኒ ኢያድኀኖሙ::ዘእንበለ የማንከ ወመዝራዕ ትከ ወብርሃነ ገጽከ:: መዝ፲፰፥፩ ፣፵፫፥፫ ፣፻፲፰፥፸፫

፰፩ ዳዊትም ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የእጆቹንም ሥራ ሰማያት ይመሰ ክራሉ አለ::ዳግመኛም በዮድ መዝሙር እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም ተባለ፣ ደግመኛም እጅህን ከአርያም ላክ ተባለ ሁለተኛም ክንድህ ከኃይል ጋር ነው እጅህ ፀናች ቀኝህም ከፍ ከፍ አለች ተብሎ ተነገረ::ሁለተኛም እጅህ ጠላቶ ችህን ሁሉ ታገኛቸው ተባለ: ዳግመኛም በዚያም እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ታስቀምጠኛለች ተባ ለ:: ዳግመኛም አንተ ረዳቴ ነህና ነፍሴን በእጅህ አማጽናለሁ ተባለ:: ዳግመኛም እጅህ ጠላቶችን ነቀለቻቸው እነርሱን ግን ተከልህ አሕዛብን ጣቀ የኻቸው አሳደድሃቸውም ምድርን በሰይፋቸው የወረሱአት አይደለም ክንዳቸውም አላዳናቸውም ከቀኝህና ከክንድህ ከፊትህም ብርሃን በቀር ተባለ:: መዝ፲፰፥፩ ፣፵፫፥፫ ፣፻፲፰፥፸፫

፰፪ ወዓዲ ተብህለ አንተ ፈጠርከኒ ወወደይከ እዴከ ላዕሌየ:: ወዓዲ ተብህለ ለምንት እግዚኦ ትመይጥ እዴከ ወየማንከ ማዕከለ ሕፅንከ ለግሙራ:: ወዓዲ ይቤ አንተ አቅደምከ ሣርሮታ ለምድር ወግብረ እደዊከ እማንቱ ሰማያት:: ወበኢሳይያስኒ ይቤ እዴከ ሣረረታ ለምድር ወየማንከ አጽንዐቶ ለሰማይ:: እመኑኬ ከመ ቦቱ ለእግዚአብሔር እእዳው ወመዝራዕት ወአጻብዕ:: ወበእንተ እንፍኒ ትብል ቅድስት ኦሪት ወአጼነወ እግዚአብሔር መዓዛ መሥዋዕቱ ለኖኅ:: ወበእንተ እንግድዓኒ ትብል ወጾሮሙ በእንግድዓሁ እግዚአብሔር ባሕቲቱ መር ሖሙ:: ዘፍ፰፥፳፩ ዘዳ፴፪፥፲፩ መዝ፻፩፥፳፭

፰፪ ዳግመኛም አንተ ፈጠርኸኝ እጅህንም በእኔ ላይ አኖርህ ተባለ:: ሁለተኛም አቤቱ ስለምን እጅህን ትመልሳለህ ቀኝህንም ለዘላለሙ ከእቅፍህ ተባለ::ሁለተኛም አቤቱ አንተ ምድርን መፍጠርን አስቀደምህ፣ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው ተባለ:: በኢሳይያስም አለ እጅህ ምድርን ሠራቻት ቀኝህም ሰማይን አፀናችው:: እግዚአ ብሔር እጆችና ክንድ ጥፍርም እንዳለው ዕወቁ :: ስለአፍንጫም የከበረች ኦሪት እግዚአብሔር ም የኖኅን መሥዋዕት መዓዛ አሸተተ አለች: ስለ ደረትም በደረቱ ተሸክማቸው እግዚአብሔር ብቻውን መራቸው ትላለች::ዘፍ፰፥፳፩ ዘዳ፴፪፥፲፩ መዝ፻፩፥፳፭

ኃጢአትክሙ ይቀውም ማእከሌየ ወማእከሌክሙ ይቤ እግዚአብሔር:: ወካዕበ ይቤ አሌ ሎሙ ለእለ ያስተእንዝዙ ቤተ ምስለ ቤት ወለእለ ያስተቃርቡ ገራሀተ ምስለ ገራሀት ከመ ይትስጡ ዘኮነ እምገራሀተ ቢጾሙ ከመ ተሰምዐ ዝንቱ ነገር ውስተ እዝነ እግዚአብሔር ፀባዖት:: ኢሳ፩+፲፰

ኃጢአታችሁ በእኔና በእናንተ መካከል ቆሟል ይላል እግዚአብሔር:: ዳግመኛም አለ ቤትን ከቤት ጋር ለሚያያዙ በባልንጀራቸው እርሻ የሆነውን ይሰርቁ ዘንድ እርሻን ከእርሻ ጋር ለሚያቀራርቡ ወዮላቸው ይህ ነገር በአሸናፊ እግዚአ ብሔር ጆሮ ተሰምቷልና:: ኢሳ፩+፲፰

፹ ካዕበ ይቤ ዳዊት አጽምዕ እግዚኦ እዝነከ ወስምዐኒ ጎቤየ:: ወካዕበ ይቤ ወይኩን እዝንከ ዘየጸምእ ቃለ ስእለትየ:: ናሁኬ ተዐውቀ ከመ ቦቱ ለእግዚአብሔር ዐይን ወቀራንብት ወአእዛን:: ወዓዲ ይነግራ መጻሕፍት ከመ ቦቱ እእዳው: ትብል ቅድስት አሪት ሶበ ፈጸመ እግዚአብሔር ተናግሮቶ ለሙሴ ወሀቦ ጽላተ ዘኪዳን ወጽላተ ዘትእዛዝ እለ ጽሑፋት በአጻብዒሁ ለእግዚአብሔር:: ወካዕበ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አነ እሠይም ገጽየ ውስተ ስቁረተ ኰኵሕ ወእሜወር በእዴየ::ወካዕበ ይቤ በነቢይ ሰማይኒ መንበርየ ወምድርኒ መከየደ እገርየ አየኑ ቤተ ተሐንጹ ሊተ ለምዕራፍየ ይቤ እግዚአብሔር:: አኮኑ እደውየ ገብራ ዘኰሉ:: ዘጸ፴፩+፲፰ ኢሳ፷፩+፩

፹ ዳግመኛም ዳዊት አቤቱ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል ስማኝም አለ: ሁለተኛም ጆሮህ የልመናዬን ድምጽ የሚሰማ ይሁን አለ፣ እነሆ እግዚአብሔር ዓይንና ሽፋሽፍት ጆሮዎችም እን ዳሉት ታወቀ::ዳግመኛም እጆች እንዳሉት መጻ ሕፍት ይናገራሉ:: የከበረች ኦሪት እለች እግዚ አብሔርም ለሙሴ መናገሩን በፈጸመ ጊዜ የትእ ዛዙን ጽላት በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፈባቸ ውን የኪዳን ጽላት ሰጠው::ሁለተኛም እግዚ አብሔር ሙሴን ፊቴን በተሰነጠቀ አለት አደር ጋለሁ በእጄም እሠወራለሁ አለው::በነቢይም ዳግመኛ ሰማይ ዙፋኔ ምድርም የእግሬ መረገጫ ነው እነሆ ለማረፊያዬ ምን ዓይነት ቤት ትሠሩ ልኛላችሁ ይላል እግዚአብሔር ይህን ሁሉ እጆቼ የሠሩት አይደለምን:: ዘጸ፴፩+፲፰ ኢሳ፷፩+፩

፹፩ ዳዊትኒ ይቤ ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር ወግብረ እደዊሁ ያየድዓ ምጽና ዓት:: ወዓዲ ተብህለ በመዝሙር ዮድ እደዊከ ገብራኒ ወለሐኳኒ:: ወዓዲ ተብህለ ፈኑ እዴከ እምአርያም:: ወዓዲ ተብህለ መዝራዕትከ ምስለ ኃይል: ጸንዐት እዴከ ወተለዐለት የማንከ:: ወካዕበ ዓዲ ተብህለ ትርከቦሙ እዴከ ለኵሎሙ ፀርከ::ወትትረከቦሙ እዴከ ለኵሎሙ ጸላዕ ትከ:: ወዓዲ ተብህለ ሀየኒ እዴከ ትመርሐኒ ወታነብረኒ የማንከ:: ወዓዲ ተብህለ እስመ አንተ ረዳእየ እግዚኦ ውስተ እዴከ አማሐፅን ነፍስየ:: ወዓዲ ተብህለ እዴከ ሠረወቶሙ ለፀር ወተከለከ ኪያሆሙ: ሣቀይኮሙ ለአሕዛብ ወሰደድኮሙ: ዘአኮ በኵናቶሙ ወረስዋ ለምድር ወመዝራዕቶ ሙኒ ኢያድኅኖሙ::ዘእንበለ የማንከ ወመዝራዕ ትከ ወብርሃነ ገጽከ:: መዝ፲፰+፩ ፣፺፫+፯ ፣፻፲፰+፸፫

፹፩ ዳዊትም ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የእጆቹንም ሥራ ሰማያት ይመሰ ክራሉ አለ::ዳግመኛም በዮድ መዝሙር እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም ተባለ፣ ደግመኛም እጅህን ከአርያም ላክ ተባለ ሁለተኛም ክንድህ ከኃይል ጋር ነው እጅህ ፀናች ቀኝህም ከፍ ከፍ አለች ተብሎ ተነገረ::ሁለተኛም እጅህ ጠላቶ ችህን ሁሉ ታገኛቸው ተባለ: ዳግመኛም በዚያም እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ታስቀምጠኛለች ተባ ለ:: ዳግመኛም አንተ ረዳቴ ነህና ነፍሴን በእጅህ አማጽናለሁ ተባለ:: ዳግመኛም እጅህ ጠላቶችን ነቀለቻቸው እነርሱን ግን ተከልህ አሕዛብን ሣቀ የኻቸው አሳደድሀቸውም ምድርን በሰይፋቸው የወረሱአት አይደለም ክንዳቸውም አላዳናቸውም ከቀኝህና ከክንድህ ከፊትህም ብርሃን በቀር ተባለ:: መዝ፲፰+፩ ፣፺፫+፯ ፣፻፲፰+፸፫

፹፪ ወዓዲ ተብህለ አንተ ፈጠርከኒ ወወደይከ እዴከ ላዕሌየ:: ወዓዲ ተብህለ ለምንት እግዚኦ ትመይጥ እዴከ ወየማንከ ማዕከለ ሕፅንከ ለግሙራ:: ወዓዲ ይቤ አንተ አቅደምከ ሣርርታ ለምድር ወግብረ እደዊከ እማንቱ ሰማያት:: ወበኢሳይያስኒ ይቤ እዴከ ሣረረታ ለምድር ወየማንከ አጽናዐቶ ለሰማይ:: እመኑኬ ከመ ቦቱ ለእግዚአብሔር እእዳው ወመዝራዕት ወአጻብዕ:: ወበእንተ እንፍኒ ትብል ቅድስት ኦሪት ወአጼነወ እግዚአብሔር መዓዛ መሥዋዕቱ ለኖኅ:: ወበእንተ እንግድዓኒ ትብል ወጾርሙ በእንግድዓሁ እግዚአብሔር ባሕቲቱ መር ሖሙ:: ዘፍ፰+፳፩ ዘዳ፴፪+፲፩ መዝ፻፩+፳፭

፹፪ ዳግመኛም አንተ ፈጠርኸኝ እጅህንም በእኔ ላይ አኖርህ ተባለ:: ሁለተኛም አቤቱ ስለምን እጅህን ትመልሳለህ ቀኝህንም ለዘላለሙ ከእቅፍህ ተባለ::ሁለተኛም አቤቱ አንተ ምድርን መፍጠርን አስቀደምህ፣ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው ተባለ:: በኢሳይያስም አለ እጅህ ምድርን ሠራቻት ቀኝህም ሰማይን አፀናችው:: እግዚአ ብሔር እጆችና ክንድ ጥፍርም እንዳለው ዕወቁ :: ስለአፍንጫም የከበረች ኦሪት እግዚአብሔር ም የኖኅን መሥዋዕት መዓዛ አሸተተ አለች: ስለ ደረትም በደረቱ ተሸከማቸው እግዚአብሔር ብቻውን መራቸው ትላለች::ዘፍ፰+፳፩ ዘዳ፴፪+፲፩ መዝ፻፩+፳፭

፳፫ ወበእንተ ሐቌ ወገበዋት ይቤ ኢሳይያስ ዘይቀንት ጽድቀ ውስተ ሐቌሁ ወይትዐጸፍ ርትዐ ውስተ ገቦሁ:: ዳንኤልኒ ይቤ ወቅንትት ሐቌሁ በወርቀ አፌዝ:: አቡቀለምሲስኒ ይቤ ወቅኑት ውስተ ሐቌሁ በቅናት ዘወርቅ:: ወካዕበ ይቤ ወጽሑፍ ውስተ ገቦሁ ዘይብል ንጉሠ ነገሥት ወእግዚአ አጋእዝት:: ዳን፲+፱

፳፬ ወበእንተ አእጋርኒ ትነግር ቅድስት አሪት ዘከመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ንግእ በትረ እምነ ደብተራ ዘመርጡል ወዝብጥ ኩኩሐ ኀበ ይቀውማ እገሪሁ ለእግዚአብሔር ለፌ ወለፌ:: ወካዕበ ትቤ ወርእዩ መካነ ኀበ ይቀውም እግዚአብሔር ዘእስራኤል ዘታሕተ እገሪሁ ከመ ግብረተ ግንፋል ዘሰንፔር ወከመ ርእየተ ጽንዓ ሰማይ ሶበ ሐወጸት :: ዘጸ፳፬+፲

፳፭ ዳዊትኒ ይቤ ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ:: ካዕበ ይቤ ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ እስከ አገብኦሙ ለጸላዕትከ ታሕተ መከየደ እገሪከ:: ወዓዲ ይቤ አጽንነ ሰማያተ ወወረደ ወቆባር ታሕተ እገሪሁ:: ዘካርያስኒ ይቤ ወይቀውማ እገሪሁ ለእግዚአብሔር ውስተ ደብረ ዘይት:: እግዚእነሂ ይቤ በወንጌል ኢትምሐሉ በሰማይ እስመ መንበሩ ለእግዚአብሔር ውእቱ ወኢበምድር እስመ መከየደ እገሪሁ ለእግዚአብሔር ይእቲ::

፳፮ እንከሰ ንትመየጥኬ ኀበ አፍ:: ትነግር ቅድስት ኦሪት ዘከመ ይቤ እግዚአብሔር አጽምዕ ሰማይ ወእንግርከ ወትስማዕ ምድር ቃለ አፋየ:: ወካዕበ ይቤ በመዝሙር ይኄይሰኒ ሕገ አፉከ እምአእላፍ ወርቅ ወብሩር:: ወዓዲ ይቤ በእንተ ዳዊት ወኢይሔሱ ዘወፅአ እምአፉየ ምዕረ መሐልኩ ለቅዱስየ ከመ ለዳዊት ኢይሔስዎ:: ወዓዲ ይቤ ወተዘከሩ መንክሮ ዘገብረ ተአምሪሁ ወኩነኔ አፉሁ:: ወዓዲ ይቤ ኢሳይያስ እስመ አፉሁ ለእግዚአብሔር ነበበ ከመዝ:: ወቃለ መዝሙር ይነግር ካዕበ እንዘ ይብል በቃለ እግዚአብሔር ጸንዓ ሰማያት ወእምእስትንፋሰ አፉሁ ኩሉ ኃይሎሙ:: ወዓዲ ይቤ ይገንዩ ለከ እግዚኦ ኩሎሙ ነገሥተ ምድር እስመ ሰምዑ ኩሎ ቃለ አፉከ:: መዝ፴፪+፮፣፹፰+፴፬ ዘካ፲፬+፬ ማቴ፭+፴፬

፳፯ ናሁኬ አብጻሕነ ለከ ስምዐ እመጻሕፍት ከመ ቦቱ ለእግዚአብሔር ፍጹመ መልክዐ እጓለ እመሕያው:: ኅድግ እንከሰ አ ንፉቅ ዕልወተ ዘላዕሌከ እመን በሥላሴ ወተጋነይ ለግጻዌ መለኮት::ወእመሰ አጥባዕከ በኑፋቄከ ይከውን መክፈልትከ ምስለ እለ ኢተጠምቁ ወርስትከኒ ምስለ ተንበላት ወኢትትኄለቍ ምስለ አባግዓ መርዔቱ ክርስቶስ::

፳፫ ስለወገብም ስለጉናችም ኢሳይያስ በወገቡ ጽድቅን ይታጠቃል ቅንነትንም በወገቡ ይታጠቃል አለ:: ዳንኤልም ወገቡ በአፌዝ ወርቅ የታጠቀ ነው::አቡቀለምሲስም ወገቡን በወርቅ ዝናር የታጠቀ ነው:: ዳግመኛም በወገቡም የንጉሦች ንጉሥ የጌቶች ጌታ የሚል ስም ተጽፏል አለ:: ዳን፲+፱

፳፬ ስለ እግሮችም የከበረች ኦሪት እግዚአብሔር ሙሴን ከደብተራ ኦሪት በትር ወስደህ የእግዚአብሔር እግሮች በዚህና በዚያ የቆሙበትን አለት ምታ እንዳለው ተናገረች:: ዳግመኛም እስራኤል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የቆመበትን ሥፍራ ከበታቹ በሰንፔር እንደተሠራ ጣዖት በጉብኙት ጊዜም እንደ ሰማይ ጽናት መልክ የሆነ አዩ:: ዘጸ፳፬+፲

፳፭ ዳዊትም የእግዚአብሔር እግር በቆመበት ሥፍራ እንሰግዳለን አለ፣ ሁለተኛም በእግሮቹ መረገጫ በታች ይሰግዱለታል:: ዳግመኛም አለ ጌታ ጌታዬን አለው ጠላቶችህን ከእግሮችህ በታች እስካስገዛልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው:: ዳግመኛም ከሰማያት ወረደ ከእግሮቹም በታች ጭጋግ አለ:: ዘካርያስም የእግዚአብሔር እግሮቹ በደብረ ዘይት ይቆማሉ አለ::ጌታም በወንጌል በሰማይ አትማሉ የእግዚአብሔር ዙፋኑ ነውና በምድርም አትማሉ የእግዚአብሔር የእግሩ መረገጫ ናትና ብሏል::

፳፮ እንግዲስ ወደ አፍ እንመለስ፣ የከበረች ኦሪት እግዚአብሔር ሰማይ ስማ ልንገርህም ምድርም የአፌን ቃል ትስማ እንዳለ ተናገረች:: ዳግመኛም በመዝሙር ከብዙ ሺህ ወርቅና ብር ይልቅ የአፍህ ሕግ ይሻለኛል አለ:: ሁለተኛም ስለዳዊት ከአፌ የወጣውን አልዋሽም ዳዊትን እንዳልዋሸው በቅድስናዬ ፈጽሜ ማልሁ አለ::ሁለተኛም ያደረገውን ድንቁንና ተአምራቱን የአፉንም ፍርድ አስቡ አለ::ኢሳይያስም ዳግመኛ የእግዚአብሔር አፍ እንዲህ ተናግሮአልና አለ በመዝሙርም ቃል ሁለተኛ በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ ብሎ ተናገረ:: ዳግመኛም አቤቱ የምድር ነገሥታት ሁላቸው ይገዙልሀል የአፍህን ቃል ሁሉ ሰምተዋልና አለ:: መዝ፴፪+፮፣፹፰+፴፬ ዘካ፲፬+፬ ማቴ፭+፴፬

፳፯ እነሆ እግዚአብሔር እንደ ሰው ልጅ ፍጹም መልክ እንዳለው ከመጻሕፍት አስረጅ አደረስንልህ ተጠራጣሪ ሆይ እንግዲህስ ባንተ ያለውን ክህደት ትተህ በሥላሴ እመን ለመለኮት በአካል መለየትም ምስጋናን አቅርብ:: በጥርጥርህ ከጸናህ ግን እድል ፈንታህ ካልተጠመቁ ጋር ርስትህም ከአስላሞች ጋር ይሆናል ከእግዚአብሔር መንጋዎች ጋርም አትቆጠርም::

፰፰ እንከሰ ንብል ስብሐት ለአብ ለዘፈነወ ወልዶ ውስተ ማኅፀነ ድንግል:: ወስጊድ ለወልድ ዘተሠገወ እምኔሃ: አኰቴት ለመንፈስ ቅዱስ ለዘቀደሳ ወአንጽሓ ወአጽንዓ::

፰፱ ወካዕበ ንብል ስብሐት ለአብ ለዘስምዐ ኮነ በእንተ ወልዱ በውስተ ምጥማቃት:: ወስጊድ ለወልድ ለዘተጠምቀ በውስተ ዮርዳኖስ:: አኰቴት ለመንፈስቅዱስ ለዘነበረ ዲቤሁ በርእየተ ርግብ:: ወዓዲ ንብል ስብሐት ለአብ ለዘተሣሃለነ በሞተ ወልዱ:: ወስጊድ ለወልድ ለዘጥዕመ ሞተ በእንተ መድኃኒትነ:: አኰቴት ለመንፈስቅዱስ ለዘአብጠሉ ለሥልጣነ ሞት በሞተ ኢየሱስ ክርስቶስ:: ማቴ፫ ፥ ፲፮-፲፯

፺ ወዓዲ ንብል ስብሐት ለአብ ለዘአንሥኦ ለወልድ እሙታን::ወስጊድ ለወልድ ለዘነበረ በየማነ አቡሁ::አኰቴት ለመንፈስ ቅዱስ ለዘወረደ ላዕለ ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን:: ወእምዝኒ ንብል ስብሐት ለአብ ለዘይ ወርድ በግርማ መንግሥቱ::ወስጊድ ለወልድ ለዚያቀውም አባግዐ በየማኑ ወአጣሌ በፀጋሙ::አኰቴት ለመንፈስ ቅዱስ ለዘይፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ::ለዓለም አሜን: ወአሜን: ለይኩን:: ማቴ፳፰ ፥ ፴፱ ሐዋ፪ ፥ ፴፱ ፪ ፥ ፬

፺፩ ተፈጸመ ዘለፋሁ ለሰባልዮስ መጽሐፈ ሕግ ዘእምብሉይ ወእምሐዲስ: ዘይነግር በእንተ ስምዐ ሥሉስ: ጸልዩ ወባርኩኒ ሊተ ለጊዮርጊስ: ዘጽሕቀ ለተናግሮ እንዘ ጽቡስ: በእንተ ቅንዐ ሃይማኖት ለለባስያነ መንፈስቅዱስ:: አሜን::

.......... /// ..........

፰፰ እንግዲህስ ልጁን ወደ ድንግል ማኅፀን ለላከ ለአብ ምስጋናን ከእርሷ ለተወለደ ለወልድም ስግደትን ላከበራት ባለመለወጥም ላጸናት በንጽህናም ለጠበቃት ለመንፈስቅዱስም አኰቴትን እናቀርባለን::

፰፱ ዳግመኛም በማጥመቂያው ስለ ልጁ ምስክር ለሆነ ለአብ ምስጋና በዮርዳኖስ ለተጠመቀ ለወልድም ስግደት በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ላረፈ ለመንፈስቅዱስ አኰቴት ይገባል እንበል:: ሁለተኛም በልጁ ሞት ይቅር ላለን ለአብ ምሥጋና ይገባል እኛን ስለማዳን ሞትን ለቀመሰ ለወልድም ስጊድ ይገባል በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የሞትን ሥልጣን ላጠፋ ለመንፈስቅዱስም አኰቴት ይገባል እንበል:: ማቴ፫ ፥ ፲፮-፲፯

፺ ዳግመኛም ልጁን ከሙታን ለይቶ ላስነሣው ለአብ ምስጋና ከሙታን ተለይቶ ለተነሣ ለወልድም ስግደት በጽርሐጽዮን በሐዋርያት ላይ ለወረደ ለመንፈስቅዱስም አኰቴት ይገባል እንበል::ከዚህም በኋላ በግርማ መንግሥቱ ለሚመጣ ለአብ ምስጋና በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ለሚያቆም ለወልድ ስግደት ለሁሉ እንደ የሥራው ለሚከፍለው ለመንፈስቅዱስም አኰቴት ይገባል እንበል ለዘላለሙ አሜን ይሁን:: ማቴ፳፰ ፥ ፴፱ ሐዋ፪ ፥ ፴፱ ፪ ፥ ፬

፺፩ ስለ ሥላሴ ምስክርነት የሚናገር ከብሉይና ከሐዲስ የተገኘ የሕግ መጽሐፍ የሆነ የሰባልዮስ ተግሣጽ ተፈጸመ:ደካማ ስሆን ስለ ሃይማኖት ቅናት ለመናገር ለተጋሁ ለጊዮርጊስ መንፈስቅዱስን የለበሳችሁ ሆይ ጸልዩልኝ ባርኩኝም አሜን: አሜን::

.......... /// ..........

## ምዕራፍ ፪

## ዘብርሃናት ምንባብ

፩ በስመ ሥሉስ ቅዱስ ኅቡረ ህላዌሁ ዘኢይትፈለጥ ወኢይቶሳሕ ዘእሐደ ይሰገድ ወእሐደ ይሴባሕ ዲበ ሠረገላ ነፋሳት ዐውደ ፀሐይ ዘይቄጥሕ ዘያሠርቆ በኀዋኀወ ሰማይ ኃይለ ነፋስ እንዘ ይነፍሕ ወነበልባለ ፀሐይ እንዘ ይትራዋሕ ወለዐውደ ቀመሩ ለወርኀ ዘይዌስኮ ብርሃነ ለለጽባሕ እስከ ይመልዕ ጥንቁቀ በዕለተ ገሐህ እምከርሠ ደመናት ነጠብጣበ ዝናማት ዘይ ቀድሕ ጸዳለ መባርቅት እንዘ ይትጋዋሕ ወቃለ ነጐድጓድ እንዘ ይኬልሕ፡ ሎቱ ስብሐት ለመኩ ንነ ኵሉ ፍጥረት ለዓለመ ዓለም አሜን ወአሜን።

፪ ንጽሕፍ እንከ ዘለፋሁ ለአቡርዮስ ዘይቤ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ዘዘዚአሁ። እፎኬ ደፈርከ ኦ አቡርዮስ ከመ ትበል አብሂ በምኵናኑ ወበሥርዓቱ ወልድሂ በምኵናኑ ወበ ሥርዓቱ መንፈስቅዱስሂ በምኵናኑ ወበሥ ርዓቱ።

፫ መቅድመሰኬ ፍታሕ ላዕለ ርእስከ። ወእመሰ ፫ ሥርዓተ ሥላሴ መኑኬ ፈጠረከ ወመኑኬ ገብረከ። ትብልኑ አብ ፈጠሮ ለርእስየ ወወልድ ለሐኮ ለእደዊየ ወመንፈስቅዱስ አጽንዖ ለእገርየ።

፬ ናሁኬ ገበርከ ፍልጠተ ውስተ መልክዕከ። ወካዕበመ ትብልኑ አብ አምላከ ሥጋየ ወወልድ አምላከ ነፍስየ ወመንፈስቅዱስ አምላከ አዕጽ ምትየ ወአሥራውየ።

፭ ናሁኬ ዘረውከ ርእሰከ በከመ ዘረውከ ጽምረተ ሥላሴ።ወዓዲመ ትብልኑ ከመ አብ ሰማያተ ገብረ ወወልድኒ ምድረ ሣረረ። ወመንፈ ስቅዱስሂ አቀመ ባሕረ። ወእመሰ ዘንተ ትብል ኮንከ ሱታፌ ትምህርቶሙ ለማርያን፡ እስመ ይቤልዎ ነገሥተ አረሚ ለቅዱስ እግዚአብሔር ጊዮርጊስ አእምር ጊዮርጊስ ከመ አጵሎን ሰማያተ ገብረ ወኤራቅሊስ ምድረ ሣረረ ሰቀምድ ሮስ ወአቴና ፀሐየ ሠርዑ ወአርዌውስ ወሶፎ ባሕረ አቀሙ። ናሁኬ ኮንከ መትልወ ትምህር ቶሙ ለረሲዓን ወከፈልኮ ለጽምረተ ሥላሴ ከመ አማልክተ አሕዛብ።

፮ ሰብልያኖስ ቶስሐ ሥላሴ በኢያእምሮ። ወአንተኒ ዘረውከ ሥላሴ በኢለብዎ። ሰብልያኖስ ኀበረ ሥርዐተ ምስለ ተንበላት ወአንተሂ ኀበርከ ሥርዓተ ምስለ መምለክያነ ጣዖት ለእለሰ ብዙኀ አማልክቲሆሙ ብዙኀ አጋንንቲሆሙ።

## ምዕራፍ ሁለት

## የብርሃናት ምንባብ

፩ በህልውና አንድ በሆነ በማይለወጥና በማይጨመርበት በአንድነት በሚሰገድለት በአን ድነትም በሚመሰገን የነፋስን ኃይል እየነፈሰ የፀሐይም ነበልባል እየተርገበገበ የፀሐይን ክበብ በነፋሳት ሠረገላ በሚከምር በሰማይ መስኮቶች ም በሚያወጣው ለጨረቃም ዐውደ ቀመር ፈጽ ሞ እስኪመላ ድረስ በብርሃን ቀን በየጠዋቱ ብር ሃንን በሚስልበት የመብረቆች ብልጭታ ሲያ በራ የነጐድጓድም ድምጽ ሲጮህ የዝናብ ጠብታ ዎችን ከደመናዎች ማኅፀን በሚቀዳ በሥሉስ ቅዱስ ስም ለፍጥረታት ሁሉ ገዥ ለእርሱ ምስ ጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን

፪ እንግዲህ አብና ወልድ መንፈስቅዱስም ለየራሳቸው ናቸው ያለ የአቡርዮስን ተግሣጽ እን ጽፋለን። አቡርዮስ ሆይ አብ በአገዛዙና በሥር ዓቱ ጸንቶ ይኖራል፡ወልድም በአገዛዙና በሥር ዓቱ ጸንቶ ይኖራል መንፈስቅዱስም በአገዛዙና በሥ ርዓቱ ጸንቶ ይኖራል ትል ዘንድ እንደምን ደፈርህ።

፫ አስቀድመህ በራስህ ፍረድ የሥላሴ ሥር ዓት ሦስት ከሆነ ማን ፈጠረህ ማንስ አበጀህ። አብ ራሴን ፈጠረው ወልድም እጄን አበጀው መንፈስቅዱስም እግሬን አጸናው ትላለህን።

፬ እነሆ በመልክህ መለያየትን አደረግህ ሁለተኛም አብ የሥጋዬ አምላክ ነው ወልድም የነፍሴ አምላክ ነው መንፈስቅዱስም የአጥቶቼና የሥሮቼ አምላክ ነው ትላለህን።

፭ እነሆ የሥላሴን አንድነት እንደበተንህ ራስህን በተንህ።ዳግመኛም አብ ሰማያትን እንደፈ ጠረ ወልድም ምድርን እንደፈጠረ መንፈስቅዱ ስም ባሕርን እንዳቆመ ትናገራለህን ይህንንስ ካልህ የጠንቋዮች ትምህርት ማኅበርተኛ ሆንህ የአረማውያን ነገሥታት የእግዚአብሔርን ቅዱስ ጊዮርጊስን ጊዮርጊስ ሆይ አጵሎን ሰማያትን እን ደፈጠረ ኤራቅሊስም ምድርን እንደሠራ ሰቀማን ድሮስና አቴናም ፀሐይን እንደፈጠሩ አርዌውስና ሶፎ ባሕርን እንዳቆሙ ዕወቅ አሉት።እነሆ የዘንጉዎችን ትምህርት የምትከተል ሆንህ የሥላሴን ም አንድነት እንደ አሕዛብ አማልክት ከፈልኸው።

፮ ሰብልያኖስ ባለማወቅ ሥላሴን ቀላቀለ አንተም ባለማስተዋል ሥላሴን ትበትናለህ። ሰብልያኖስ ከእስላሞች ጋር በሥርዓት ተባበረ አንተም ጣዖት ከሚያመልኩ ጋር በሥርዓት ተባበርህ አማልክቶቻቸው ብዙ ስሆኑት አጋንቶቻቸውም ብዙ ናቸው።

፯ ለሰብልያኖስ ዘለፈቶ ቅድስት ኦሪት ሰበ ትነግር እንዘ ትብል ይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ:: ወለከኒ ዘለፈተከ ሶበ ታየድዕ እንዘ ትብል ስማዕ እስራኤል ፩ እግዚአብሔር አምላክከ ኢኮነ ፪ ወኢ፫ :: ዘንተ ዘይቤ አኮ ከመ ያጽርዕ ትሥልስተ አላ ከመ ያስተዋኅድ ጽምረተ ሥላሴ:: ዘፍ፩+፳፮ ዘዳ ፮+፬

፰ ለሰብልያኖስ አውቀይነ ልሳኖ ሶበ ንብል በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ በበገጻዊሆሙ ወለከኒ ፈጸምነ አፉከ ሶበ ንብል ፩ አምላክ በህላዌሆሙ:: ለሰብልያኖስ ዘሰፍናሆ ከመ ኢያስተዋሕድ ገጻዌ መለኮት ወለከኒ ከላዕናከ ከመ ኢታስተባዕድ ሥላሴ:: ኦ አቡርዮስ እፎኑ ትከፍሎ ለዘኢይተከፈል ወእፎ ትሌልዮ ለዘኢ ይትሌለይ:: ኦ አቡርዮስ እፎ ትነፍቆ ለዘኢይትነፈቅ ወእፎ ትዘርዎ ለዘኢይዘረው::

፱ ኦ አቡርዮስ እፎ ታስተባዕድ ለዘኢይትበዐድ ወእፎ ታስተርሕቅ ለዘኢይ ርሕቅ:: ኦ አቡርዮስ እፎኑ ትብል ነኪር ፩ እም ፩ ወይትፈለጥ ካለኡ እምካልኡ:: ሠፀርከ ርእሰ ከ በሰይፈ መለኮት ወመተርከ ልሳነከ በመጥ ባሕተ ወንጌል:: ትብልኑ በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ከመ እሳት ወነፋስ ወማይ:: እመኒ ስመይክሙ እሳተ ፩ ውእቱ እሳተ ሕይ ወት ዘያውዒ ሦከ ኃጢአቶሙ ለመሀይምናን:: ወእመኒ አስተማሰልክሙ በነፋስ ፩ መንፈስ እሙንቱ ህላዌሆሙ ዘኢይትገሠሥ:: ወእምኒ አስተማሰልክሙ በቀላየ ማይ ፩ ውእቱ ባሕረ ምሕረት ዘበስመ ዚአሁ ተጠመቅነ::

፲ ኢትገኒ ላዕለ ሥርዓተ ሥላሴ በገዕዘ ፫ ጠባይዕ ዘዘከርናሆሙ ዘ፩ ውዑይ ወ፩ ቊሪር ወ፩ ርጡብ:: በከመ አብ ፀሐይ ዘዘልፈ ያበርህ ወልድኒ ፀሐይ ዘዘልፈ ያበርህ ዲበ ቅዱሳን መንፈስቅዱስኒ ፀሐይ ዘያሠረግዎ ለቤተ ክርስቲያን::

፲፩ ወበከመ አብ ይነብር ዲበ ሠረገላ ኪሩቤል ወልድኒ ይነብር በየማኑ ዲበ ፬ እንስሳሁ ወከመ ወልድ ይነብር ዲበ እንስሳሁ መንፈስቅዱስኒ ይሜለስ ዲበ መንበረ ስብሐ ቲሁ::

፲፪ ወበከመ አብ ለሐኮ ለአዳም ወልድኒ ገብሮ በአርአያሁ ወበአምሳሊሁ:: ወበከመ ወልድ ገብሮ በአርአያሁ ወበአምሳሊሁ መንፈስቅዱስኒ ፈጠሮ በመልክዐ ዚአሁ::ወበከመ አብ አስተንፈሰ በአፈ ነቢያት ወይቤ ወለድኩከ እምከርሥ እም ቅድመ ኮከበ ጽባሕ:: ወካዕበ ይቤ በአፈ ኢሳይያስ ናሁ ይሌቡ ቍልዔየ ይትሌዓል ወይከ

፯ ሰብልያኖስን የከበረች ኦሪት እግዚአብ ሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር አለ ብላ በተናገረች ጊዜ ዘለፈችው: አንተንም እስራኤል ሆይ ስማ አምላክህ አንድ ነው ሁለት ወይም ሦስት አይደለም ብላ (ተና ገረች ጊዜ ዘለፈችህ::ይህንን ያለው የመለኮትን ሦስትነት ሊያጠፋ አይደለም የሥላሴን አንድነት ያስማማ(አንድ ያደርግ) ዘንድ ነው እንጂ:: ዘፍ፩+፳፮ ዘዳ ፮+፬

፰ በየአካሉ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም ባልን ጊዜ የሰብልያኖስ አንደበቱን ቆረጥን በባሕርዩ አንድ አምላክ ባልንም ጊዜ የአንተን አፍ ዘጋን የመለኮትን አካል አንድ እን ዳይል ሰብልያኖስን ገሠጽነው::አንተንም ሥላሴን እንዳትለይ ከለከልንህ::አቡርዮስ ሆይ የማይከፈለ ውን እንደምን ትከፍለዋለህ የማይለይ እርሱን እንደምን ትለየዋለህ:አቡርዮስ ሆይ የማይከፈለ ውን እርሱን እንደምን ትከፍለዋለህ የማይበተነ ውን እንደምን ትበትነዋለህ::

፱ አቡርዮስ ሆይ የማይለይ እርሱን እንደምን ትለየዋለህ የማይርቀውን እንደምን ታርቀዋለህ:: አቡርዮስ ሆይ እንደምን አንዱ ከአንዱ ልዩ ነው ሁለተኛውም ከሦስተኛው ይለያል አልህ፣ ራስህን በመለኮት ሰይፍ ቆረጥህ ምላስህን በወንጌል ካራ ቆረጥኸው:: አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስንም እንደ እሳትና ነፋስ እንደ ውኃም ናቸው ትላለህን፣ እሳትም ካልሁቸው የምእመና ንን የኃጢአታቸውን እሾህ የሚያቃጥል አንድ የሕይወት እሳት ናቸው::በነፋስም ብትመ ስላቸው አካላቸው የማይዳሰስ አንድ መንፈስ ናቸው:: በቀላይ ውኃ ብትመስላቸው በስሙ የተጠመቅን አንድ የምሕረት ባሕር ነው::

፲ አንዱ የሚያቃጥል አንዱም የሚቀዘቅዝ አንዱም ርጥበት ባለው በጠቀስነው ሦስት ጠባያት በሕርይ የሥላሴን ሥርዓት አታስብ: አብ የማይጠልቅ ፀሐይ እንደሆነ ወልድም ዘወትር በቅዱሳን ላይ የሚያበራ ፀሐይ ነው::ወልድ ዘወትር በቅዱሳን ላይ የሚያበራ ፀሐይ እንደሆነ መንፈስቅዱስም ቤተክርስቲያንን የሚያስጌጣት ፀሐይ ነው::

፲፩ አብ በኪሩቤል ሠረገላ እንደሚቀመጥ ወልድም በቀኙ በአራቱ እንስሳ ላይ ይቀመጣል ወልድ በአራቱ እንስሳው ላይ እንደሚቀመጥ መንፈስቅዱስም በምስጋና ዙፋኑ ላይ በሦስትነት ይመሰገናል::

፲፪ አብ አዳምን እንዳበጀው ወልድም በመልኩና በምሳሌው ፈጠረው መንፈስቅዱስም በመልኩ ፈጠረው:: አብ በነቢያት አንደበት የአጥቢያ ኮከብ ሳይፈጠር አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ ሁለተኛም በኢሳይያስ አፍ እነሆ ወዳጄ ያስተውላል ከፍ ከፍ ይላል ይከብራል

ብር ወያክሩ አሕዛብ በእንቲአሁ። ወካዕበመ ይቤ አነ እከውኖ አባሁ ወውእቱኒ ይከውነኒ ወልድየ።በአፈ ያዝያን ይቤ እም ግብጽ ጸዋዕክዎ ለወልድየ። ዝ ስምዐ አብ በእንተ ወልዱ ዘበነቢ ያቲሁ ዘተየድዐ። መዝ፻፱+፫ ሆሴ፲፩+፩

፲፫ ወካዕበመ ወልድሂ አስተንፈሰ በአፈ ነቢያቲሁ በእንተ አቡሁ ወይቤ እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ ወአነ ዮም ወለድኩከ ሰአል እምኔየ እሁበከ አሕዛበ ለርስትከ ወምኩ ናኒከኒ እስከ አጽናፈ ምድር።በእንተ ርእሱኑ ይነግር በእንተ ሕማማቲሁ እንዘ ይብል ተካፈሉ አልባስየ ለርእሶሙ ወተዐፀዉ ዲበ ዓራዝየ። ወካዕበ ይቤ ቀነዉኒ እደውየ ወእገርየ ወኖለቁ ኵሉ አዕጽምትየ፤ወካዕበመ ይቤ ወወደዩ ሐሞተ ውስተ መብልዕየ፡ ወአስተዩኒ ብሒአ ለጽምእየ። መዝ ፳፩+፲፯

፲፬ በአፈ ኢሳይያስኒ ይቤ ወመጠውኩ ዘባንየ ለመቅሠፍት ወመላትሒየ ለጽፍዓት ወኢሚጥኩ ገጽየ እምኀፍረተ ምራቅ።ዝ ስምዐ ቃሉ ለወልድ በእንተ ርእሱ ወበእንተ አቡሁ ዘተ የድዐ በአፈ ነቢያቲሁ።ወበእንተ መንፈስቅዱስሂ ይነግር እንዘ ይብል መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌየ ዘቀብዐኒ እዜንዎሙ ለነዳያን ፈነወኒ እስብክ ግዕዛነ ለፂውዋን። ዝስ ቃለ ተነብዮ በእንተ መንፈስቅዱስ ዘወረደ ላዕሌሁ በርእየተ ርግብ። ኢሳ፷፩+፩-፫

፲፭ እዜንዎሙ ለነዳያን ፈነወኒ ብሂል ከመ እኩን መምህረ ለአሕዛብ እስመ አሕዛብ በመዋዕለ ትካት ነዳያን እምቃለ እግዚአብሔር ግዱራን እምሕገ ኦሪት። ወእስብክ ግዕዛነ ለፂ ውዋን ብሂለ ለእለ ተጼወው እም አምልኮ እግዚአብሔር ውስተ አምልኮ ጣዖት። ወካዕበመ ይቤ በእንተ መንፈስቅዱስ ላዕለ አግብርትየ ወአእማትየ እሠውጥ እምነ መንፈስየ ዲበ ኵሉ ዘሥጋ ወእሁብ ትእምርተ በሰማይ በላዕሉ ወመ ንክረ በምድር በታሕቱ። ዝኒ ቃለ ተነብዮ ዘኢዩ ኤል በእንተ መንፈስቅዱስ ዘወረደ ላዕለ ሐዋር ያት በጽርሐ ጽዮን ወላዕለ እሙሂ ለኢየሱስ ወላዕለ አንስትኒ እለ ተለዋሁ ወተልእካሁ በንዋ ዮን። ወመንፈስቅዱስ አስተንፈሰ በአፈ ነቢያት ወይቤ አነ አስተባዛኅኩ ራእየ ነቢያት ወበእደ ነቢያት ተመሰልኩ። ኢዩ፪+፳፰

፲፮ ወካዕበ ይቤ እወዲ ሕግየ ውስተ ልቦሙ ወእጽሕፍ ውስተ እንግድዓሆሙ፡ እሙንቱሂ ይከውኑኒ ሕዝብየ ወአነሂ እከው ኖሙ አምላኮሙ። ወካዕበ ይቤ በአፈ ኢሳይያስ ኀበ መኑ አዐርፍዘእንበለ ኀበ የዋህ ወትሑት ወጽምው ዘይርዕድ እምቃልየ። ዘንተ ነገረ በእንተ ርእሱ። ወበእንተ አብኒ ይቤ ኅሥዎ

አሕዛብም ስለርሱ ያደንቃሉ ዳግመኛም እኔ አባቱ እሆንዋለሁ እርሱም ልጄ ይሆነኛል አለ፣ በያዝያንም አፍ ልጄን ከግብጽ ጠራሁት ብሎ እንደተናገረ። ይህ አብ ስለ ልጁ የመሰከረው በነቢያቱ የተነገረ ነው። መዝ፻፱+፫ ሆሴ፲፩+፩

፲፫ ዳግመኛም ወልድ ስለ አባቱ በነቢያቱ አንደበት ተናገረ እለም እግዚአብሔር አለኝ አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወለድሁህ ከእኔ ለምን፡ አሕዛብን ለርስትህ እሰጥሀለሁ፡ ግዛትህም እስከምድር ዳርቻ ይሁን። ስለራሱም ይናገራል ስለመከራው እንዲህ ብሎ ልብሴን ለራሳቸው ተካፈሉ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ አጥንቶ ቼንም ሁሉ ቆጠሩ ሁለተኛም በሆምጣጤ ላይ ሐሞት ቀላቀሉ ለጥሜም መራራውን አጠጡኝ። መዝ ፳፩+፲፯

፲፬ በኢሳይያስ አፍ ጀርባዬን ለግርፋት ሰጠሁ፡ ጉንጮቼንም ለጥፊ፡ ፊቴንም ከምራቅ እፍረት አልመለስሁም አለ። ይህ የወልድ የምስ ክርንት ቃሉ ስለራሱና ስለአባቱ በነቢያቱ አንደ በት የተነገረ ነው።ስለ መንፈስቅዱስም ለድሆች የምስራች እንድነግራቸው የቀባኝ በእኔ ያለ የእግዚአብሔር መንፈስ ለተማረኩት ነፃነትን እን ድሰብክላቸው ላከኝ ብሎ ተናገረ። ይህም የትን ቢት ቃል በርግብ አምሳል በርሱ ላይ ስለወረደ መንፈስቅዱስ ነው። ኢሳ፷፩+፩-፫

፲፭ ለድሆች የምስራች እንድነግራቸው ላከኝ ማለት ለአሕዛብ መምህር እሆን ዘንድ ማለት ነው።በቀደመው ዘመን አሕዛብ ከእግዚ አብሔር ቃል የደኸዩ ለኦሪትም ሕግ መጻ ተኞች ናቸውና።ለምርኮኞች ነፃነትን እሰብክ ዘን ድ ማለት እግዚአብሔርን ከማምለክ ጣዖትን ወደ ማምለክ ለተማረኩት ነው። ዳግመኛም ስለ መንፈስቅዱስ በወንዶች አገልጋዮቼና በሴቶች አገልጋዮቼ ላይ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ ከመን ፈሴ አፈሳለሁ፡ በላይ በሰማይ ምልክት እሰጣለሁ በታች በምድርም ድንቅ የሆነውን።ይህም ኢዩ ኤል የተናገረው የትንቢት ቃል በጽርሐ ጽዮን በሐዋርያት በኢየሱስ እናት ላይ በተከተሉትና በገንዘባቸው ባገለገሉት ሴቶች ላይ ስለ ወረደ ስለ መንፈስቅዱስ ነው፡መንፈስቅዱስም በነቢያት አፍ እኔ የነቢያትን ራእይ አበዛለሁ በነቢያትም እጅ ተመሰለሁ ብሎ ተናገረ። ኢዩ፪+፳፰

፲፮ ዳግመኛም ሕጌን በልባቸው አኖራለሁ በደረታቸውም እጽፈዋለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ እኔም አምላካቸው እሆናለሁ አለ። ሁለተኛም በኢሳይያስ አፍ ወደ ገርና ትሑት ጭምትም ወደ ሆነው ከቃሌም የተነሣ ወደሚን ቀጠቀጠው ካልሆነ በቀር በማን ላይ አርፋለሁ አለ፤ይህንንስ ነገር ስለራሱ ተናገረ ስለአብም

ለእግዚአብሔር ወእምከመ ረከብክሙዎ ጸውዕዎ ወእምከመ ቀረብክሙ ኀቤሁ ይኅድግ ኃጥእ ፍኖቶ ወብእሲ ዐማፂ ምግባሮ። ወካዕበ ይቤ ፍርሁዎ ለእግዚአብሔር ኵልክሙ ቅዱሳኒሁ እስመ አልቦሙ ተጽናስ ለእለ ይፈርህዎ። ኢሳ፶፭+፮

እግዚአብሔርን ፈልጉት ካገኛችሁትም ጥሩት ወደ ርሱም ከቀረባችሁ ኃጢአተኛው መንገዱን ይተው አመፀኛውም ሰው ምክሩን ይተው አለ። ሁለተኛም ቅዱሳኑ ሁላችሁ እግዚአብሔርን ፍሩት የሚፈሩት ችግር የለባቸውምና አለ። ኢሳ፶፭+፮

፲፯ ወበእንተ ወልድኒ ይቤ ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር። ወካዕበ ይቤ እግዚአብሔርሰ እምቴማን ይመጽእ ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን። ከደነ ሰማያተ ሥኑ ወመልዐ ምድረ ስብሐቲሁ። ወካዕበ ይቤ ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር። ወከመ ነጠብጣብ ዘያንጠበጥብ ዲበ ምድር። ወበአፈ ኢሳይያስኒ ይቤ መጽአ ይጠባሕ ከመ በግዕ ወከመ በግዕ ዘኢይነብብ በቅድመ ዘይቀርፆ ከማሁ ኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ እስመ ይነሥእዋ ለፍትሑ ወኢየአምርዋ ለልደቱ በኃጢአተ ሕዝብየ በጽሐ እስከ ለሞት፡ ወበእንተ ትንሣኤሁኒ ይቤ ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃህ እምንዋም ወከመ ኃያል ዘኅዳገ ወይን። ወበእንተ ዕርገቱኒ ይቤ ተለዐለ ዘይኳንኖ ለምድር።ናሁኬ አስተንፈሰ ሥላሴ በአፈ ነቢያቲሁ እንዘ ያርኢ ፍናወ ነገር በበህላዌሁ። መዝ፻፲፯+፳፮፣፷፯+፳፩ ኢሳ፶፫+፯ ዕን፫+፫

፲፯ ስለ ወልድ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው አለ፣ ሁለተኛም እግዚአብሔር ከቴማን ይመጣል ቅዱሱም ከፋራን ተራሮች፣ ክብሩ ሰማያትን ከደነ ምስጋናውም ምድርን መላ አለ።ዳግመኛም እንደ ጠል በፀምር ላይ በምድርም ላይ እንደሚንጠባጠብ ነጠብጣብ ወረደ። በኢሳይያስም አፍ እንደ በግ ሲታረድ መጣ በመከራው ሰዓት በሸላቹ ፊት እንደማይናገር በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም ፍርዱን ይወስዷታልና ልደቱንም አያውቋትምና በሕዝቤ ኃጢአት እስከሞት ደረሰ አለ። ስለትንሣኤውም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ የወይን ስካርም እንደ ተወው ብርቱ ሰው እግዚአብሔር ተነሣ አለ፡ ስለ ዕርገቱም አለ ምድርን የሚገዛት ከፍ ከፍ አለ።። እነሆ ሦስትነቱን በየህልውናው የነገር መንገድ እያሳየ በነቢያቱ አፍ ተናገረ። መዝ፻፲፯+፳፮፣ ፷፯+፳፩ ኢሳ፶፫+፯ ዕን፫+፫

፲፰ ተኀፈርኬ ኦ አቡርዮስ ዘትቤ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ዘዘዚአሁ። ስማዕኬ ኦ ድንቅው እንዘ ብከ እዝነ ዘይቤ እግዚእነ በወንጌል ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአቡየ። ናሁኬ ፩ ራእይ። ወካዕበሰ ይቤ አነ ወአብ ፩ ንሕነ። ናሁኬ ፩ ህላዌ።ወካዕበሰ ይቤ በከመ አብ ሕያው አነኒ ሕያው በእንተ አብ። ነዋኬ ፩ ሕይወት። ወዓዲ ይቤ እመቦ ዘሰአልክሙዎ ለአብ በስምየ ይገብር ለክሙ ከመ ይሰባሕ አብ በወልዱ። ወእመኒ ሰአልክሙኒ በስመ አቡየ እገብር ለክሙ።ናሁኬ ፩ ሥምረት። ወዓዲሰ ይቤ አነኒ አቡክሙ ወአቡየኒ አቡክሙ። ወበእንተ መንፈስቅዱስኒ ይቤ ዘኢተወልደ እማይ ወእመንፈስ ኢይክል በዊአ ውስተ መንግሥተ ሰማያት። ናሁኬ ፩ ወሊድ። ዮሐ፫+፬ ፣ ፮+፶፯ ፣ ፲፬+፱

፲፰ አብና ወልድ መንፈስቅዱስም ለየራሳቸው ናቸው የምትል አቡርዮስ ሆይ እፈር፣ ጆሮ ሳለህ የደንቆርህ ሆይ ጌታችን በወንጌል እኔን ያየ አባቴን አይቷል ያለውን ስማ እነሆ እንደ ኅብረ መልክእ ናቸው። ሁለተኛም እኔና አብ አንድ ነን አለ አንድ ህልውና እነሆ፡. ሁለተኛም አብ ሕያው እንደሆነ እኔም ስለ አብ ሕያው ነኝ አለ፡ አንድ ሕይወት ይኸዋ ! ዳግመኛም አብን በስሜ የምትለምኑት ቢኖር አብ በልጁ እንዲመሰገን እርሱ ያደርግላችኋል። በአባቴም ስም ብትለምኑኝ አደርግላችኋለሁ አለ እነሆ አንድ ፈቃድ። ዳግመኛም እኔም አባታችሁ ነኝ አለ። ስለመንፈስቅዱስም ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ወደ መንግሥተሰማያት መግባት አይችልም አለ፡ እነሆ አንድ መውለድ። ዮሐ፫+፬፣ ፮+፶፯፣፲፬+፱

፲፱ ወዓዲሰ ይቤ ወበከመ አብ ያነሥኦሙ ለምውታን ወያሐየውሙ ወከማሁ ወልድኒ ያሐዩ ለዘፈቀደ። ናሁኬ ፩ ሥልጣን። ዓዲሰ ይቤ ወኵሉ ዘቦ ለአቡየ ዚአየ ውእቱ። ወለአቡሁኒ ይቤሎ ወኵሉ ዘዚአየ ዚአከ ውእቱ ወዘዚአከኒ ዚአየ። ናሁኬ ፩ እግዚእ። ወዓዲሰ ይቤ ወበከመ የአምረኒ አብ አነኒ አአምሮ ለአብ ። ናሁኬ ፩ አእምሮ። ወዓዲሰ ይቤ ወአልቦ ዘይክል መጺአ ኀቤየ እመ ኢሰሐቦ አቡየ ዘፈነወኒ። ወበካልዕኒ ገጽ ይብል ወአልቦ ዘይክል መጺአ ኀበ አብ ዘእንበለ እንተ ኀቤየ። ናሁኬ ፩ ጸውዖ።ወካዕበ ይቤሎሙ ለአይሁድ ኢኪያየ

፲፱ ዳግመኛም አብ ሙታንን እንደሚያስነሣቸው ሕይወትንም እንደሚሰጣቸው እንዲሁ ወልድም ለወደደው ሕይወትን ይሰጣል አንድ ሥልጣን እነሆ።ሁለተኛም ለአባቴ ያለው ሁሉ የእኔ ነው አለ።አባቱንም የእኔ የሆነው ሁሉ ያንተ ነው የአንተም የሆነው የእኔ ነው አለው፣ አንድ ጌትነት እነሆ ! ዳግመኛም አብ እንደሚያውቀኝ እኔም አብን ዐውቀዋለሁ አለ፡ እነሆ አንድ ዕውቀት።ዳግመኛም የላከኝ አብ ካልሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም።በሌላም ሥፍራ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ መምጣት የሚቻለው የለም አለ፡ እነሆ

ተአምሩ ወኢአቡየ ሶበሰ ኪያየ አእመርክሙኒ እምአእመርክሞሂ ለአቡየ፡ ናሁኬ ፩ አዕቆ። ዮሐ፰+፳፩ ፲፭+፶፮ ፲፯+፲፭

፳ ወዓዲመ ይቤ ዘተወክፈ ለዘፈነወኒ ኪያየ ተወክፈ ወዘኪያየ ተወክፈ ተወክፈ ለዘፈነወኒ ። ናሁኬ ፩ ተወክፎ፡ ወዓዲመ ይቤ አመ ተሰዐሰ ወልደ እጓለ እመሕያው ውእተ አሚረ አሜሃ ተአምሩ ከመ አነ ውእቱ አኮ ዘእምኅቤየ ዘእነግር በከመ መሀረኒ አብ ከማሁ እነግር ወአብል ዘፈነወኒ ሀሉ ምስሌየ ኢየኅድገኒ ባሕቲትየ እስመ አነ ሥምሪቶ እገብር። ናሁኬ ፩ ትምህርት።

፳፩ ወካዕበሰ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ውእተ አሚረ ተአምሩ ከመ አነ በአብ ወአብ ብየ ወአንትሙኒ ብየ ወአነኒ ብክሙ። ናሁኬ ፩ ትብሬ።ወካዕበ ይቤ እንዘ ያስተበቍዕ ኀበ አቡሁ በእንተ አርዳኢሁ በከመ አንተ አብ ምስሌየ ብየ ወአነኒ ምስሌከ ብከ ወከመ ይኩኑ እሙንቱኒ ፩ ብነ ከማነ ከመ ይእመን ዓለም ከመ አንተ ፈነውከኒ። ናሁኬ ፩ ድማሬ። ወካዕበ ይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ዘኪያክሙ ሰምዐ ኪያየ ሰምዐ ወዘ ኪያየ ሰምዐ ሰም? ለዘፈነወኒ። ናሁኬ ፩ አእምሮ። ማቴ፲+፵ ዮሐ፲፯+፳፱

፳፪ እንከሰ ፈጸምነ በእንተ ጽምረተ አብ ወወልድ። ወበእንተ መንፈስቅዱስኒ ንነግር በከመ አሰንበለ ወአስተአኀዘ ወልደ እግዚአብሔር ህላዌ ዚአሁ ምስለ አቡሁ ከማሁ አሰንበሰ ወአስተአኀዘ ጳውሎስ ህላዌ መንፈስቅዱስ ምስለ አብ ወወልድ፡ ሶማዕ ዘይቤ በመልእክቱ ወአልቦ ዘየአምር ኀሊናሁ ለብእሲ ዘእንበለ መንፈሱ ለብእሲ ዘሀሎሉሁ ወለነሰኒ ኀሊናሁ ለእግዚ አብሔር ብነ ዘይከሥት ኅቡኣቲሁ ይፈትን ማዕምቅቲሁ፡ እስመ ኀሊናሁ ለእግዚአብሔር ብሂል ማእምረ ኅቡኣቲሁ ብሂል፡ እስመ ኢሀሉ ኀሊና ባዕለ አብ ዘኢሀሉ ባዕለ ወልድ ወኢሀሉ ኀሊና ባዕለ ወልድ ዘኢሀሉ ባዕለ መንፈስቅዱስ እስመ ፩ ይኄልዩ ወአሐቲ መለኮቶሙ። ዮሐ፲፯+፳፪ ፩ቆር፪+፲፮

፳፫ ወካዕበ ይቤ ጳውሎስ ወአልቦ ዘይክል ብሂለ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘእንበለ በመንፈስቅዱስ፤ ወአልቦ ዘይብል ውጉዝ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘእንበለ በቤልሆር ።ወመክፈልታተ ሱታፌ ጸጋ ህልው ለዝንቱ ፩ መንፈስቅዱስ ወመክፈልታተ ሱታፌ ተልእኮ ህልው ለዝንቱ ፩ እግዚእ፤ወመክፈልታተ ሱታፌ ምግባረ ሠናይ ህልው ለዝንቱ አምላክ ዘይገብር ኵሎ ውስተ ኵሉ እስመ ለለዘዚአሁ ጸጋሁ በመንፈስ ቅዱስ።ወእግዚእነኒ ይቤ በወንጌል ውብየ ብዙኀ

አንድ መጥራት! ሁለተኛም አይሁድን እኔን ዐታ ውቁኝም አባቴንም ዐታውቁም እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ባወቃችሁት ነበር አለ እነሆ አንድ ማሳወቅ! ዮሐ፰+፳፩ ፲፭+፶፮ ፲፯+፲፭

፳ ሁለተኛም እኔ የላክሁትን የተቀ በለው እኔን ተቀበለ እኔንም የተቀበለ የላከኝን ተቀበለው አለ እነሆ አንድ መቀበል! ዳግመኛም የሰው ልጅ ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ ያን ጊዜ እኔ እንደሆንሁ ታውቃላችሁ ከራሴ አንቅቼ አልና ገርም አብ እንዳስተማረኝ እንዲሁ አስተምራለሁ፡ የላከኝ ከእኔ ጋር አለ አብ ብቻዬን አይተወኝም እኔ ፈቃዱን አደርጋለሁና አለ፡ አንድ ትምህርት እነሆ !

፳፩ ሁለተኛም ደቀመዛሙርቱን ያን ጊዜ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እና ንተም በእኔ እኔም በእናንተ እንዳለሁ ታውቃላ ችሁ አላቸው፡ እነሆ አንድ መወሀድ! ዳግመኛም ስለደቀመዛሙርቱ እየማለደ አንተ አባቴ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ እንዳለሁ እነርሱም እን ደኛ በእኛ አንድ ይሁኑ አንተ እንደላክኸኝ ዓለም ሁሉ ያምን ዘንድ አለ፡ አንድ አንድነት እነሆ ! ሁለተኛም ደቀመዛሙርቱን እናንተን የሰማ እኔን ሰማ እኔንም የሰማ የላከኝን ሰማው፡አላቸው እነሆ አንድ ማሳመን ! ማቴ፲+፵ ዮሐ፲፯+፳፱

፳፪ እንግዲህስ ስለ አብና ስለ ወልድ አንድ መሆን ፈጽመን፡፡ስለመንፈስቅዱስም ይናገ ራል የእግዚአብሔር ልጅ የርሱን ህልውና ከአባቱ ጋር ፈጽሞ እንዳያያዘ እንዲሁ ጳውሎስ የመንፈስቅዱስን ህልውና ከአብና ከወልድ ጋር ፈጽሞ አያይዞታል። በመልእክቱ በላዩ ላይ ካደረ የሰው መንፈሱ በቀር የሰውን አሳቡን የሚያውቅ የለም።ለእኛ ግን የተሠወረውን የሚገልጥ የተሸ ሸገውንም የሚመረምር የእግዚአብሔር መንፈስ አለን ያለውን ሰማ።የእግዚአብሔር ኀሊና ማለት የተሠወረውን የሚያውቅ ማለት ነው።በወልድ የሌለው ኀሊና በአብ ላይ የለምና። በመንፈስ ቅዱስም ዘንድ የሌለ ኀሊና በወልድ የለምና በአንድነት ያስባሉና መለኮታቸውም አንዲት ናትና። ዮሐ፲፯+፳፪ ፩ቆር፪+፲፮

፳፫ ዳግመኛም ጳውሎስ በመንፈስቅዱስ ካልሆነ በቀር ኢየሱስ ክርስቶስ ማለትን የሚችል የለም አለ። በብዔል ዜቡል ካለሆነም በቀር ኢየሱስ ክርስቶስን ውጉዝ የሚል የለም የጸጋ ድርሻ እድል ፈንታ ለዚህ አንድ መንፈስቅዱስ አለው። የማገለገልም ድርሻ እድል ፈንታ ለዚህ አንድ ጌታ አለው። የበጎ ሥራም ድርሻ እድል ፈንታ ለዚህ በሁሉ ዘንድ ሁሉን የሚያደርግ አምላክ አለው። ለእያንዳንዱ ጸጋው የተለያየ ነውና። ጌታም በወንጌል የምነገራችሁ ብዙ ነገር

ነገር ዘእነግረክሙ ወባሕቱ ኢትክሉ ጸዊሮቶ
ይእዜ።ወመጺኦ ወእቱ መንፈሰ ጽድቅ ይመር
ሐክሙ በኵሉ ጽድቅ እስመ ኢይነግር ዘእምነ
ቤሁ ወዘሰምዐ ዳዕሙ ይነግር ወዘይመጽእ ይነ
ግረክሙ ወይዜንወክሙ ውእቱ። ኪያየ ይዌድስ
ውእቱ ወይሴብሖ እስመ እምዚአየ ይነሥእ
ወይ ነግረክሙ ወይዜንወክሙ ኵሉ።
ዮሐ፲፮፥፲፪

፳፬ አእምርኬ ኦ አብድ ሶበ ይብል እምዚ
አየ ይነሥእ ወያዜክረክሙ ኵሉ ያኤምረክሙ
ከመ ቃለ ወልድ ቃለ ትምህርቱ ለጰራቅሊጦስ።
በእንተ አቡሁሰ ይቤ ኵሉ ዘሰማዕኩ በኀበ አብ
እነግር። ወበእንተ መንፈስቅዱስኒ ይቤ ዘእም
ዚአየ ይነሥእ ወያዜክረክሙ ኵሉ። ናሁኬ
ጽምረተ ሥላሴ በአሐቲ ሥርዓት ወአልቦ ተፍላ
ጠ ኀበ ኀልዮ ወነቢብ ወአልቦ ተውላጠ ኀበ
ግጻዌ ወጸዳል። እመንኬ ኦ ረሲዕ ከመ ኢህሉ
ዕበይ ላዕለ አብ ዘኢህሉ ላዕለ ወልድ ወኢህሉ
ዕበይ ላዕለ ወልድ ዘኢህሉ ላዕለ መንፈስቅዱስ።

፳፭ ዝክረ ሃይማኖቶሙ ለረሲዓን ሰቆራር
በኀበ እግዚአብሔር ወቃለ አፉሆሙ ዘምሉዕ
ጽርፈተ ያረኵሳ ለጥምቀቶሙ ድምፀ ትምህር
ቶሙ የሀውካ ለቤተክርስቲያን ወነሰላወ እገሪ
ሆሙ ያረኵሳ ለምድር።

፳፮ ሰብልያኖስ ቶስሐ ግጻዌ መለኮት
ወአቡርዮስ ዘረወ ጽምረተ ሥላሴ ክልዔሆሙ
ደቂቀ ገሃነም ኮኑ ምጥዋነ ለመንጸፈ ደይን።
ወለዘሂ የአምን በሃይማኖቶሙ ኢታብኦ ውስተ
ቤትከ ወበሐዊ ጥቀ ኢትበሎ። ኢትንበር ደወለ
ቀልቀል ምስለ ጸላዒከ ከመ ኢያጽድፍከ ወኢ
ትባእ ውስተ ዐዘቃተ ዓም ዓም ከመ ኢያሐ
ጥከ።ኢትትዐረኮ ለተኵላ ከመ ኢይሐጥከ ወኢት
ቅንት ከይሴ ውስተ ሐቌከ ከመ ኢያሕስም
ላዕሌከ። ኢትዕንቆ ለአፍዖት ውስተ ክሳድከ ከመ
ኢያሕምምከ በሕምዙ።ወኢትደዮ ውስተ ሕፅንከ
ለአቅራብ ከመ ኢያመምትከ በዘነቡ። ኢትሀብ
ቅድሳተ ለከለባት ወኢትደይ ባሕርየከ ቅድመ
አሕርው። ወእመ ብከ ልብስ ንጹሕ ኢታቅርቦ
ኀበ ጸለሎ መቅጹት ከመ ኢይደይ ውስቴቱ
ጽልመቶ።ወለእመ አጥረይከ ዕንቌ ክቡረ ኢት
ዝግቦ ውስተ መሬት ከመ ኢያደምኖ በርስሐቱ።
ማቴ፯፥፮

፳፯ መሰልነ ለከ ዘንተ ምዕዳነ በእንተ
ተራሕቆ እምዕልዋን እስመ ፍትሐ ኵነኔ ወጽአ
ላዕሌሆሙ እምኀበ እግዚአብሔር በከመ ጽሑፍ
ውስተ መጽሐፈ ኦሪት።ወወጽአ ወልደ ብእሲት
እስራኤላዊት ወአቡሁሰ ግብጻዊ ወሰመየ ስሞ
ለእግዚአብሔር ወልዳ ለእንታክቲ ብእሲት
እስራኤላዊት ወረገመ ወአምጽእዎ ኀበ ሙሴ፣
ወስማ ለእሙ ሰሎሚት ወለተ ዳቤር ዘእምነገደ
ዳን ወወደዮ ውስተ ሞቅሕ እስከ ይኳንኖ በትእ

እለኝ ነገር ግን ዛሬ ልትሸከሙት አትችሉም ።
የእውነት መንፈስ መጥቶ እርሱ በጽድቅ ሁሉ
ይመራችኋል ከራሱ የሆነውን አይነግራችሁምና
የሰማውን ይናገራል እንጂ የሚመጣውንም
ፈጽሞ ይነግራችኋል እኔንም ያከብረኛል ከእኔ
ተቀብሎ ይነግራችኋልና ሁሉንም ይገልጥላች
ኋልና። ዮሐ፲፮፥፲፪

፳፬ አንተ ሰነፍ ዕወቅ ከእኔ ተቀብሎ ሁሉን
ይነግራችኋል ባለ ጊዜ የወልድ ቃል የጰራ
ቅሊጦስ የትምህርቱ ቃል እንደሆነ ያመለክ
ታል።ስለአባቱም በአባቴ ዘንድ የሰማሁትን ሁሉ
አለ፣ስለ መንፈሱም ከእኔ ተቀብሎ ይነግራችኋል
ሁሉንም ያሳስባችኋል አለ።እነሆ የሥላሴ አን
ድነት በአንዲት ሥርዓት ነው በማሰብና በመ
ናገር መለያየት የለም በመልክና በብርሃን መለዋ
ወጥ የለም ዝንጉ ሆይ በወልድ ዘንድ የሌለ ጌት
ነት በአብ ዘንድ እንደሌለ በመንፈስቅዱስም ዘን
ድ የሌለ ጌትነት በወልድ ዘንድ እንደሌለ ዕወቅ።

፳፭ የዝንጉዎች የሃይኖታቸው መታሰቢያ
በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው፡ ስድብን
የተመላ የአንደበታቸውም ቃል ጥምቀታቸውን
ያረክሳታል የትምህርታቸው ድምፅ ቤተ
ክርስቲያንን ያውካታል። የእግራቸውም መመላ
ለስ ምድርን ያረክሳታል።

፳፮ ሰብልያኖስ የመለኮትን አካል ቀላቀለ
አቡርዮስም የሥላሴን አንድነት በተነ ሁለቱም
የገሃነም ልጆች የፍዳን ቦታ የተቀበሏት ሆኑ፡
በሃይማኖታቸውም የሚያምነውን ወደ ቤትህ
አታስገባው ፈጽመህም ሰላም አትበለው።
እንዳይገፈትርህ ወደ ገደልም እንዳትገባ ረግረ
ግም እንዳይውጥህ ከጠላትህ ጋር አፋፍ ላይ
አትቀመጥ።እንዳያስትህ ተኵላን ጓደኛህ አታድ
ርገው። ክፉ እንዳያደርግብህ እባብን በወገብህ
አትታጠቅ፡ በመርዙም እንዳይጐዳህ እፉኝትን
በአንገተህ አትሠር በጅራቱ አካልህን እንዳያጕ
ድል ጊንጡን በእቅፍህ አታኑር፡ የተቀደሰውን
ለውሾች አትስጥ ዕንቍን በእሪያዎች ፊት
አታኑር። ንጹህ ልብስ ቢኖርህ ጥላሸቱን በላዩ
እንዳያኖርብህ ወደ ማሰሮ ጥቀርሻ አታቅርበው።
የከበረ ዕንቍ ብትገዛ በእድፉ እንዳያዝግብህ
መሬት ውስጥ አትቅበረው። ማቴ፯፥፮

፳፯ ከኃጢአተኞች ስለመራቅ ይህን
ምክር በምሳሌ አቀረብንልህ። የፍዳ ፍርድ
ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቶባቸዋልና በኦሪት
መጽሐፍ የእስራኤላዊት ሴት ልጅ ወጣ አባቱም
ግብጻዊ ነበር፣ የዚያች እስራኤላዊት ሴት ልጅ
የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ተራገመ፣ ወደ
ሙሴም አመጡት የእናቱም ስም ከዳን ወገን
የሆነ የዳቤር ልጅ ሰሎሚት ናት፣በእግዚአብሔር
ትእዛዝ እስኪቀጣው ድረስ አሠረው። እግዚአ

ዛዘ እግዚአብሔር፡፡ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ አውፅኦ ለዘረገመ አፍአ እምትእይንት ወይደዩ እደዊሆሙ ላዕለ ርእሱ ኵሎሙ እለ ሰምዕዎ ወይገርዎ በእብን ኵሉ ተዓይን ፡፡ ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ወአውፅእዎ ለዘጸረፈ አፍአ እምትዕይንት ወወገርዎ በእብን ወሞተ በትእዛዘ አምላክ ያዕቆበ፡፡

፳፰ ወእግዚእነሂ ይቤ በወንጌል ይኄይሶ ይእስሩ በክሳዱ ማሕረፀ አድግ ወያስጥምዎ ውስተ ልጐተ ቀላየ ባሕር፡፡ናሁኬ ትእዛዘ ሞት ወፅአ ላዕለ ዕልዋነ ሃይማኖት በብሉይኒ ወበሐዲስኒ፡፡ወበነቢይኒ ይነግር በእንተ ቅንዐተ ሃይማኖት ወይቤ ማሕረስክሙኒ አንህቡ ለመጥባሕት ወማዕፆዕክሙኒ አግብሩ ረምሐ የዋህኒ ለይኩን መስተባእሰ ድኩምኒ ለይበል ፅኑዕ አነ፡፡ ኢሳ፱÷፬

፳፱ ዳዊትኒ ይቤ አኮኑ ጸላዕተከ ጸላዕኩ እግዚኦ ወተመንሰውኩ በእንተ ፀርከ፡፡ ፍጹመ ጽልዐ ጸላዕክዎሙ ወኮኑኒ ፀርየ፡፡ ወጴጥሮስኒ ርእሰ ሐዋርያት ይቤሎ ለቀሌምንጦስ ተቃተል በሰይፈ ሐጺን ከሐድያነ ወዕልዋነ እለ ኢየአምኑ በክርስቶስ ወምላሕ ሰይፈከ በእንተ ሃይማኖት ፍጽምት፡፡ወካዕበመ ይቤ ሰሎሞን ቅትል ረሲዓነ በቅድመ ንጉሥ ወይኩን ንጹሐ መንበሩ፡፡ መዝ ፻፴፰÷፳፩ ምሳ፳፭÷፭

፴ መንኬ ረሲዕ ዘእንበለ ዳዕሙ ዕልዋነ ሃይማኖት እለ ረስዑ አምልኮ እግዚአብሔር ዘተወፈዩ እምሐዋርያት፡፡ ወለንጉሥኒ ኢይደልዎ ትዕግሥት በእንተ ቅንዐተ ሃይማኖት፡፡ ቈስጠንጢኖስ ተወደሰ በእንተ ስደቱ ለአርዮስ ወበእንተ ጉባኤሆሙ ለማኅበረ ኒቂያ ዘውእቶሙ ፫፻፲ወ፰ እስከ ክብረ ክርስቶስ ማዕከሌሆሙ እንዘ ኢየአምርዎ ከመ ፩ እምኔሆሙ፡፡

፴፩ አቀመ ለርእሱ ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ ዝክረ ውዳሴ ለትውልደ ትውልድ እስመ በመዋዕሊሁ ሥርዓተ ሃይማኖት ረትዐት ወበመዋዕሊሁ አስተርአየ መስቀለ ክርስቶስ ዝሕነ ማዕበለ ዕልዋን ወነድአ ትንግሌ መዋግድ ዘመናፍቃን መቀመ ርቱዐ ሠርዌ ሐመረ ቤተክርስቲያን፡፡ አንፈርዐፁ ናሉተ አጣንዕ ዘውእቶሙ ኤጲስቆጶሳት እለ ተቀደሱ በእስትንፋሰ አፉሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡፡

፴፪ በከመ ኮነት ውድስት መንግሥተ ቈስጠንጢኖስ በእንተ ሥርዓተ ማኅበር ዘኮነ በመዋዕሊሁ ወኮነት ዝልፍተ መንግሥተ መርቅያን ንጉሠ ሮሜ ዘአፍቀረ ሃይማኖተ ንስጥሮስ እንተ ወጠንዋ ታስሮስ ወዲድሮስ ወከልዐ እግዚአብሔር አቅሞታ ለይእቲ ሃይማኖት በአስተፋጥና ሞቱ ለንስጥሮስ፡፡

ብሔርም ሙሴን አለው የተራገመውን ሰው ከከተማ ወደ ወጪ አውጣው የሰሙትም ሁላቸው እጃቸውን በራሱ ላይ ይጫኑ የተሰበሰቡትም ሁሉ በደንጊያ ይውገሩት፡፡ሙሴም ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው የተሳደበውንም ሰው ከከተማ ወደ ውጭ አውጥተው በደንጊያ ወገሩት በያዕቆብም አምላክ ትእዛዝ ሞተ ተብሎ እንደ ተጻፈ፡፡

፳፰ ጌታችንም በወንጌል በአንገቱ የወፍጮ ደንጊያ አሥረው ወደጥልቁ ያስጥሙት አለ እነሆ ሃይማኖትን በካዱት ላይ በብሉይም በሐዲስም የሞት ትእዛዝ ወጣ በነቢይም ስለ ሃይማኖት ቅናት ማረሻችሁን ጐራዴ አሠሩት ማጭዳችሁንም ጦር አድርጋችሁ አሠሩት ገራገሩ ጠበኛ ይሁን ደካማውም እኔ ብርቱ ነኝ ይበል ብሎ ተናገረ፡፡ኢሳ፱÷፬

፳፱ ዳዊትም አቤቱ ጠላቶችህን ጠላሁ ስለጠላትህም ማሰንሁ ፈጽሞ መጥላትን ጠላኋቸው ጠላቶቼም ሆኑኝ አለ፡፡ የሐዋርያት አለቃ ጴጥሮስም ቀሌምንጦስን ፍጽምት ስለምትሆን ሃይማኖት ሰይፍህን መዝዘህ በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑትን ከሀዲዎችንና ጨካኞች በብረት ሰይፍ ተዋጋ አለው፡፡ ሁለተኛም ሰሎሞን ዝንጉዎችን ከንጉሥ ፊት አርቅ ዙፋኑም ንጹህ ይሆናል አለ፡፡ መዝ ፻፴፰÷፳፩ ምሳ፳፭÷፭

፴ ከሐዋርያት የተቀበሉትን አምልኮ እግዚአብሔር የረሱ ሃይማኖትን የካዱ ካልሆኑ በቀር ዝንጉ ማነው፤ ለንጉሥም ስለሃይማኖት ቅናት መታገሥ አይገባውም በአርዮስ መሰደድ ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንት ስለሆኑ የኒቅያ ማኅበረተኞች ጉባኤያቸው ቈስጠንጢኖስ ተመሰገነ ከእርሱ እንደ አንዱ ሆኖ ሳያውቁት ክርስቶስ በመካከላቸው ተገኝቷልና፡፡

፴፩ ቈስጠንጢኖስ ለልጅ ልጅ የሚሆን የምስጋና መታሰቢያ ለራሱ አቆመ፡፡ በዘመኑ የቀናች ሃይማኖት ተሠርታለችና በዘመኑም የክርስቶስ መስቀል ተገልጦ የከሀዲዎች ማዕበል ቆሟልና የመናፍቃንም ሞገድ መነሣት ጸጥ ብሏልና የቤተክርስቲያንም የመርከቧ አለቃ በእውነት ቆሟልና፡፡ እነሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንፋሽ የተቀደሱ ኤጲስቆጶሳት ናቸው፡፡

፴፪ በዘመኑ ስለተደረገ የማኅበር ሥርዓት የቈስጠንናስ መንግሥት የተወደሰች እንደሆነች ታስሮስና ዲድሮስ የወጠኑአትን የንስጥሮስን ሃይማኖት የወደደ የሮም ንጉሥ የመርቅያን መንግሥት የተወቀሰች ሆነች፡ እግዚአብሔርም የንስጥሮስን ሞት በማፋጠን የዚያችን ሃይማኖት መጽናት ከለከለው፡፡

፴፫ ወእምዝ ተመይጠ ኀበ ሃይማኖተ ልዮን ወአቀመ ላቲ ሰይእቲ ሃይማኖት ኤጲስ ቆጶሳተ ፪፻፴ወ፮ እንዘ ይጌሊ በልቡ ከመ ትኩን ካዕበተ እማኅበረ ኒቅያ።ወበዝንቱ ቈናጽል ወው ጎደት ሃይማኖት በዝንቱ ተኳሉት ወተዘርዉ አባግዐ ምሥጢር። በዝንቱ ሰባክያነ ሐሰት ወተግ ሕሰ እምኀብረቶሙ ጸጋ መንፈስቅዱስ ምስለ ዲዮስቆርስ ቀናዒ በእንተ ሃይማኖት ዘተመልሐ ጥረሲሁ ወተነጽየ መብዝኀተ ጽሕሙ።

፴፬ ዘለፋሁ ለመርቅያን ናሁ እንከ ይእዜ በኀበ መሀይምናን በእንተ ሃይማኖቱ ጽይዕት ወበእንተ እምነቱ ርኩስት እስመ ዝክረ ረሲዓን ለዓለም ይሄሉ ዘምስለ ዘለፋ ወጽዕለት። ናሁ ካዕበ ዝክረ ሃይማኖቱ ለቈስጠንጢኖስ ነያ እስከ ዮም ዘምስለ ውዳሴ ወስብሐት፡ እስመ ዝክረ ጻድቅ ካዕበ ለዓለመ ዓለም ይሄሉ ዘምስለ እእኩቶ ወእስተብጽዖ ወወድሶ።

፴፭ ወእምዝ ሠርዑ ማኅበረ ቅዱሳን እለ በኒቅያ ሃይማኖተ ርትዕተ ለኵሉ ሕዝበ ክርስቲያን፡ ከመዝ ገብሩ ወይቤሉ እምኀበ ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ ግሩም ረከብነ መባሕተ ከመ ናስተናሥእ ወናጽንዓ ለቤተክርስቲያን በሃይማኖተ ኢየሱስ ክርስቶስ። ወለዘዐለወ ዘንተ ይትኀበዮ ሰይፍ፡ አሜን፡ ወአሜን።

፴፮ ተፈጸመት ዛቲ ድርሳን እንተ ተጽሕ ፈት ለዘለፋ አቡርዮስ ረድአ ሰይጣን አጽሐፍክዋ አነ ጊዮርጊስ ምስኪን ወበእንበይነ ኃጢአትየ ምኑን ወበእንበይነ እምነትየ ዘእም ሕዝበ ናዝራውያን ወእንበይነ ጥምቀትየ ወልደ ሐዋ ርያት ዐቢየ ክርስቲያን ቅኑት በኃይለ ሃይማኖት ውኑቱም በቅብዐ በለሳን። ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ለዓለመ ዓለም አሜን።

.......... /// ..........

፴፫ ከዚያም በኋላ ወደ ልዮን ሃይማኖት ተመለሰ ለዚያችም ሃይማኖት የኒቅያ ማኅበር እጥፍ እንድትሆን በልቡ አስቦ ፪፻፴፮ ኤጲስ ቆጶሳትን አቆመላት፣ቀበሮዎች በዙ ሃይማኖትም ጉደለች ተኩላዎች በዙ የምሥጢር በጎችም ተበ ተኑ ሐሰትን የሚያስተምሩ በዙ፣ከጉባኤያቸውም የመንፈስቅዱስ ጸጋ ተለየ ስለ ሃይማኖት ቀንቶ ጥርሱን ከተነቀለ የጺሙም ብዙው ከተነጨ ከዲዮስቆሮስ ጋር ሆነ።

፴፬ የመርቅያን ወቀሳ እነሆ በምእመናን ዘንድ እስካሁን ድረስ ስለተበላሸ ሃይማኖቱ ስለ ረከሰችም እምነቱ። የዝንጉዎች መታሰቢያ ለዘ ላለም ከወቀሳና ከስድብ ጋር ይኖራልና። እነሆ ሁለተኛ የቈስጠንጢኖስ የሃይማኖቱ መታሰቢያ እነኋት እስከዛሬ ድረስ ከፍጹም ምስጋና ጋር ትኖራለች የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ከማመ ስገንና ከማድነቅ ከማክበርም ጋር ይኖራልና።

፴፭ ዚህም በኋላ በኒቅያ የነበሩ የቅዱሳን ማኅበረተኞች ለክርስቲያን ወገን ሁሉ የቀናች ሃይማኖትን ሠሩ እንደዚህ አንድ ሆነው ከተወ ደደ ንጉሥ ከቈስጠንጢኖስ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት ቤተክርስቲያንን እንድናነሣት እንድናጸናትም ሥልጣንን አገኘን ይህንንም የተላለፈ ሰይፍ ይለፍበት። አሜን፡ ወአሜን።

፴፮ የሰይጣን ደቀመዝሙር አቡርዮስን ለመውቀስ የተጻፈች ድርሳን ተፈጸመች ስለ ኃጢአቴ የተናቅሁ ስለእምነቴ ግን ከናዝራውያን ወገን ስለጥምቀቴም የክርስቲያን ታላላቆች የሐዋርያት ልጅ የሆንሁ በሃይማኖት ዝናር የታጠቅሁ በሜሮን ቅባት የታተምሁ እኔ ምስኪን ጊዮርጊስ አጻፍሁአት። ለአብና ለወልድ ለመንፈስቅዱስም ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

.......... /// ..........

## ምዕራፍ ፫

### ዘኖላዊ ምንባብ

፩ በስመ እግዚአብሔር እምቅድመ ዓለም ሥላሴሁ ዘአኀበረ፡ እንበለ ቱሳሔ ህላዌሁ ዘደመረ። ዘኢኮነ ፍጡረ ወኢግቡረ፡ ወኢኮነ ብዑደ ወኢነኪረ ፡ ዘእንበለ ዓምድ ወሰዋቅ ሰማየ ዘፈጠረ፡ ምድረ ርግዕተ በዘባነ ባሕር ዘአንበረ። ዐውደ ፀሐይ ወወርኀ ከመ መጽሔት ዘቀመረ፡ ዘሠርዐ ሎሙ ሠረገላ ነፋሳት መጸውረ ዘገብረ ሎሙ በገጸ ሰማይ ምሕዋረ፡ እንዘ ይሚግብዎሙ መላእክት ወይመርሕዎሙ ከዋክብት እመ ንገለ ጽባሕ ለመንገለ ዐረብ እንጸረ፡ ሎቱ ስብሐት ለእግዚአ ብርሃናት ለዓለመ ዓለም አሜን።

፪ ንንግር እንከ ዘለፋሁ ለአርዮስ ዘበዲቁናሁ አሥረፀ ዕልወተ ወበቅስናሁ ፈረየ ሦከ ኃጢአት። አርዮስ ሠረገላሁ ለሰይጣን ወሱታፌሆሙ ለአጋንንት።አርዮስ ሙሱነ ኀሊና ወጽልኀወ ልብ ወሕሡመ ሃይማኖት። አርዮስ ጽዩአ ከናፍር ወቍሱለ ልሳን ዘሐመ በሕምዘ ግዘት። አርዮስ ርጉም በአፈ እግዚአብሔር ጸባዖት ዘረገማ ለአርዌ ምድር ወይቤላ ርግምተ ኩኒ እምኵሉ እንስሳ ወእምኵሉ አራዊተ ምድር በእንግድዓኪ ሑሪ ወመሬተ ብልዒ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትኪ። እስተፃርር ማዕከሌኪ ወማዕከለ ብእሲት ማዕከለ ዘርእኪ ወማዕከለ ዘርኣ ውእቱ ለይዕቀብ ርእሰኪ ወአንቲኒ ዕቀቢ ሰኰናሁ። ዘፍ፫፥፲፬-፲፭ ኩፋ፬፥፳፩

፫ ደቂቀ አርዮስ የዐቅቡ ሰኳንወ እመቦ ዘረከቡ እምቢጸ ትሑታን ከመ ይሚጥዎ ኀበ ግዕዞሙ። ወንሕነኒ ነዐቅብ ርእሰ እመቦ ዘረከብነ እመምህራኒሆሙ ከመ ንምትር ርእሶሙ ወናውቂ ልሳኖሙ።

፬ አርዮስ ኢፍሉጥ ወኢሊሉይ እምዲያብሎስ ዘወድቀ እምጸታ መላእክት።አርዮስ ኢብ ዑድ ወኢነኪር እም አርዌ ምድር ዘአስሐታ ለሔዋን። አርዮስ ምቱር በሰይፈ እሳት ዘይወፅእ እምአፉሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ። አርዮስ ሥርው መሪር ዘበቍለ በእስክንድርያ ወተመልሐ በጽንዓ ሃይማኖቶሙ ለ፫፻፲ወ፰ ማኅበረ ቅዱሳን፡ ዘፍ፫፥፲፫

፭ ወጥንተ ነገሩሰ ኮነ በመዋዕሊሁ ለዲዮግልድያኖስ ዕልው ዘአዘዘ ይዕፅዉ አብያተ ክርስቲያናት ወያርኀዉ አብያተ ጣዖት።ሦዐ ለአጋንንት ወተቀንዮ ለግልፎ።አዘዘ ስደተ ለኤጲስቆጶሳት ወመጻእርተ ኩነኔ ዕፁብ ላዕለ መሀይምናን

## ምዕራፍ ሦስት

### የኖላዊ ምንባብ

፩ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ሦስት ሲሆን አንድ በሆነ ያለመቀላቀል መለኮቱን ከሥጋ ባሞሀደ ፈጽሞ የተፈጠረ ባይደለ በእግዚአ ብሔር ስም፤ ፈጽሞ የተለየ አይደለም፡ ሰማይን ያለምሰሶና ድጋፍ የፈጠረ የረጋች ምድርን በውኃ ትከሻ ላይ ያስቀመጠ የፀሐይንና የጨረቃን ክበብ እንደመስታወት ክበብ የወሰነ የነፋሳትን ሠረገላ ተሽካሚ አድርጎ የሠራላቸው መላእክት እየመገቧቸው ከዋክብትም ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ በአንፃር እየመሩአቸው በጠፈር ላይ መመላለሻን የሠራላቸው ለብርሃናት ጌታ ለርሱ ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

፪ እንግዲህ በዲቁናው ክህደትን ያበቀለ በቅስናውም የኃጢአትን እሾህ ያፈራ የአርዮስን ተግሣጽ እንናገር። አርዮስ የሰይጣን ሠረገላው የአጋንንትም ማኅበረተኛቸው ነው። አርዮስ ኅሊናው የጠፋ ልቡም የታወረ ሃይማኖቱም የከፋ ነው።አርዮስ ከንፈሮቹ የተበላሹ በውግዘት መርዝ የታመመ የምላስ ቁስለኛ ነው፡ከእንስሳና ከምድር አራዊት ሁሉ መካከል የተረገምሽ ሁኚ በደረትሽ ተሳቢ ትቢያም ብዪ በሕይወት ዘመንሽ ሁሉ በአንቺና በሴቲቱ መካከል በዘርሽና በዘሯ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፡እርሱ ራስሽን ይጠ ብቅ አንቺም ተረከዙን ጠብቂ ብሎ እባብን በረገማት አሸናፊ በሚሆን በእግዚአብሔር አንደበት የተረገመ ነው።መዝ ፻፴፰፥፳፩ ምሳ፳፭፥፩

፫ የአርዮስ ልጆች ከትሑታን ባልንጀሮች መካከል ቢያገኙ ወደ ጥፋታቸው ይመልሱት ዘንድ ተረከዝ ይጠብቃሉ፡ እኛም ከዐዋቂዎቻቸው ብንገናኝ ራሱን ልንመትር ምላሱንም ልንቆርጥ ራስ እንጠብቃለን።

፬ አርዮስ ከመላእክት ወገን ከወደቀ ከዲያብሎስ ፈጽሞ የሚለይ አይደለም አርዮስ ሔዋንን ካሳታት ከእባብ ፈጽሞ የተለየ አይደለም።አርዮስ ከኢየሱስ ክርስቶስ አፍ በሚወጣ የእሳት ሰይፍ የተቆረጠ ነው።አርዮስ በእስክንድርያ የበቀለ በሦስት መቶ አሥራስምንቱ የቅዱሳን ማኅበረተኞች ተነቅሎ የወደቀ መራራ ሥር ነው። ዘፍ፫፥፲፫

፭ ጥንተ ነገሩም እንዲህ ነው አብያተ ክርስቲያናትን እንዲዘጉ አብያተ ጣዖታትን ግን እንዲከፍቱ ባዘዘ ለአጋንንት በሠዋና ለጣዖት በሰገደ በከሀዲው በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን በኤጲስቆጶሳት ላይ ስደት በምእመናንም ላይ አስጨናቂ

እለሂ ተመይጡ ኀበ አምልኮቱ ሕሰምት ምዑ ለኢጋንንት እምፍርሀተ ኮነኔ ወእለሂ ተሰዱ ተንበሉ ውስተ አድባር ወበዐታት ወግበበ ምድር። ወእለሂ ተርፉ ውሉዳን ውስተ አብያተክርስቲያን እሕሰሙ ሃይማኖተ ኩሉ ነበበ በከመ ፈቀደ ወመሀረ በከመ ሐለየ።

፮ ወእምዝ ተሰምዐ ድምፀ ዕልወቱ ለአርዮስ እንዘ ዓዲሁ ዲያቆን ወይቤ ክርስቶስ ፍጡር ውእቱ ለመድኃኒተ ዓለም ዘተፈጥረ። ወሶበ ሰምዐ ዘንተ አውግዞ ጴጥሮስ ወሰደዶ እፍአ እምቤተክርስቲያን። ወሖረ አርዮስ ኀበ አኪላስ ወእለእለስክንድርስ ቀሳውስት ወሰአሎሙ ያስተብቍዕዎ ለጴጥሮስ ሊቀጳጳሳት ከመ ይፍትሖ እምግዘቱ።

፯ ወሖሩ እሙንቱ ቀሳውስት ኀበ ጴጥሮስ ሊቀጳጳሳት ሰንዱ ወአስተብቍዕዎ በእንተ አርዮስ ከመ ይፍትሖ እማእሥረ ግዘቱ። ወአበዮሙ ጴጥሮስ እንዘ ይብል አርዮስ ፍሉጥ ወሊሉይ እምስብሐተ ኢየሱስ ክርስቶስ። ወእሙንቱሂ እንተ አስተብቍዕዎ በእንተ አርዮስ እንዘ ይመስሉሙ ከመ ይትመየጥ ኀበ ርትዕት ሃይማኖት።

፰ ወሶበ አጽሐብዎ ብዙኀ አዘዘ ጴጥሮስ ከመ ይትጋባእ ሕዝብ ወይትርፉ ምስሌሁ አኪላስ ወእለእለስክንድርስ ወይቤሎሙ አስተርአየኒ በዛቲ ሌሊት እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ በአምሳለ ሕፃን ብሩህ ወይቴጽር ገጸ እምግዘን ወይለብስ ሥጡጠ አልባስ ወይእኅዝ ሥጡተ ልብሶ በክልኤ እደዊሁ። ወእቤሎ እ እግዚእየ መኑ ሠጠጠ ለልብስከ። ወይቤለኒ አርዮስ ሠጠጠ ለልብስየ ዑቅ ኢትትወከፎ፡ እስመ ሀሉ ጸዋሐ ያስተብቍዑከ በእንቲአሁ ዘከፈለኒ እመለኮተ አቡየ ኢይትዌከፎ መስኮተ አቡየ ውስተ መንግሥቱ።ወእምዝ ኀደጉ አስተብቍዖቶ ለሊቀ ጳጳሳት እሙንቱ ቀሲሳን፡ ወእምድኅረዝ ተፈነወ ጠርጥናፍተ ሚትራይቀይ ዘውእቶሙ ኃላት ብትእዛዘ ዲዮቅልጥያኖስ ከሃዲ ከመ ይምትሩ ርእሶ በእንተ ዘአሐዎሙ ለፃዎ መርጦንቱ።

፱ ወበፅዐ ጴጥሮስ ፈጸመ ሰምዐ ዘበሰ ይፍ ወተከለለ በከመ ኢየሱስ ክርስቶስ ወአን ፈሰ እምዝ ዓለም። ወድኅሬሁ ተሰይመ አኪላስ ወሖረ አርዮስ ወአስተብቍዖ ለአኪላስ ከመ ይፍትሖ እምግዘቱ እንተ ረገሞ ጴጥሮስ።ወፈ ትሖ እምግዘቱ ወሴሞ ቀሲሰ ወእምዝ ገብአ ኀበ እበዱ ዘትካት።

፲ ወሰዲዮቅልጥያኖስኒ ገፍትኦ እግዚአብሔር እመንበረ መንግሥቱ ወአያር ዘመኰንንሩ ወርቅ ክልኤ አዕይንቲሁ ዘኢንክ ኮሎንታሁ ወእደየ ልሳኖ ወተበዐረ እመንግሥቱ ወነበረ እንዘ ይሴአል ምጽዋተ በአዕጋተ አንጾኪያ። ወነገሠ ሆኖሪዮስ ተሰጠንጢኖስ በሮምሠ ርወ መንግሥተ ሮሜ ዝእኑ ጭገደ ዕልዋን

መከራዎችን አዘዘ።ወደከፋች አምልኮቱ የተመለሱትም ከመከራቸው ፍርሀት የተነሣ ለኢጋንንት መሥዋዕት አቀረቡ የተሰደዱትም በተራራ ችና በዋሻዎች በፍርኩታዎችም ተሸሸጉ። በቤተ ክርስቲያንም የተረፉት ጥቂቶች ሃይማኖትን እጠቁ ሁሉ እንደወደደ ተናገረ እንዳሰበውም አስተማረ።

፮ ከዚህ በኋላ ገና ዲያቆን ሳለ የአርዮስ የክህደት ድምፅ ተሰማ ክርስቶስ ዓለምን ሰማዳን የተፈጠረ ፍጡር ነው አለ። ጴጥሮስም ይህን በሰማ ጊዜ አውግዞ ከቤተክርስቲያን አስወጣው፡ አርዮስም ቀሳውስት ወደሆኑት ወደ አኪላስና ወደ እለእስክንድርስ ሄዶ ከውግዘቱ ይፈታው ዘንድ ከሊቀጳጳሳቱ ከጴጥሮስ እንዲያማልዱት ለመናቸው።

፯ እኒያም ቀሳውስት ወደ ሊቀጳጳሳቱ ወደ ጴጥሮስ ዘንድ ሄዱ፡ እጅ ነሥተው ከውግዘቱ ማሠሪያም ይፈታው ዘንድ ስለአርዮስ ተማፀኑት ጴጥሮስ ግን አርዮስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ፈጽሞ የተለየ ነው ብሎ እንቢኝ አላቸ ው። እነርሱም ወደ ቀናችይቱ ሃይማኖት የሚመለስ መስሏቸው ስለአርዮስ አብዝተው ማለዱት።

፰ አብዝተው ባስጨነቁት ጊዜ ጴጥሮስ ሕዝቡ እንዲሄርቁ አኪላስና እለእስክንድርስ ግን ከእርሱ ጋር እንዲቆዩ አደረገ፡ አላቸውም በዚህች ሌሊት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በብሩህ ሕፃን አምሳል ተገለጠልኝ ራሱን በግዘን ቋጥር ነበር የተቀደደ ልብስ ለብሶ ነበር። እኔም ጌታዬ ሆይ ልብስህን ማን ቀደደው አልሁት እርሱም አርዮስ ልብሴን ቀደደው ዕወቅ አትቀበለው በንግህ ስለርሱ ይለምኑህ ዘንድ አላቸውና ከአባቴ መለኮት ስለለየኝ የአባቴ መለኮት በመንግሥቱ አይቀበለውም።ከዚህ በኋላ ቀሳውስቱ ሊቀጳጳሳ ቱን መማፀኑን ተዉት፣ ከዚህም በኋላ የሞርጦንቱን ምርኮኞች ስለታደጋቸው ራሱን ይቆርጡት ዘንድ በከሃዲው በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ ጠርጣናት ሚትራይቀይ የተባሉ ጭፍሮች ተላኩ።

፱ ብፁዕ ጴጥሮስም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሰይፍ ተከልሎ ምስክርነቱን ፈጸመ ከዚህም ዓለም አረፈ። ከእርሱም በኋላ አኪላስ ተሾመ።አርዮስም ሄዶ ጴጥሮስ ካወገዘው ውግዘት ይፈታው ዘንድ አኪላስን ተማፀነው። እር ሱም ከውግዘቱ ፈትቶ ቅስና ሾመው ከዚህም በኋላ ወደ ቀደመ ስንፍናው ተመለሰ።

፲ ዲዮቅልጥያኖስንም እግዚአብሔር ከመን ግሥቱ ዙፋን ገለበጠው ሁለት ዓይኖቹንም በወ ርቅ መዝራክር አሳወረው ሁለንተናው ቆስለ እሩም ሸተተ ከመንግሥቱም ተሻረ በአንጾኪያ ጎዳናዎች ምጽዋት እየለመነ ኖረ፡ በርሱም ፈን ታ ከሮም መንግሥት ወገን የሆነ ቈስጠንጢ ኖስ ነገሠ የከሃዲዎች ጭገድ ቆመ የኃጢአትም

ወንድአ ማዕበለ ኃጢአት እንፈስት ቤተክርስ ቲያን። ወተግህደ ሃይማኖተ ክርስቶስ ወተጋብኡ ኤጲስቆጶሳት ፫፻፲ወ፰ በደብረ ኒቂያ እንተ ይእቲ ቢታንያ እመ እህጉር ወምስሌሆሙ ቈስጠን ጢኖስ ንጉሥ ወመዋዒ ወአውገዝዎ ለአርዮስ ዘሰመዮ ለፈጣሪ ፍጡረ። ወአውገዙ ኵሉ ዘየአምን በሃይማኖቱ ወሰደድዎ እምአግባዐ መር ዔቱ ለክርስቶስ።

፲፭ ወእምድኅረ ጕንዱይ መዋዕል ሖረ ኀበ ካልዕ ንጉሥ ወተማኅፀነ ቦቱ እንዘ ይብል አስተብቍዖሙ ለካህናተ እለእስክንድርያ በእንቲ አየ ከመ ይሳተፉኒ በጸሎት ወበቍርባን ወእነሂ አንብር ሃይማኖተ ምስሌሆሙ። ወለእከ ሎቱ ንጉሥ እንዘ ይብል ሥረዩ ሎቱ ለአርዮስ ምግ ባሬቲሁ ዘትካት ወውእቱኒ የኀብር ሃይማና ተክሙ ወተሳተፍዎ ጸሎተ ወቍርባነ። ወለአኩ ካህናተ እለእስክንድርያ ኀበ ንጉሥ እንዘ ይብሉ አርዮስ የኀብእ ጽልሑተ ውስተ ልቡ ለለስደቱ ይትጋነይ ወይቤ እትመየጥ ለለበአቱ ይትከሀድ ወይገብእ ኀበ ዘትካት ህላዌሁ። ጴጥሮስ አውገዞ ወሰደዶ እምቤተክርስቲያን። ወእኪላስ ተወክፎ ሶበ ተጋነየ ሎቱ ወሜሞ ቀሲስ።

፲፮ ወእምዝ አፈድፈደ ጸሪፈ ላዕለ ክርስቶስ ወሰደደ መሀይምናነ በመዋዕለ መምለክያነ ጣዖት። እለስክንድሮስ አውገዞ ወተጋነየ ሎቱ ወፈትሖ። ወካዕበ እሕሠመ ሃይማኖተ ከመ ቀዲሙ ፫፻፲ወ፰ ኤጲስቆጶሳት አውገዝዎ ወሜልሱ ዝንቱ እንዘ ይትጋነይ። ወንጉሥሰ አስተብቍዖሙ ብዙኀ በመልእክቱ ከመ ይሳተ ፍዎ። ወእሙንቱኒ እም ፍርሀተ ንጉሥ ይቤሉ ይገብር እግዚአብሔር ከመ ይደሉ። ውእቱኒ ይጸውም ወይጸሊ ሰቡዐ መዋዕለ ወንሕነኒ ንገብር ከማሁ።

፲፯ ወወሀብዎ ዕድሜ መዋዕል ለተሳትፎ ጸሎት ወቍርባን እስከ ዕለተ እሑድ። ወበለተ እሑድ መጽአ ንጉሥ ውስተ ቤተክርስቲያን ተሰርጊዎ አልባሰ ቀደውተ ወቆመ ንስቲተ ጊዜ ጸሎት።ወእምዝ ተሀውከ ከርሡ ወወጽአ ጽሚተ ወሖረ ውስተ ዐጸደ ምኵሳሕ ወነበረ ከመ ያኵስሕ ወወጽአ አማዑቱ ወተክዕወ ኵሉ ንዋየ ውስጡ።

፲፰ ወሶበ ጕንደየ መጊእ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ተበሀሉ ካህናት ርኢናሁ ለአርዮስ ጊዜ ጸሎት፡ ወይእዜሰ አይቴኑ ሖረ። ሐሩ ወጸውዕዎ ለነሚእ ቍርባን ከመ ኢይትመዐዕ ንጉሥ ላዕሌነ። ወሶበ ሖሩ ለጸውዖቱ ረከብዎ ምውተ ውስተ መካነ ኵስሕ እንዘ ክዕው አማ ዑቱ ወኵሉ ንዋየ ውስጡ።ወአንከሩ ወሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ዘአድኀናሙ እምሱታፌሁ ለንፉቀ ሃይማኖት።

ማዕበል ጸጥ አለ ቤተክርስቲያን አረፈች የክርስ ቶስም ሃይማኖት ተገለጠች ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ኤጲስቆጶሳት በደብረ ኒቅያ ተሰበሰቡ ። ይህችውም የሀገሮች እናት ቢታንያ ናት ከነርሱ ም ጋር የተወደደና አሸናፊ የሆነ ቈስጠንጢኖስ ነበር።ፈጣሪን ፍጡር ያለው አርዮስን አወገዙት በሃይማኖቱ ያመኑትንም ሁሉ አወገዙ ከክርስ ቶስም ከመንጋው በጎች ለይተው አጋዙት።

፲፭ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደሌላ ንጉሥ ዘንድ ሄዶ በጸሎትና በቁርባን እንዲያሳትፉኝ ስለእኔ የእስክንድርያን ካህናት ለምንልኝ እኔም በሃይማኖት ከእነርሱ ጋር እተባበራለሁ ብሎ ተማፀነበት። ንጉሥም የአርዮስን የቀደመ ሥራ ዎቹን ይቅር በሉት እርሱም በሃይማኖታችሁ ይኖራል በጸሎትና በቁርባንም አሳትፉት ብሎ ላከለት። የእስክንድርያም ካህናት አርዮስ በሚ ሰደድ ጊዜ ክፋቱን በልቡ ሸሽጎ እመለሳለሁ እያ ለ ይማፀናል፡ ሲመለስ ግን ከዶ ወደ ቀድሞ ግብሩ ይመለሳል፡ ጴጥሮስ አውግዞ ከቤተክርስ ቲያን አስወጣው እኪላስ ግን በፊቱ በተማለለ ጊዜ ተቀበሉ ቅስና ሾመው።

፲፮ ከዚህም በኋላ በክርስቶስ ላይ ስድብን አበዛ በጣዖት አምላኪዎች ዘመን ምእመናንን አሳደደ።እለእስክንድሮስ አወገዘው በፊቱ ተማለለ ፈታውም ሁለተኛ እንደተደመው ሃይማኖትን አጠፋ ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ አወገዙት ይቅርታ ሲጠይቅ ይህ ሦስተኛ ነው ብለው ላኩ።ንጉሥም እንዲያስተፉት በመልእክቱ አብዝቶ ማለዳቸው። እነርሱም ንጉሥን ከመፍራት የተነሣ እግዚአብሔር እንደሚገባ ያድርግ እርሱ ሰባት ቀን ይጹም ይጸልይ እኛም እንዲሁ እናደርጋለን አሉ።

፲፯ እስከ እሑድ ቀንም በጸሎትና በቁርባን ለመሳተፍ የጊዜ ዕድሜ ሰጡት በእሑድ ቀንም በሐር ልብስ ተሸልሞ ወደነርሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጣ ጥቂት ጊዜም ለጸሎት ቆመ። ከዚህ በኋላ ሆዱ ታወከበት በዝምታም ወጣ ወደ መፀዳጃም ቦታ ሄዶ ሊፀዳዳ ተቀመጠ አንጀቱ ወጣ ሆድ ዕቃውም ሁሉ ተዘረገፈ።

፲፰ ወደ ቤተክርስቲያንም ለመምጣት በዘገየ ጊዜ ካህናት አርዮስን በጸሎት ጊዜ አየነው አሁን ግን ወዴት ሄደ፤ ሂዱ ንጉሥ በእኛ ላይ እንዳይቆጣ ቁርባን ለመቀበል አርዮስን ንሩት አሉ። ሲጠሩት በሄዱ ጊዜ በመፀዳጃ ሥፍራ አንጀቱ ወጥቶ ሆድቃውም ሁሉ ተዘርግፎ አገ ኙት፡ አደነቁ የሃይማኖት ተራጣሪ ከሆነ እርሱ ጋር ማኅበረተኛ ከመሆን ያዳናቸው እግዚአብ ሔርን አመሰገኑት።

፲፭ ወተፈጸመ ላዕሌሁ ለአርዮስ ቃለ ነቢይ ዘይቤ ሞቱ ለኃጥእ እኩይ። ወበካልዕኒ ይብል ገሩም መቅሠፍተ መዐትከ ላዕለ ኃጥእን። ጳውሎስኒ ይቤ በእምጣነ ታጸንዕ ልበከ ወኢትኔስሕ ትዘገብ ለከ መቅሠፍተ። በዘከመዝ ንግር ኮነ ሞቱ ለአርዮስ። መዝ ፴፫+፳፩ ሮሜ፪+፭

፲፮ እስኩ ይቤ አርዮስ ፍጡር ውእቱ ክርስቶስ። ውእቱሰ ፩ደ ጥንተ ይሬሲ ህላዌ ዘመለኮትነ ወዘትስብእትነ፡እስመ ህላዌ መለኮትሰ እምቅድመ ዕለት ወሰዓት እምቅድመ አዝማን ወዓመታት እምቅድመ ኵሉ ዘገቡር ወፍጡር። ህልው አብ በአብናሁ ወኢይትመየጥ ለከዊነ ወልድ ወኢለከዊነ መንፈስቅዱስ ህልው ወልድ በወልድናሁ ወኢይትመየጥ ለከዊነ አብ ወኢለከዊነ መንፈስቅዱስ።ህልው መንፈስቅዱስ በመንፈስቅድስናሁ ወኢይትመየጥ ለከዊነ አብ ወኢለከዊነ ወልድ። መዝ፻፮+፲፮

፲፯ አልቦ ቀዲመ ህላዌ ለአብ እምወልድ ኢመጠነ ቅጽበተ ዐይን ወኢመጠነ ከበስበሰ ቀራንብት። አልቦ ቀዲመ ህላዌ ለወልድ እምቅድመ መንፈስቅዱስ ወኢመጠነ ሩጸተ መባርቅት ወኢመጠነ ጥፍሐተ አክናፈ አንስርት። ኢሀሉ ዕበይ ላዕለ አብ ዘኢሀሉ ላዕለ ወልድ ዘእንበለ ተሰምዮ አብ ባሕቲቱ። ወኢሀሉ ትሕትና ላዕለ ወልድ እምዕበየ ክብር ዘአቡሁ ዘእንበለ ተሰምዮ ወልድ ባሕቲቱ። ወኢሀሉ ኑታጌ ስብሐት ላዕለ መንፈስቅዱስ ዘእንበለ ተሰምዮ መንፈስ ባሕቲቱ።

፲፰ ረከብናሁ ለአብ እንዘ ይሰመይ አበ ለወልዱ። ፍጡራነ ዝ ዓለም ኢነአምር ዘከመ እፎ ወለዶ እስመ አልቦቱ እም አሜሃ ወኢሥጋዌ ለዘርአ መላድ። ኢተልሕኮ አሜሃ አበ ኵልነ አዳም ወኢወፅአት እምገቦሁ እመ ኵልነ ሔዋን። ወዓዲመ ረከብናሁ ለመንፈስቅዱስ እንዘ ይሰመይ መንፈስቅዱስ ዘአልቦቱ አበ ወኢወልደ በገዐዘ መለኮቱ ወባሕቱ ወለነሰ ወለደነ በጥምቀተ ማይ በገዐዘ መለኮቱ። አብኒ ወለደነ ወልድኒ ወለደነ መንፈስቅዱስኒ ወለደነ።በእንተ አቡሁሰ ወበእንተ ርእሱ ይቤ እነኒ አቡክሙ አቡየኒ አቡክሙ።ቀላ ፪+፲፱

፲፱ ወበእንተኒ መንፈስቅዱስ ይቤ ዘኢተወልደ እማይ ወእመንፈስ ኢይክል በዊአ ውስተመንግሥተ እግዚአብሔር እስመ ዘተወልደ እምሥጋ ሥጋ ውእቱ ወዘተወልደ እመንፈስ መንፈስ ውእቱ፡ በከመ አብ ወለደነ በብዝኀ ኂሩቱ ወልድኒ ወለደነ በብዝኀ ምሕረቱ። በከመ ወልድ ወለደነ በብዝኀ ምሕረቱ መንፈስቅዱስኒ ወለደነ በብዝኀ ኂሩቱ ወዕበየ ጸጋሁ። በከመ አብ ሕያው ወልድኒ ሕያው በእንተ አብ። ወበከመ

፲፭ የኃጥእ ሞቱ ክፉ ነው፡ያለው የነቢይ ቃል በአርዮስ ላይ ተፈጸመ።በሌላም ሥፍራ ላይ የቁጣህ በትር ገሩም ነው ይላል።ጳውሎስም ልብህን በምታደነድንና በማትጸጸት መጠን መቅሠፍትን ለራስህ ታከማቻለህ አለ። የአርዮስ ሞቱ እንዲህ ባለ ነገር ሆነ።መዝ ፴፫+፳፩ ሮሜ፪+፭

፲፮ አርዮስ እንደምን ክርስቶስ ፍጡር ነው አለ እርሱ ግን የመለኮትንና የትስብእትን የህልውና መሠረት አንድ አደረገ የመለኮት ህልውና ከሰዓትና ከዕለት ከዘመናትና ከዓመታት ከፍጥረትም ሁሉ አስቀድሞ የነበረ ነውና። አብ በአባትነቱ ይኖራል ልጅ ወደ መሆን መንፈስ ቅዱስንም ወደመሆን አይለወጥም፤ ወልድ በልጅነቱ ይኖራል አባት ወደመሆን መንፈስቅዱስንም ወደመሆን አይለወጥም።መንፈስቅዱስም በመንፈስ ቅዱስነቱ ይኖራል አባት ወደመሆን ልጅም ወደመሆን አይለወጥም። መዝ፻፮+፲፮

፲፯ የዓይን ጥቅሻ ያህል የሽፋሽፍትንም መገለጥ ያህል እንኳ ቢሆን አብ ከወልድ በህልውና መቅደም የለውም። ወልድም የመብረቆችን ሩጫ ያህል የንስሮችንም ክንፎችን መማታት ያህል እንኳ ቢሆን ከመንፈስቅዱስ በህልውና መቅደም የለውም።ለብቻው አባት ከመባል በቀር በወልድ ዘንድ የሌለ ጌትነት በአብ ዘንድ የለም በወልድም ለብቻው ልጅ ከመባል በቀር ከአባቱ የጌትነት ክብር መጉደል የለም ለብቻው መንፈስቅዱስ ከመባል በቀር በመንፈስቅዱስ ዘንድ የምስጋና መጉደል የለም።

፲፰ አብን ለልጁ አባት ሲባል አገኘነው የዚህ ዓለም ፍጥረቶች እንደምን እንደወለደው አናውቅም፤ ያን ጊዜ እናት የለችውምና ለመወለድም ዘር ሥጋ አልተፈጠረም፤ያን ጊዜ የሁላችን አባት አዳም አልተፈጠረም የሁላችን እናት ሔዋንም ከጐኑ አልወጣችም።መንፈስቅዱስንም በመ ለኮት ባሕርዩ አባትና ልጅ ሳይኖረው መንፈስ ቅዱስ ሲባል አገኘነው።ነገር ግን በቸርነቱ ባሕርዩ እኛን በውኃ በጥምቀት ወለደን አብም ወለደን ወልድም ወለደን መንፈስቅዱስም ወለደን። ወልድ ስለአባቱና ስለራሱ እኔም አባታችሁ ነኝ አባቴም አባታችሁ ነው አለ።ቀላ ፪+፲፱

፲፱ ስለ መንፈስቅዱስም ከውኃና ከመንፈስቅዱስ ያልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይቻለውም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነውና አለ።አብ የቸርነቱ ብዛት አብ እንደ ወለደን ወልድም በይቅርታው ብዛት ወለደን መንፈስቅዱስም በይቅርታውና በጸጋው ታላቅነት ወለደን። አብ ሕያው እንደሆነ ወልድም የአብ ልጅ ስለሆነ ሕያው ነው። ወልድም ሕያው እንደሆነ

ወልድ ሕያው መንፈስቅዱስሂ ሕያው ወማሕየዊ በአንተ አባግዒሁ ለወልድ።ዮሐ፲፡፲ ፲፩፡፳፭

፳ በከመ አብ አፍቀረነ ወአምሐኦ ለወልዱ ዘያፈቅር እምኔነ ወልድሂ አፍቀረነ ወመጠወ ነፍሶ ለቤዛ አባግዒሁ። ወበከመ ወልድ አፍቀረነ ወመጠወ ነፍሶ ቤዛ አባግዒሁ ተአሥርነ በአንባለ ሥላሴ ወተሞቃሕነ በሰንሰለሁ ዘኢይትፈለይ ወተቀነውነ በቅንዋተ ፍቅሩ ዘኢይትመላሕ እምአልባቢነ።አንዘንሁ ወኢንገድፎ ውእቱሂ አፍቀረነ ወኢይገድፈነ።አስመከነ ዲቤሁ በሃይማኖት ወኢንትትን እምኔሁ ለይምን ወለፀጋም። አንበርናሁ ከመ ሕልቀት ውስተ ልብነ ወከመ ማዕተብ ውስተ መዝራዕትነ።

፳፩ ወደይናሁ ከመ ባሕርይ ውስተ አስኪፈነ ልብነ ወከመ መካልየ ወርቅ ውስተ መዝገበ ኅሊናነ።ለበስናሁ ከመ ሞጣሕት ወተዓጸፍናሁ ከመ ዓጽፈ ሜላት። ቀነትናሁ ከመ ሰይፍ ዘሐራ ነገሥት ወተወልተውናሁ ከመ ወልታ መዊዕ ዘድልው ለንዋየ አብዕ፡ አስመ መልዐ ውስተ ልብነ ፍቅረ ዚአሁ ከመ ተከዚ ግዮን በወርኀ ኢሉል። ዮሐ፲፡፲፯

፳፪ ወከመ ተከዚ ዮርዳኖስ ዘጊዜ ማእረር። ከመ ተከዚ ጤግሮስ አሚ ክረምት ወከመ ተከዚ ኤፍራጥስ አመ ይሰዊ ሥርናይ።ሰቀየ ለልብነ በአፍላገ ወንጌል ወአፅበቶ ለሐመርነ ውስተ ቀላየ ሃይማኖት።መሰቀረ ንብረ እምዕፀወ ሊባኖስ ዘውእቶሙ ነቢያት አዕፁቀ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ።ወናትያተኒ አርእየ አለ ይትኬወሩ ውስተ ባሕረ ዓለም ፲ወ፪ ዕደወ ኃይል ዘአምጎ ፲ወ፪ ሕዝበ ዲዮስጶራ ዘውእቶሙ ሐዋርያት። ወለመርድአ ግብር ዘይትገሀ ለሥርዓተ አሕማር ዘሃይማኖት ኀረየ ፩ ወረሰየ ዘእምነ ተርሴስ ዘቂልቅያ ዘእምሕዝበ ብንያም ዘውእቱ ጳውሎስ ዘጸሐፈ ዜናሁ ውስተ መጽሐፈ አብረክሲስ አንተ ይእቲ መጽሐፈ ዜናሆሙ ለሐዋርያት። ወሀየንተ መቃድፍ አርአየ ፸ ዕደወ አለ ይትራድኡ ለአርውየ ሐመር። ማቴ ፲፡፩-፭ ሉቃ፲፡፩ ሐዋ፩፡፲፫-፲፭

፳፫ ንንግር ኀበ ዘለፋሁ ለአርዮስ ዘይቤ ፍጡር ውእቱ ክርስቶስ። አ ዕዉረ ልብ አርዮስ ትብልኑ ከመ ክርስቶስ ፍጡር ውእቱ ዘወእንቲአሁ ተብህለ በከዊኑ እምቅድመ ዓለም ሀሎ ለዓለም። ወከዕበ ይቤ ወለድኩከ እምከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ። ለሊሁኒ ይቤ በወንጌል ስብሐኒ አባ በስብሐቲከ ዘሀሎ ምስሌከ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም። ወመጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ሰብሕክዎሂ ወዓዲ እሴብሖ። እመሰ ፍጡር ውእቱ ክርስቶስ እምኢይቤ እምቅድመ ረከበ ስብሐቲሁ እምቅድመ ፍጥረተ ዓለም።

መንፈስቅዱስም ስለወልደዐቸው (ምእመናን) ሕያውና ሕይወትን የሚሰጥ ነው። ዮሐ፲፡፲ ፲፩፡፳፭

፳ አብ እኛን እንደወደደን የሚወደው ልጁንም እንዲልራራለት ወልድም ወደደን ነፍሱንም ስለበጎቹ ቤዛ ሰጠ መንፈስቅዱስም ወደደን ወደ መንጋዎቹም መወረድን አልናቀም በሥላሴ ገመድ ታሠርን በማይለያይ ሰንሰለቱም ታሠርን ከልቦቻችን በማይነቀሉ የፍቅሩ ችንካሮች ተቸነከርን። ያዝነው እንለቀውም እርሱም አቀፈን አልተወንም ወደርሱ በሃይማኖት አቀረበን ከእርሱም ወደቀኝ ወደግራ አንሸሽም እንደ ተሰበት በልባችን እንደማኅተም በክንዳችን አኖርነው።

፳፩ እንደ ዕንቁ በልባችን ሣጥን አስ ቀመጥነው እንደወርቅ ሣንቲም በኅሊናችን መዝገብ አኖርነው። እንደ ግምጃ ለበስነው እንደ ሐር ግምጃ ተጐናጸፍነው እንደ ነገሥታት ወታደሮች ሰይፍ ታጠቅነው ለጦር ዕቃ እንደ ተዘጋጀ የድል ጋሻ ተደገፍነው ተከዜና ግዮን በኢሉል ወር እንደሚሞሉ ፍቅሩ በልባችን መል ቶአልና። ዮሐ፲፡፲፯

፳፪ እንደ መከር ጊዜ የዮርዳኖስ ወንዝ እንደክረምት ጊዜም የጤግሮስ ወንዝ ስንዴ ሲያጭዱት እንደሚሆን የኤፍራጥስ ወንዝ ልባችንን በወንጌል ፈሳሾች አረሰረሰው መርከባችንን በሃይማኖት ቀላይ አስሞላው። ከሊባኖስ እንጨቶች መርከብን አደረገ እኒሁም የአብርሃምና የይስሐቅ የያዕቆብም ትርጓሜዎች ነቢያት ናቸው፤ ዋናተኞችንም በዓለም ባሕር የሚቀዝፉ ከአሥራሁለቱ የስደት ሕዝቦች አሥራሁለቱን የኃይል ሰዎች መረጠ እኒሁም ሐዋርያት ናቸው። ለመ ርከብ ሥርዓት ለተግባራ ሥራ የሚተጋ የቂልቅያ ግዛት ከሆነች ከጠርሴስ ከብንያም ሕዝብ ወገን የሆነ አንድ ጉልማሳ መረጠ ይኸውም ታሪኩ በአብረክሲስ መጽሐፍ የተጻፈ ጳውሎስ ነው። ይኸውም የሐዋርያት የዜናቸው መጽሐፍ ነው ።በመቅዘፊያ ፈንታ መርከብን ለማርጋ የሚረዱ ሰባ ወንዶችን ገለጠ።ማቴ ፲፡፩-፭ ሉቃ፲፡፩ ሐዋ፩፡፲፫-፲፭

፳፫ ክርስቶስ ፍጡር ነው ያለ አርዮስን ወደ መዝለፍ እንመለስ። ልብህ የታወረ አርዮስ ሆይ ስለርሱ በከሊይ ከዉሐይ አስቀድሞ ስሙ አለ ሁለተኛም ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ ተብሎ የተነገረለትን ክርስቶስ ፍጡር ነው ትላለህን። እርሱም ራሱ በወንጌል አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ከአንተ ጋር ባለ ክብር አክብረኝ አለ፤ ከሰማይም አክብርሁህ ዳግም አከብርሃለሁ የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ። ክርስቶስ ፍጡር ከሆነ አንግዲህ ከዓለም መፈጠር አስቀድሞ ክብሩ ከወዴት መጣ ዓለም

ወእመሂ ኢተሰብሐ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም እምኢይቤሉ አቡሁ ሰባሕከኒ ወዓዲ እሴ ብሐከ፡፡ በእንተሰ ህላዌ መለኮት ይቤ በአፈ ነቢይ እምቅድመ ዓለም ወለደኒ እምቅድመ ያስተርኢ ጽንዐ ሰማያት ወእምቅድመ ይጣዕጥዐ መሠረተ አውግር፡፡ መዝ፻፱+፫ ምሳ፲+፳፭ ዮሐ፲፯+፭

፳፬ ወበእንተኒ ህላዌ ትስብእት ትብል ቅድስት አሪት ወይቤ እግዚአብሔር አዳም ኮነ ከመ ፩ እምኔነ፡፡ በእንተ ልደቱ ዘእምአብ ይቤ ዮሐንስ ወንጌላዊ ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ወውእቱ ቃል እምኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ወእግዚ አብሔር ውእቱ ቃል ወከማሁ እምቀዲሙ ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ወኵሉ ቦቱ ኮነ ወዘእንበ ሌሁሰ አልቦ ዘኮነ፡፡ ዘፍ፫+፳፪

፳፭ ስማዕ ዘንተ ቃለ ወንጌላዊ እስመ ዘመለኮት ይትናገር፡፡ ወያቀድም ወይብል ቀዳ ሚሁ ቃል ውእቱ፡፡ቃለ ይሰምዮ ለወልድ በእን ተ ዘይዜኑ ትእዛዘ አብ በከመ ይቤ ለሊሁ ኩሉ ዘሰማዕኩ በኀበ አብ እነግር፡፡ ወእምዝ ያተሉ ወይብል ወውእቱ ቃል እምኀበ እግዚአብሔር ውእቱ፡፡ ዝኒ ከመ እምኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ይነግር ወከመ ኢታምስሉሙ ነቢበ ዘበእዝን ወመልክዐ አልቦ ይሜልስ ወይብል ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል፡፡

፳፮ እንሥእ ርእሰ ነቢናሁ ንጽሕት ወንጌላዊ ከመ ይትናገር ልዑላተ ወይቤ ዘቦቱ ኵሉ ኮነ፡፡ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ፡፡ ናሁኬ አሰበወ ወአጠየቀ ከመ አልቦ ዘገብረ አብ ዘእንበለ ወልድ፡፡ ከመ ለሊሁ ቃል ውእቱ ዜነወ፡፡ ወከመ ምስለ አብኒ እምቅድመ ዓለም ህልወ አይድዐ፡፡ ወከመ ለሊሁኒ ቃለ እግዚአብሔር ውእቱ ነገረ፡፡ ወከመ ፍጥረተ ዓለምኒ ዘእንበለ ወልድ አልቦ ዘኮነ አጠየቀ፡፡ ሰይፈ ልሳኑ ለዮሐንስ ወንጌላዊ መተረ ልሳኖ ለአርዮስ ዘይነብብ ጽርፈተ ላዕለ እምላክነ፡፡ስማዕኬ አ አርዮሳዊ ዘከመ ይቤልዎ አይሁድ ለእግዚእነ ፶ ዓመት አልብከ አብርሃምሃ ርኢከ ወነሥኦ እብነ ካዕበ ከመ ይውግርዎ፡፡ ዮሐ ፩+፫ ፲፰+፶፱

፳፯ ይጌይስ እበደ ዚአሆሙ እምአበደ ዚአከ፡፡ እማንቱ ይቤሉ በእንተ ትስብእቱስ ይደምጽ እስመ ፴፪ ዓመቱ ለኢየሱስ እስከ ከመ ተሰቅለ፡፡ እማንኬ የሐጽጽ ፴ እም፶ ጕልቈ ዓመተ ልደቱ ዘእማርያም ወኢያእመሩ ልደቶ ዘእምአብ ወመሰሉሙ ወልደ ዮሴፍ ውእቱ፡፡ ርእዩ እሞ ምድራዊተ ወኢርእዩ አቡሁ ሰማያዌ፡ ርእዩ ውርዙቶ ዘበሥጋ ወኢያእመሩ ህላዌሁ እምቅድመ ዓለም፡፡ ርእይዎ እንዘ ይሬዕይ ምስለ ጋዋእን ወይትገሰስ በእደ ዘማዊት ወኢርእይዎ እንዘ ይጼዓን ላዕለ ኪሩቤል ወይትቄደስ እም ሱራፌል፡፡ መጽአ ኀቤሆሙ በትሕትና ከመ

ከመፈጠሩ አስቀድሞ ክብሩ ባይገለጥ እባቱ አከበርሁህ አሁንም አከብርሃለሁ ባላለው ነበር፡፡ ስለ መለኮት ህልውናው በነቢይ አፍ ከዓለም አስቀድሞ ወለደኝ የሰማያት መጽናት ሳይታይ የተራሮች መሠረት ሳይከናዋወን አስቀድሞ ወለደኝ አለ፡፡መዝ፻፱+፫ ምሳ፲+፳፭ ዮሐ፲፯+፭

፳፬ ስለ ትስብእቱ ህልውና የከበረች አሪት እንዲህ አለች እግዚአብሔርም አለ አዳም ከእኛ አንደ አንዱ ሆነ፡፡ከአብ ስለመወለዱም ወንጌላዊ ዮሐንስ በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ያም ቃል እግዚአብ ሔር ነበረ የመጀመሪያውም እንደርሱ ከቀድሞ ጀምሮ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለርሱም የሆነ የለም አለ፡፡ ዘፍ፫+፳፪

፳፭ ይህን የወንጌላዊ ቃል ስማ መለኮት በመጀመሪያ ቃል ነበረ ብሎ የሚናገረውን ያስቀ ድማልና፡፡ የአብን ትእዛዝ ስለሚናገር ወልድን ቃል አለው እርሱ ራሱ በአብ ዘንድ የሰማሁትን እናገራለሁ እንዳለ ከዚህም በኋላ አስከትሎ ያም ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው ይህም ከእግዚ አብሔር ዘንድ እንደሚናገር ነው በጆሮ እንደሚ ሰማ ንግግር አታስመስለው ሦስት የሚሆን አካ ልም የለውም አትበል፡፡ ያም ቃል እግዚአብሔር ነው አለ፡፡

፳፮ ወንጌላዊ ከፍ ከፍ ያሉትን ይናገር ዘንድ ንጹህ የሚሆን የጎሊናውን ራስ አነሣ ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለርሱም የሆነ የለም አለ፡፡ እነሆ አብ ያለወልድ የፈጠረው እንደሌለ ፈጽሞ አስረዳን እርሱም ራሱ ቃል ተናገረ ከአብም ጋር ከዓለም አስቀድሞ መኖሩን አስታወቀ እርሱም ቃል እግዚአብሔር እንደሆነ ነገረን የዓለም ፍጥረታትም ያለወልድ የተፈጠረ እንደሌለ አስገ ነዘቡ የወንጌላዊ ዮሐንስ የአንደበቱ ሰይፍ በአም ላካችን ላይ ስድብን የሚናገር የአርዮስን አንደ በት ዘጋ፡፡ አርዮሳዊ ሆይ አይሁድ ጌታችንን ገና ፶ ዓመት አልሞላህም አብርሃምን ግን አየህ እንዳሉት ስማ ሊወግሩትም ደንጊያ አነሡ፡፡ ዮሐ፩+፫ ፲፰+፶፱

፳፯ ከአንተ እብደት የእነርሱ እብደት ይሻ ላል ስለ ትስብእቱ በእውነት ተናገሩ እስከ ተሰቀለበት ጊዜ ድረስ የኢየሱስ ዕድሜ ሠላሳ ሦስት ዓመት ነውና በእውነት ከማርያም የተወ ለደው ልደቱ ሠላሳ ከኀምሳ ያንሣል፡ ከአብ የተ ወለደውን ልደቱን አያውቁም የዮሴፍም ልጅ ይመስላቸው ነበር፡፡ ምድራዊት እናቱን አዩ ሰማ ያዊ አባቱን ግን አላዩም በሥጋ የሆነ ጉልምስ ናውን አዩ ከዓለም አስቀድሞ ያለ ህልውናውን ግን አላወቁም፡፡ከኃጥአን ጋር ሲቀመጥ በአመ ንዝራይቱ እጅ ሲዳሰስ አዩት በኪሩቤል ሠረገላ ተቀምጦ በሱራፌል ሲመሰገን ግን አላዩትም፡፡

ኢያእምርዎ ወኢያስተርአዮሙ በዕበየ መለኮቱ ከመ ኢይሰብውዎ። ሉቃ፳፬+፴፮ ዮሐ፩+፩

፳፰ ወባሕቱ ደኀየሙ በሐጸ ቃል ሶበ ይብል ዘእንበለ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ። መሰሎሙ ከመ ዘአብደ ወተሐዘበሞ ከመ ዘሐሰወ። ወበእንተዝ ነሥኡ እብነ ከመ ይውግርዎ። ወአንተሰኬ ኦ አርዮስ ትብል እንከ ክርስቲያናዊ አነ ወጥሙቅ።ወእመሰ ክርስቲያናዊ አንተ በስመ መኑ ተጠምቀ በስመ አብኑ ዘእንበለ ወልድ።ናሁኬ ኢይደሉ ተጠምቆ ዘእንበለ በሥላሴ በከመ ይቤ በወንጌል እንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ። ወእመሂ ትብል ተጠመቁ በስመ አብ ፈጣሪ ወበስመ ወልድ ፍጡር ናሁኬ አሕሠምከ ጥምቀተከ እስመ ረሰይከ ጸጋ ጥመቀትከ ላዕለ ፍጡራን። ማቴ፳፰+፲፱

፳፱ ወበእንተ ቀረበ ቊርባንኒ ትብልኑ እበልዕ ሥጋ እጓለ እመሕያው ዘእንበለ ኃይለ መለኮት ወእስቲ ደመ ሰብእ ዘእንበለ ቱሳሔ መንፈስቅዱስ። ኮንከ ነማቲሃ ለሕግ እስከ ለገሲሰ አብድንተ ሰብእ ታረኵስ ኦሪት እፎኬ እንከ ለበሊዐ ሥጋ ሰብእ። እመሰ ይደልዎ ለሰብእ በሊዐ ሥጋሆሙ ለቅዱሳን ወእምደሰዎሙ ለእስራኤል በሊዐ ሥጋሁ ለሙሴ እስመ ውእቱ መጋቤ ሕጎሙ ወተመጣዌ ኦሪቶሙ። ወእም ደለወነ ለነሂ ከመ ንብላዕ ሥጋሆሙ ለሐዋርያት ወከመ ንስቲ ደሞሙ ለአርዳእ ኢየሱስ ክርስቶስ።
ዘሌ፲፩+፳፬

፴ እመሰ ይትቄደስ ሥጋሁ ለፍጡር በደመ ፍጡራን እምተቀደሱ አበው በደመ አቤል ወእምድኅኑ በሞቱ እምፍትሐ ኲነኔ ዘወጽአ ላዕለ አዳም።ወጽአ ትእዛዝ እምኀበ እግዚአብሔር ኀበ አብርሃም ከመ ይሡዖ ለይስሐቅ ወልዱ ወሶበ ተኀበለ ለሕርደቱ ወመልሐ መጥባሕቶ ለጠቢሕ አኀደጎ ቃለ እግዚአብሔር ከመ ኢይጥብሖ። ወአውረደ ሎቱ ቤዛሁ በግዐ እስመ እሙር ውእቱ በመጽሐፈ ሕግ ወሥርዓት ወኢእዙዝ በሊዐ ሥጋሁ ለእጓለ እመሕያው። ወጥቢሐተ በግዕሰ ወብልዓተ ሥጋሁ ልማድ ውእቱ። እመሂ ለበሊዕ ወእመሂ ለሠዊዕ። አዘዞ እግዚአብሔር ከመ ያመክሮ ወይቤሉ ሡዕ ወልደከ ዘታፈቅር ይስሐቅሃ። ወካዕበመ ይቤሉ ኢታውርድ እዴከ ላዕለ ወልድከ አእመርኩ ከመ ታፈቅረኒ። ቀዲሙሰ ኢያእመረኑ እግዚአብሔር ከመ ያፈቅርአብርሃም ሐሰ ሎቱ። ዘፍ፳፪+፩-፲፰ ያዕ፪+፳፩

፴፩ ወባሕቱ ኀደገ ለነ ትእምርተ ከመ ናእምር ዘከመ ያፈቅር አብርሃም ለእግዚአብሔር ከመ ኢንበል በምንትኬ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለአብርሃም ድንግልኑ ውእቱ አው መነኩስ ሰማዕትኑ ውእቱ አው መስተጋድል በለቢሰ ጸማ።

ወደ ነርሱ በትህትና መጣ እነርሱ ግን ፈጽመው አላወቁትም እንዲያስተውሉት በመለኮቱ ክብር አልተገለጠላቸውም።ሉቃ፳፬+፴፮ ዮሐ፩+፩

፳፰ ዳሩ ግን አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርሁ ባለ ጊዜ በቃል ፍላፃ ነደፋቸው ያበደ መስላቸው ውሸት እንደሚናገር ታዘቡት፣ስለዚህም ይወግሩት ዘንድ ደንጊያ አነሡ አንተም አርዮሳዊ ሆይ ራስህን እኔ ክርስቲያን የተጠመቅሁኝ ነኝ ትላለህ አንተ ክርስቲያን ከሆንህ እንግዲህ በማን ስም ተጠመቅህ ያለወልድ በአብ ስም ነውን እነሆ በወንጌል ስታጠምቋቸው በአብና በወልድ በመንፈስቅዱስም ስም በሉ እንደተባለ በሥላሴ ካልሆነ በቀር መጠመቅ አይቻልም አይገባምና፣ ፈጣሪ በአብ ስም ፍጡር በሆነ በወልድም ስም ተጠመቁ ብትል እነሆ ጥምቀትህን አረከስህ የጥምቀትህን ጸጋ በፍጡ ራን ላይ አድርገሀልና።
ማቴ፳፰+፲፱

፳፱ ስለ ቊርባን መለኮት ያልተዋሀደው የሰው ልጅ ሥጋ እበላለሁ መንፈስቅዱስ ያልለወጠው የሰው ደም እጠጣለሁ ትላለህን ኦሪት ርኩስ የምትለውን የሰው በድን እስከ መዳሰስ ደርሰህ ሕግን የምታፈርሣት ሆንህ።እንግዲህ የሰው ሥጋ ስመብላት እንደምን ይሆናል።ለሰው የቅዱሳ ንን ሥጋ መብላት ከተገባው እስራኤል የሙሴን ሥጋ መብላት በተገባቸው ነበር፡ እርሱ የሕጋ ቸው አስተዳዳሪ ኦሪታቸውን የተቀበለ ነውና፡ እኛም የሐዋርያትን ሥጋ እንበላ ዘንድ በተገባን ነበር የኢየሱስ ክርስቶስን ደቀመዛሙርት ደማ ቸውን ልንጠጣ በተገባን። ዘሌ፲፩+፳፬

፴ ፍጡር በፍጡራን ደም የሚከብር ቢሆንስ አባቶች በአቤል ደም በከበሩ፣ በሞቱም በአዳም ከተፈረደው የሞት ፍርድ በዳኑ ነበር። ልጁ ይስሐቅን ይሠዋው ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ትእዛዝ ወደ አብርሃም መጣ። ሊሠዋው ተደፋፍሮ ለማረድ ቢላውን ሲመዝ የእግዚአብሔር ቃል እንዳያርደው አስተወው። ቤዛውንም በግ አወረደለት። በሕግና በሥርዓት መጽሐፍ የታወቀ ነውና፡ የሰውን ልጅ ሥጋ መብላት አልታዘዘምና።የበጉ መታረድ ሥጋውንም መብላት ግን ልማድ ነው። ለመብላትም ቢሆን ለመሠዋትም ቢሆን ይፈትነው ዘንድ እግዚአብሔር አዘዘው የምትወደው ልጅህ ይስሐቅን ሠዋልኝ ብሎ፡ ሁለተኛም እጅህን በልጅህ ላይ አታሳርፍ እንደምትወደኝ ዐወቅሁ አለው ቀድሞውንስ እግዚአብሔር አብርሃም እንደሚወደው አያውቅምን፣ አይደለም።
ዘፍ፳፪+፩-፲፰ ያዕ፪+፳፩

፴፩ ዳሩ ግን አብርሃም እግዚአብሔርን እንደሚወደው እናውቅ ዘንድ ምልክት ተወልን እግዚአብሔር አብርሃምን ስለምን ወደደው ድንግል ነውን ወይስ መነኩሴ ሰማዕት ነውን ወይስ ድካምን በመልበስ የሚጋደል ነው እንዳንል።

ሬከብኪ በኀበ አብርሃም ገድለ ኵሉሙ ቅዱሳን ቀንዐ ለአምላኩ እግዚአብሔር ወአውዐየ ቤተ አማልክተ አበዊሁ ምስለ ጣዖታቲሆሙ። ወበእንተዝ ኮነ አቡሁ ለሙሴ ዘአውፅአ እሳተ እማዕጠንታቲሆሙ ለደቂቀ ቆሬ እስከ በልዐቶሙ። ዘኍ ፲፯+፩-፴፭

፴፪ ወካዕበ ኮነ አቡሁ ለኤልያስ ዘአውዐዮሙ ለ፪ አርእስተ ፶ ዕደው በአውርዶ እሳት እምኀበ እግዚአብሔር ዘውእቶሙ ሐራ ንጉሥ መምለክያነ ጣዖት። ፪ ነገ ፩+፩-፲፰

፴፫ ወወፅአት ትእዛዝ እምኀበ እግዚአብሔር ኀበ አብርሃም ከመ ይፃእ እም ቤተ አቡሁ ወእምብሔረ ሙላዱሁ። ወወፅአ እንዘ ይትፌሣሕ በእግዚአብሔር። ወበእንተዝ ተሰምየ አቡሆሙ ለመነኮሳት ዘቦሙ ትእዛዝ ለኀዲገ አበው ወውሉድ ወለኀዲገ አዝእርት ወገራውህ። ተመከረ በሂደተ ብእሲቱ ሳራ እምኀበ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ወእምአቤሜሌክ ንጉሠ ጌራራ። ወበእንተዝ ኮነ አቡሆሙ ለግፉዓን። አዘዞ እግዚአብሔር ከመ ይትገዘር እመ ፺ወ፱ ዓመታቲሁ ወኢኀፈረ ከሢተ ዕርቃና ለተከስቦ ከመ ደቂቅ።በእንተዝ ተሰምየ አቡሆሙ ለሕፃናት ወኢፈርሀ ሕማመ ተወቅዮ ቍልፈተ ነፍስቱ እንዘ አረጋዊ ውእቱ። ወበእንተዝ ተሰምየ አቡሆሙ ለሰማዕታት እስመ ኢየሐጽጽ ሕማመ ግዝሮሙ ለአእሩግ እምሕማመ ኀርደ ቶሙ ለንዑሳን። ዘፍ ፲፪+፩-፰፣ ፲፯+፳፭፣ ፰+፩-፲፰

፴፬ ተአዘዘ ከመ ይሡዖ ለይስሐቅ ወልዱ ዘያፈቅር ወአምሐኮ አብርሃም ለወልዱ ዘያ ፈቅር አብደረ ይግበር ትእዛዘ እግዚአብሔር እምይምሐኮ ለይስሐቅ ወልዱ።ተሐበለ ከመ ይሕርዶ ወአስከቦ ከመ ይዝብሖ። ወአውረደ እግዚአብሔር በሐኩ ጸዓዳ ለተውላጠ ይስሐቅ ወልደ አብርሃም።እግዚአብሔርኒ ኢምሕከ ወልዶ ዘያፈቅር ወፈነዎ ከመ ይሠገው እምዘ ርእ ይስሐቅ ወልደ አብርሃም ዘውእቱ በግዕ በኀበ ኢሳይያስ ወዮሐንስ። ኅብስተ ሥርናይኒ ወሞጻሕተ ወይን በኀበ መልከጼዴቅ። ላሕም መግዝዕ በኀበ ሉቃስ ወመሥዋዕት ንጹሕ በኀበ ኵሉሙ ሐዋርያት ዘአዘዘ ከመ ያዕርጉ ለሥ ርየተ ኃጢአተ ኵሉሙ አሕዛብ እምሥራቀ ፀሐይ እስከነ ዐረብ እምአጽናፈ ሰሜን ወእስከ ደቡብ። ዘፍ ፳፪+፲፫ ኢሳ፵+፯ ዮሐ፩+፳፱

፴፭ አእመረኬ ፈጣሪ ከመ ኢይትቄደስ ሰብእ በቍርባነ ሥጋሁ ለሰብእ ዘእንበለ በቍርባነ ሥጋሁ ለወልደ እግዚአብሔር ወተሠገወ እም ውሉደ ሰብእ።አእመረኬ ሕያው ዘኢይመውት ከመ ኢይትቄደስ እጓለ እመሕያው በቍርባነ ደሙ ለእጓለ እመሕያው ዘእንበለ በቍርባነ ደሙ ለወልደ አምላክ ሕያው ዘተሠገወ እምእጓለ እመ

በአብርሃምስ ዘንድ የቅዱሳንን ሁሉ ገድል አገኘን ለአምላኩ እግዚአብሔር ቀንቶ የአባቶቹን አማል ክት ቤት ከጣዖቶቻቸው ጋር አቃጠለ ስለዚህም ነገር እስኪያጠፋቸው ድረስ ከቆሬ ልጆች ማዕጠ ንት እሳትን ላወጣ ለሙሴ አባቱ ሆነ። ዘኍ ፲፯+፩-፴፭

፴፪ ዳግመኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ እሳት በማውረድ ሁለቱን የኀምሳ አለቆች ላቃጠላቸው ለኤልያስ አባት ሆነ። እነሁም ጣዖትን የሚያመ ልኩ የንጉሥ ወታደሮች ናቸው።፪ ነገ ፩+፩-፲፰

፴፫ ከአባቱ ቤት ከትውልድ ሀገሩም እንዲወጣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ትእዛዝ ወደ አብርሃም መጣ፡ በእግዚአብሔርም ደስ እያለው ወጣ።ስለዚህም ነገር አባቶችንና ልጆችን አዝዕ ርትና እርሻዎችን ስለመተው ትእዛዝ ላለባቸው ለመነኮሳት አባታቸው ሆነ። በግብጽ ንጉሥ በፈ ርዖን በጌራራም ንጉሥ በአቤሜሌክ ዘንድ ሚስቱን በመነጠቅ ተፈተነ፣ስለዚህም ለሚገፉት ሰዎች አባታቸው ሆነ፡በዘጠና ዘጠኝ ዕድሜው እንዲገረዝ እግዚአብሔር አዘዘ። እንደ ልጅ ለመገረዝ ዕርቃኑን ለመግለጥ ግን አላፈረም ስለ ዚህም የሕፃናት አባት ተባለ ሽማግሌም ሲሆን የሰውነቱን ሸለፈት ለመቆረጥ አልፈራም ስለዚህ የሰማዕታት አባት ተባለ የሽማግሌ የመገረዝ ሕማም ከብላቴናች የመታረድ ሕማም አያንስ ምና። ዘፍ ፲፪+፩-፰፣ ፲፯+፳፭፣ ፰+፩-፲፰

፴፬ የሚወደው ልጁ ይስሐቅን እንዲሠ ዋው ታዘዘ ለልጁ ለይስሐቅ ከሚራራለት ይልቅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይፈጽም ዘንድ መረ ጠ። ሊያርደውም ተደፋፈረ ሊሠዋው በሆዱ አስተኛው። እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ ለይስ ሐቅ ለውጥ ነጭ ሙክት አወረደ እግዚአ ብሔርም ለሚወደው ልጁ አልራራም ከአብርሃም ልጅ ከይስሐቅ ዘር ሰው ሆኖ ይወለድ ዘንድ ላከው ይኸውም በኢሳይያስና በዮሐንስ ዘንድ በግ በመልከጼዴቅ ዘንድ የስንዴ ኅብስትና የወይን ጭማቂ በሉቃስም ዘንድ ፍሪዳ ለሕዝቡ ሁሉ ኃጢአት ሥርየት ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያ ከሰሜን ዳርቻ እስከ ደቡብ ዳርቻ ድረስ ያሳርጉት ዘንድ ባዘዙ ሐዋርያት ሁሉ ዘንድ ያለ ደም የሆነ ንጹህ መሥዋዕት ነው። ዘፍ ፳፪+፲፫ ኢሳ፵+፯ ዮሐ፩+፳፱

፴፭ ፈጣሪስ ከሰዎች ወገን ሰው ሆኖ ከተወለደ ከወልደ እግዚአብሔር የሥጋው ቁርባን በቀር ሰው በሰው ሥጋ ቁርባን እንደማ ይድን ዐወቀ።ሕያውና የማይሞት እርሱ ከሰዎች ልጆች ሰው ሆኖ ከተወለደ ሕያው ከሚሆን ከአ ምላክ ልጅ የደም ቁርባን በቀር እንደማይቀደስ ዐወቀ።ይህ ሕያው የማይሞት የሚሞት ሥጋን

ሕያው። ዝኩ ሕያው ዘኢይመውት ለብሰ ሥጋ ዘይመውት። ዝኩ ኃይል ዘኢይማስን ለብሰ ሥጋ ዘይማስን። ለውእቱ ሥጋ ዘይማስን ረሰዮ ነባቤ ዘኢይማስን። ኀደረ ለሐኩሁ ለአዳም ኀበ ወለተ አዳም ዘበጸጋ ትውልድ። አኮ ዘአምጽአ ሥጋ ንጽሕተ ለርእሱ እምሰማየ ሰማያት ከመ ይሠገው ባቲ፡ አላ ለሊሁ ኃይል ወረደ እንዘ ኢየሐጽጽ እምህላዌሁ። ወረደ እንዘ ኢይትሐወስ ወረደ እንዘበ ድምፅ። ኀደረ ውስተ ማኅፀን ድንግል እንዘ ኢይትጋባእ በመላድ ወኢይ ትጓለድ በማኅፀን ተሠገወ ፈጣሪ እምወለተ ፍጡራን። ኢዕፁብ ሎቱ ለንዳቲ ኀዲር ኀበ ዘነደቀ ጽርሐ ኢነግር ሎቱ ለለሐኮ ለቢሰ ሥጋ ለዘለሐኮ። ዕብ፱+፲

፴፫ ንግባእኬ ኀበ ዘለፋሁ ለአርዮስ እ አርዮስ ሠርፀ ዕልወት ትብሉኑ ለፈጣሪ ፍጥረተ ዘይቤ አነ ወአብ ፩ ንሕነ ፍጡርኑ። ወዘይቤ ዓዲ ወዘኪያየ ሰምዐ ሰመዖ ለዘፈነወኒ ወዘኪያየ ክሕደ ክሕዶ ለዘፈነወኒ። ወዓዲመ ይቤ እልቦ ዘይክል መጺአ ኀበ አብ ዘእንበለ እንተ ኀቤየ። ወካዕበመ ይቤ ኵሉ ዘዚአከ ዚአየ ውእቱ ወዚአ የኒ ዚአከ ውእቱ። ወዓዲመ ይቤ ኵሉ ዘቦ ለአቡየ ዚአየ ውእቱ። ወዓዲመ ይቤ በከመ አብ ሕያው እነዊ ሕያው በእንተ አብ ወዘበልዐ ሥጋየ የሐዩ በእንቲአየ። ናሁኬ አስተሳተፈነ ሕያው ወማኅየዊ በበሊዐ ሥጋሁ ምስለ መለኮተ ዚአሁ ወረሰየነ ሱቱፋነ ለሕይወተ ዚአሁ።በከመ ይቤ ዮሐንስ ወንጌላዊ በውስተ መልእክቱ ቀዳሚ ይ ወሱታፌነሰ ምስለ አብ ወምስለ ወልዱ ኢየሱስ ክርስቶስ። ዮሐ፲፱+፮ ፩ዮሐ፩+፫

፴፬ ንሕነሰ ነአምነከሙ ሥጋሁ ለክርስቶስ ፍጡር ውእቱ ዘእምሥርወ አዳም ወሔዋን ወመለኮቱሰ ለሐኩሁ ውእቱ ለአዳም ወገባሬሃ ለሔዋን። ወሶበሰ ኢኮነ ሥጋዊሁ ፍጡረ እምኢተገምረ በማኅፀን። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እመ ኢተረክበ ማኅተመ ድንግ ልናሃ ለእሙ እምድኅረ ልደቱ። ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዊሁ ፍጡረ እምኢተሐቅፈ በእብራከ ወእ መ ኢተገሰ በእደዊሁ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢያንቅዐ ሐሊበ ድንግልና እምአ ጥባተ ወለት እንተ ኢተአምር ብእሴ። ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዊሁ ፍጡረ እምኢልህቀ በበሕቅ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢይቤ ዘእንበለ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢኮነ ስምዐ አብ በእንቲአሁ እንዘ ይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ሎቱ ስምዕዎ። ወዓዲመ እምኢነበረ ዲቤሁ መንፈስቅዱስ በርእየተ ርግብ ዘሥጋ። ማቴ ፫+፲፫-፲፯

፴፭ ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዊሁ ፍጡረ

ለበሰ ያንን የሚሞት ሥጋ የማይሞት ሕያው አደረገው። ይህ የማይጠፋ ኃይል የሚጠፋ ሥጋን ለበሰ ያንን የሚጠፋ ሥጋ የማይጠፋና የሚናገር አደረገው አዳምን ያበጀው በስድሳ ሁለተኛው ትውልድ በተገኘች በአዳም ሴት ልጅ አደረ። ሰው ይሆንባት ዘንድ ለራሱ ንጽህት ሥጋ ከሰማየ ሰማያት ያመጣ አይደለም ኃይል የተባለ እርሱ ከህልውናው ሳይጉድል ወረደ እንጂ፡ ሳይቀሳቀል ሄደ ሳይሰማ ወረደ በመዋለጃ አካል ሳይሰበሰብ በማኅፀንም ሳይወሰን በድንግል ማኅፀን አደረ።ከፍጡራን ሴት ልጅ ፈጣሪ ሰው ሆኖ ተወለደ፡ ቤት ሠሪ በሠራው ቤት ማደር የሚያስጨንቀው አይደለም ለፈጣሪም የፈጠ ረውን ሥጋ መልበስ የሚያስቸግር አይደለም። ዕብ፱+፲

፴፫ አርዮስን ወደ መውቀሱ እንመለስ፡ የክህደት ቡቃያ አርዮስ ሆይ እኔና አብ አንድ ነን ብሎ የተናገረ የፍጥረታትን ፈጣሪ ፍጡር ነው ትለዋለህን፡ ዳግመኛም እኔን ያየ አብን አይቷል ያለ ፍጡር ነውን፣ እንደገናም እኔን የሰማ የላከ ኝን ሰማው ያለ ዳግመኛም በእኔ በኩል ካልሆነ ወደአብ መምጣት የሚቻለው የለም አለ። ሁለ ተኛም የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው የአንተም የሆነው ሁሉ የእኔ ነው አለ።ዳግመኛም የአባቴ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው አለ። ዳግመኛም አብ ሕያው እንደሆነ እኔም የአብ ልጅ ስለሆንሁ ሕያ ው ነኝ ሥጋዬን የበላ የእኔ ሥጋ ስለበላ በሕይ ወት ይኖራል አለ።እነሆ ሕያውና ሕይወትን የሚያድል እርሱ ሥጋውን በመብላት ከመለኮቱ ጋር አንድ አደረገን ወንጌላዊ ዮሐንስ በመጀመ ሪያ መልእክቱ ኅብረታችን ከአብና ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው እንዳለ በአባቱ ሕይወት ማኅበረ ተኞች አደረገን። ዮሐ፲፱+፮ ፩ዮሐ፩+፫

፴፬ እኛ ግን የክርስቶስ ሥጋ ከአዳምና ከሔዋን ባሕርይ የተገኘ ፍጡር እንደሆነ መለ ኮት ግን አዳምን ያበጀው ሔዋንንም የፈጠራት እንደሆነ እናምናለን። ሥጋው ፍጡር ባይሆን ኖሮ በማኅፀን ከመወሰዱ በኋላ የእናቱ ማኅተመ ድንግልና ባልተገኘ ነበር። ሥጋው ፍጡር ባይሆን ኖሮ በጉልበት ባልታቀፈ በእጆችም ባልተዳሰሰ ነበር መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን ወንድ ከማታውቅ ሴት ልጅ ጡት የድንግልና ወተት ባልፈሰሰ ነበር።መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን ኖሮ አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርሁ ባላለ ነበር። ሥጋው ፍጡር ባይሆን ኖሮ በዮሐንስ እጅ ባልተዳሰሰ በዮርዳኖስም ባሕር ባልተጠመቀ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን አብ ይህ የምወደው ልጄ ነው እርሱን ስሙት ብሎ ስለርሱ ባልመሰከረ መንፈስቅዱስም ዳግመኛ በሥጋዊ ርግብ አምሳል በራሱ ላይ ባላረፈ።ማቴ ፫+፲፫-፲፯

፴፭ ሥጋው ፍጡር ባይሆን ለጥመ

እም እስእለ ማየ ሰጽምኡ እምሰምራዊት። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢረሰዮ ለማይ ወይነ በቃና ዘገሊላ። ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እምኢገሰሰት እንተ ይውሕዛ ደም ዘፈረ አልባሲሁ ወኃጥአትኒ እገሪሁ። ወሶበሰ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢይቤ ብእንተ ዘገሰሰቶ ልብሶ አአመርኩ ከመ ኃይል ወፅአ እምኔየ። ኃይለ ይሰምዮ ለመለኮቱ ወበኃይለ መለኮቱ አይበሰ ንትዓ ደማ። ወእምኢይቤ ኄሰበ ብእንተ ኃጥእትኒ እንተ ገሰሰት እገሪሁ ተኀደገ ለኪ ኀጢአትኪ። መኑ ይክል ኀዲገ ኃጢአት ዘእንበለ እግዚአብሔር ባሕቲቱ። ወሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እመኢጸውዓ ለወለተ ኢያኢሮስ ወለትየ እንዘ ይብል። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢያንሥኣ ሕያውታ እምድኅረ ሞተት።

፵፱ ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እምኢገብረ ጽቡረ ውስተ መሬት ምድር በምራቁ። ወሶበ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢከሠተ አዕይንቲሁ ለዘዕውሩ ተወልደ በትብዐተ ምራቁ። ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እምኢኖመ በከርሠ ሐመር እንዘ ይትነሥኡ መዋግድ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢያዘሐና ለባሕር በተግሣጸ ነፋሳት።ማቴ፳፥፳፱ ዮሐ፱፥፩-፯

፶ ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እምኢደክመ በሐዊረ ፍኖት።ሶበሰ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢያሕየዎሙ ለስቡራን እግር ወእምኢያንሥኦሙ ከመ ሩጸተ ኃየል። ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እምኢርኅበ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢያጸግቦሙ ለ፶፻ ዕደው በኃምስ ኅብስት ወበ፪ ዓሣት። ማቴ፲፭፥፩፥፲፭፥፴፪-፴፱ ዮሐ፮፥፫-፲፬

፶፩ ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እምኢበከየ በእንተ ሞተ አልዓዛር። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢያውጽኦ በጽዋዔ እምከርሠ ገሐር። ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እምኢተጽዕነ ዲበ እድግት ወዕዋላ። ሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢተሰብሐ እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት።ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እምኢተጸፍአ እምአግብርተ ሊቃነ ካህናት። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢያገብአ እዝነ ለዘመተረ ጴጥሮስ በመጥባሕት።ወሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እመኢቆመ ቅድመ ዐውደ ጲላጦስ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እም ኢይቤሎ ለጲላጦስ ወሶበሰ ኮነ እምዝ ዓለም መንግሥትየ እምተበአሱ ወእምተቃተሉ ሊተ ወዓልያንየ ከመ ኢያግብኡኒ ለአይሁድ ገቢኦ። ማቴ፳፮፥፲፮ ዮሐ፲፰፥፴፮ ፤፲፰፥፷፯

፶፪ ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዌሁ ፍጡረ እመኢለብሶ አልባሲሁ ሐራ ጲላጦስ። ወሶበሂ

ከሰምራዊቷ ሴት ውኃ ባልጠየቀ፤ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን የገሊላ ክፍል በምትሆን በቃና ውኃውን ወይን ባላደረገ፤ሥጋው ፍጡር ባይሆን ደም የሚፈሳት ሴት የልብሱን ጫፍ ኃጢአተኛ ሞም እግሮቹን ባልዳሰሰች መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን ልብሱን ስለዳሰሰችይቱ ሴት ከእኔ ኃይል እንደወጣ በውቂአለሁ ባላለ። መለኮትን ኃይል አለው በመለኮትም ኃይል የደሟን ፈሳሽ አደረቀ እግሮቹን ስለዳሰሰች ኃጢአተኛይቱም ሴት ኃጢአትሽ ተሠርዮልሻል ባላላት ከበቻውን ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአትን ማስተሠረይ እንግዲህ ማን ይችላል። ሥጋው ፍጡር ባይሆን ልጄ ብሎ የኢያኢሮስን ሴት ልጅ ባልጠራት ነበር መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን ከሞተች በኋላ ሕያዊት ሆና ባላስነሣት።

፵፱ ሥጋው ፍጡር ባይሆን በምራቁ እንትፍ ብሎ መሬት ላይ ጭቃ ባላደረገ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ምራቁን በመቀባት ዓይናቹን ባላበራ፤ ሥጋው ፍጡር ባይሆን ሞገድ ሲነሣ በመርከብ በውስጠኛው ክፍል ባልተኛ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን ነፋሳትን በመገሠጽ ባሕርን ጸጥ ባላደረጋት ነበር። ማቴ፳፥፳፱ ዮሐ፱፥፩-፯

፶ ሥጋው ፍጡር ባይሆን መንገድ በመሄድ ባልደከመ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን እግረ ሰባሮችን ባላዳናቸው እንደ ጉበዝ ሩጫም እንዲሮጡ ባላደረጋቸው።ሥጋው ፍጡር ባይሆን ባልተራበ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን አምስቱን ሺህ ሰዎች በአምስት እንጀራ በሁለት ዓሣዎች አራቱን ሺህ ሰዎች በሰባት እንጀራ በጥቂት ዓሣዎች ባላጠገባቸው ነበር። ማቴ፲፭፥፩፥፲፭፥፴፪-፴፱ ዮሐ፮፥፫-፲፬

፶፩ ሥጋው ፍጡር ባይሆን ስለ አልዓዛር ሞት ባላለቀሰ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን በመጥራት ከመቃብር ውስጥ ባላወጣው፤ ሥጋው ፍጡር ባይሆን በአህያይቱና በውርንጭላዋ ላይ ባልተቀመጠ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን በሕፃናትና በሚጠቡት አፍ ባልተመሰገነ።ሥጋው ፍጡር ባይሆን በሊቃነ ካህናት አገልጋዮች በጥፊ ባልተመታ ነበር። መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን በጴጥሮስ ሰይፍ የተቆረጠውን ሰው ጆሮ ባልመለሰ። ሥጋው ፍጡር ባይሆን በጲላጦስ አደባባይ ባልቆመ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን ጲላጦስን መንግሥቴ በዚህ ዓለም ቢሆን ኖር አይሁድ ወዳንተ አሳልፈው እንዳይሰጡኝ ባለሟሎቼ ፈጽመው በተዋጉልኝ ነበር ባላለው ነበር። ማቴ፳፮፥፲፮ ዮሐ፲፰፥፴፮ ፤፲፰፥፷፯

፶፪ ሥጋው ፍጡር ባይሆን የጲላጦስ ወታደሮች ልብሱን ባልገፈፉት መለኮቱም ፈጣሪ

ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢኀደረ ፀሐይ ነጽርቶ ዕርቃና ወእምኢሠወረ ብርሃና በእጽልሞተ ዓለም። ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዊሁ ፍጡረ እምኢይቤ አምላኪየ አምላኪየ ነጸረኒ ወለምንት ኀደገኒ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢይቤ ኀዕበ አባ ውስተ እደ-ከ አማኀፅን ነፍስየ። ማቴ፳፯+፵፭-፶፯

፶፫ ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዊሁ ፍጡረ እምኢጥዕመ ሞተ በሥጋ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢያንቀልቀላ ለምድር ወእምኢሰጠጠ ለመንጦላዕተ ቤተመቅደስ።ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዊሁ ፍጡረ እምኢተረግዘ በኩናተ ሐራዊ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እመ ኢያንቅዐ ኩኩሐ ንጉበተ ደመ ወእምኢያንሥእ ሙታነ ጠለ ምሕረት በውኀዘ እምገቦሁ። ማቴ፳፯+፶፱ ዮሐ፲፱+፴፬

፶፬ ወሶበሰ ኢኮነ ሥጋዊሁ ፍጡረ እምኢኖመ ውስተ ከርሠ መቃብር ከመ አብድንተ ትካት። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እመኢሥጣ ለነፍሱ ውስተ ሥጋሁ ለአንሥኦ በከመ ይቤ ለሊሁ ለልየ እሜጥዋ በፈቃድየ። ብውሕ ሊተ አንብራ ወካዕበ ብውሕ ሊተ አንሥኣ። ወዘንተ ትእዛዘ ነሣእኩ በኀበ አቡየ። ዮሐ፲+፲፰

፶፭ ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዊሁ ፍጡረ እመኢረፈቀ ምስለ አርዳኢሁ ለበሊዐ ማዕድ በምሴተ እሑድ እንተ ባቲ ተንሥአ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢነፍሐ ውስተ ገጾሙ ለአርዳኢሁ እንዘ ይብል ንሥኡ መንፈሰ ቅዱሰ ለእለ ኀደግክሙ ኀጢአተ ይትኀደግ ሎሙ ወለእለ ኢኀደግክሙ ኢይትኀደግ ሎሙ። ሶበሰ ኢኮነ ሥጋዊሁ ፍጡረ እምኢያኀብረ እደዊሁ ላዕለ ሐዋርያቲሁ በከመ ሥርዓተ መምህራን ላዕለ አርዳእ። ወሶበሂ ኢኮነ መለኮቱ ፈጣሬ እምኢተ ጽዕነ በደመና እሳት ወእምኢተሰዐለ ውስተ ኑኃ አርያም ወእምኢነበረ በየማነ አቡሁ። ዮሐ፳+፲፰-፳፫ ሐዋ፩+፱

፶፮ ነገርነኬ በእንተ ህላዌ መለኮቱ ወትስብእቱ እምድኅረሰ ሥጋዊሁ ኢንኤሉ ወልደ እግዚአብሔር በመለኮቱ ወወልደ እጓለ እመሕያው በትስብእቱ፡ ድንግልኒ ወለደት ዘኢ.ዘአሃ መለኮተ በዘዚአሃ ሥጋ ምስለ ዘዚአሃ ሥጋዊ። አብኒ ወለደ ዘኢ.ዚአሁ ሥጋ በዘዚአሁ መለኮት ምስለ ዘዚአሁ ኃይል ዘህሉና አምላክ። ልደትሰ ቀዳማዊ ባሕቲቱ እግዚአብሔር ዘእምባሕቲቱ እግዚአብሔር ብርሃን ዘእምብርሃን፡ እሳተ ሕይወት ዘእምእሳተ ሕይወት፡ ወልድ ሕያው ዘእምሕያው አብ፡ ኢፍጡር ዘእምኢግቡር፣ ዘኢ.ያስተርኢ እምዘኢ.ይትኤጸር፣ ዘኢ.ይትገሰስ እምዘ ኢይትለከፍ፣ ዘኢ.ይነጻ.ፂ እምዘ ኢይፄነስ፣ ዘኢ.ይ መውት እምዘኢ.ይሰማን፣ ዘኢ.ይበሊ እምዘኢ.ይ

ባይሆን ፀሐይ ዕርቃትን ለማየት ባላፈረ ዓለምንም ጨለማ ውስጥ ለመተው ብርሃኑን ባልሠወረ ሥጋው ፍጡር ባይሆን አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ ባላለ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ ባላለ ነበር። ማቴ፳፯+፵፭-፶፯

፶፫ ሥጋው ፍጡር ባይሆን ሞትን በሥጋ ባልቀመሰ፣ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን ምድርን ባላነዋወጣት የቤተመቅደስንም መጋረጃ ባልቀደዳት ነበር። ሥጋው ፍጡር ባይሆን በጭፍራ ጦር ባልተወጋ መለኮቱም ፈጣሪ ባይ ሆን የደሙ ጠብታ አለቱን ባልሰነጠቀ ከጉኑም የፈሰሰ የምሕረቱ ጠል ሙታንን ባላነሣ። ማቴ፳፯+፶፱ ዮሐ፲፱+፴፬

፶፬ ሥጋው ፍጡር ባይሆን ቀድሞ እንደሞተ በመቃብር ውስጥ ባልተኛ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን እርሱ እኔ ራሴ ነፍሴን በፈቃዴ እሰጣታለሁ ላኖራት ሥልጣን አለኝ ሁለተኛም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህን ትእዛዝ ከአባቴ ዘንድ ተቀበልሁ እንዳለ ለማስነሣት ነፍሱን ወደ ሥጋው ባልመለሣት። ዮሐ፲+፲፰

፶፭ ሥጋው ፍጡር ባይሆን በተነሣባት እሑድ ምሽት ለመመገብ በማዕድ ከደቀመ ዛሙርቱ ጋር ባልተቀመጠ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን መንፈስቅዱስን ተቀበሉ ኃጢአታቸውን ይቅር ላላችኋቸው ይቀርላቸዋል ኃጢአታቸውን ይቅር ላላላችኋቸው አይቀርላቸውም ብሎ በደቀ መዛሙርቱ ፊት ላይ እፍ ባላለባቸው ነበር። ሥጋው ፍጡር ባይሆን መምህራን በተማሪዎች እንደሚያደርጉት ሥርዓት እጁን በሐዋርያቱ ራስ ላይ ባላኖረ መለኮቱም ፈጣሪ ባይሆን በእሳት ደመና ባልተጫነ ወደ ሰማይም ከፍ ከፍ ብሎ በአባቱ ቀኝ ባልተቀመጠ ነበር። ዮሐ፳+፲፰-፳፫ ሐዋ፩+፱

፶፮ ስለመለኮቱና ስለ ትስብእት ህልውና እነሆ ተናገርን። ሰው ከመሆኑ በኋላ በመለኮቱ የእግዚአብሔር ልጅ በሰውነቱም የሰው ልጅ ነው እንለውም።ድንግልም ለርሷ በተገባ ሥጋዊ የርሷ በሆነ ሥጋ የርሷ ያልሆነውን መለኮትን ወለደችው። አብም የባሕርዩ ያልሆነውን ሥጋ የባሕርዩ ከሆነ የህሉና አምላክ ኃይል ጋር የርሱ በሆነ መለኮት ወለደ። ቀዳማዊ ልደትሰ ብቻውን ከሚሆን ከእግዚአብሔር ብቻውን የሆነ እግዚ አብሔር ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከሕይወት እሳት የተገኘ የሕይወት እሳት ከሕያው አብ የተገኘ ሕያው ወልድ፣ ፍጡር ካይደለ የተወለደ ያልተፈጠረ ከማይታይ የተገኘ የማይታይ፡ ከማይዳሰስ የተወለደ የማይዳሰስ ከማይችገር

ትነሣት ዘኢይነውም እምዘኢይዴቅስ ዘኢይዴምን እምዘኢይጸልም ዘኢይትሌቦ እምዘ ኢይጤየቅ ዘኢይትበዐድ እምዘኢይትዌለጥ ዘኢይደክም እምዘ ኢይፀብስ ዘኢይትቤቀል እምዘ ኢይትቄየም ዘኢይቀብል እምዘኢየሐጽጽ ዘኢይረኩስ እምዘ ኢይረስሕ:: መዝ ፻፲፱፥፩

፶፯ በእንተ መንፈስቅዱስ ንነግር ከመ ኢሕጹጽ ውእቱ በዕበየ ስን በአካል ወበመልክዕ እምሕሱና አብ ወወልድ ኢፍሉጥ ውእቱ ወኢሊሉይ ውእቱ ኢነኪር ውእቱ ወኢብዑድ ውእቱ ስብሐቲሁ ከመ ስብሐቲሆሙ ወመልክዐ ገጹ ዘከመ አርአያሆሙ:: እትዛን በጽምረት ወድሙራን በተዋሐዶ ግልቡባን በነደ እሳት ወክዱናን በሥዋሬ ኅቡኣን በእንጦላዒ:: ኢርኩባን በኅልዮ ወክቡታን በምሥጣሬ:: ልዑላን እምሰማየ ሰማያት ወዕሙቃን እምቀላየ ቀላያት:: ወስፉሓን እምአጽናፈ አጽናፍ አኮ በኩፋሌ አላ በትባሬ: አኮ በተሌልዮ አላ በጽመረተ ህላዌ::

፶፰ ስብሐት ለሥላሴሆሙ ዘኢይዘረው: አኩቴት ለድማሬሆሙ ዘኢይቶሳሕ: ዕበይ ለህላዌሆሙ ዘኢይትከፈል ለዓለመ ዓለም :: አሜን : ወአሜን

፶፱ ተፈጸመ ዘለፋሁ ለአርዮስ ዓላዊ: ዘበጽልሑተ ልቡ ጉሕላዊ: እሰረ ሰይጣን ተላዊ ለመራዕየ ከለባት ኖላዊ: ዘነበበ ጽርፈተ ላዕለ መለኮተ ኢየሱስ ገሊላዊ: ይቤ ጊዮርጊስ ሰግላዊ: ዘበሃይማኖቱ ክርስቲያናዊ: ዘበሕገ ሙሴ ኦሪታዊ: ወዘበክርስቶስ ወንጌላዊ: ዘበማኅተሙ መስቀላዊ: ዘበተከንሶ መርጡላዊ: ዘበትብዐ ጥምቀቱ ናዝራዊ: ወበምግባሩሰ ኃጥእ ወዘማዊ: ስብሐት ለእግዚአብሔር ሕያው ወማሕየዊ ለዓለመ ዓለም አሜን: ወአሜን::

——— /// ———

የተወለደ የማይቸገር፤ከማይጠፋ የተወለደ የማይጠይፋ ከማይፈርስ የተወለደ የማያረጅ ከማያንቀላፋ የተገኘ የማይተኛ፤ ከማይጨልም የተገኘ የማይጠቁር፤ ከማይመረመር የተወለደ የማይለይ፤ድካም ከሌለበት የተወለደ የማይደክም ከማይበቀል የተወለደ የማይቀየም፤ከማይጉድል የተወለደ የማይጉድል ከማያድፍ የተወለደ የማይረክስ ነው:: መዝ ፻፲፱፥፩

፶፯ ስለመንፈስቅዱስም በጌትነት በክብር በአካል በመልክ ከአብና ከወልድ የማያንስ እንደሆነ እንናገር:: ፈጽሞ የማይለይ ነው:: ክብሩ እንደ ክብራቸው የፊቱም መልክ እንደ መልካቸው ነው በአንድነት የተያያዙ በአንድነትም አንድ በእሳት የተሸፈኑ በመሠወር የተከደኑ በመጋረድ የተሸሸጉ በማሰብ የማይገኙ በመራቀቅ የተሸሸጉ ከሰማየ ሰማያት ይልቅ ከፍ ከፍ ያሉ ከቀላየ ቀላያት ይልቅ ጥልቅ የሆኑ ከአጽናፍ አጽናፍ ይልቅ የሚሰፉ ናቸው:: በመከፋፈል አይደለም በመተባበር ነው እንጂ በመለያየት አይደለም በባሕርይ አንድነት ነው እንጂ::

፶፰ ለማይበታተን ሦስትነታቸው ምስጋና ለማይጨመርበት አንድነታቸውም አኩቴት ለማይከፈል ህልውናቸው ጌትነት ይገባል ለዘላለሙ አሜን: አሜን::

፶፱ በሸንጋይ ልቡ የሚሸነገል የሰይጣንን አሠር የሚከተል የውሾችን መንጋ ጠባቂ በገሊላዊ ኢየሱስ አምላክነት ላይ ስድብን የተናገረ የከሀዲው የአርዮስ ተግሣጽ ተፈጸመ: በሃይማኖቱ ክርስቲያናዊ በሙሴም ሕግ ኦሪታዊ በክርስቶስም ወንጌላዊ በማኅተሙም የመስቀል አማኝ የሆነ በጥምቀቱ ቅባት ናዝራዊ የሆነ በሥራው ግን ኃጢአተኛ የሆነ ጊዮርጊስ ተናገረው፤ሕያው ለሆነ ሕይወትንም ለሚያድል ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን::

——— /// ———